# ኦሪት ዘኢያሱ

ምዕራፍ ፩ ።

፩ ወኮነ እምድኅረ ሞተ ሙሴ ገብረ እግዚአብሔር ፡ ይ
ቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወልደ ነዌ ላእኩ ለሙሴ ።

፪ ናሁ ሞተ ሙሴ ቍልዔየ ወይእዜኒ ተንሥእ ወዕድዎ
ለዝንቱ ዮርዳኖስ አንተ ወኵሉ ዝንቱ ሕዝብ ውስተ ምድ
ር እንተ እሁበክሙ አነ ለክሙ ለደቂቀ እስራኤል ።
፫ ኵሎ መካነ ኀበ ኬዳ እገሪክሙ ለክሙ ነዋ እሁበክሙ
በከመ እቤሎ ለሙሴ ።
፬ እምገዳም ዘአንጢሊባኖን እስከ ፈለግ ዐቢይ ፡ ፈለገ
ኤፍራጥስ ኵሎ ምድሮሙ ለኬጥያውያን ወእስከ ደኃሪት
ባሕር ፡ ወእስከ ምዕራብ ፀሐይ ይኩን ደወልክሙ ።

፭ ወአልቦ ሰብእ ዘይትቃወም ቅድሜከ በኵሉ መዋዕለ
ሕይወትከ ወበከመ ሀሎኩ ምስለ ሙሴ ከማሁ እሄሉ ምስ
ሌከ ወኢየኀድገከ ወኢይትዔወረከ ።
፮ ጽናዕ ወትባዕ እስመ አንተ ትከፍሎሙ ለኵሎሙ ለዝ
ንቱ ሕዝብ ምድረ እንተ መሐልኩ ለአበዊሆሙ ከመ
አሀበሙ ።
፯ ወባሕቱ ጽናዕ ወትባዕ ጥቀ ከመ ትዕቀብ ወትግበር
ኵሎ ሕገ ዘከመ አዘዘከ ሙሴ ቍልዔየ ፡ ወኢትትገ
ኃሥ እምኔሁ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ከመ ታእምር ኵሎ
ዘከመ ትገብር ።
፰ ወኢትትኀደግ መጽሐፉ ለዝንቱ እምአፉከ ወአንብብ
ቦቱ መዐልተ ወሌሊተ ከመ ታእምር ኵሎ ገቢረ ዘጽሑፍ
ውስቴቱ እስመ ትረትዕ ፍኖትከ ወቦቱ ትጠበብ ።
፱ ወናሁ እኤዝዘከ ትባእ ወጽናዕ ወኢትፍራህ ወኢት
ደንግፅ እስመ ሀለወ እግዚአብሔር አምላክከ ምስሌከ ው
ስተ ኵሉ ዘሖርከ ።
፲ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለጸሐፍተ ሕዝብ ወይቤሎሙ ፡ ባኡ
ውስተ ትዕይንት ወአዝዝዎሙ ለሕዝብ ወበልዎሙ አስተ
ዳልዉ ለክሙ ስንቀ ።
፲፩ እስመ እስከ ሠሉስ መዋዕል ተዐድውዎ ለዝንቱ ዮር
ዳኖስ አንትሙ ወትበውኡ ምድረ እንተ ይሁበክሙ እግ
ዚአብሔር አምላከ አበዊክሙ ከመ ትትዋረስዋ ።

፲፪ ወለሮቤልሂ ወለጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴሂ ይቤ
ሎሙ ኢያሱ ፡ ተዘከሩ ቃለ ዘአዘዘክሙ ሙሴ ቍልዔሁ

ምዕራፍ ፩ ።

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ከሞተ በኋላ እንዲህ
ሆነ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ የነዌ ልጅ ኢያሱን
እንዲህ አለው ። ዘፀ ፳፬ ፲፫ ፡ ዘዳ ፩ ፴፰ ።
እነሆ ባለሟሉ ሙሴ ሞተ አሁን ተነሥተህ አንተ ይህንን
ዮርዳኖስ ተሻገረው ለናንተ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ እኔ
ወደ ምሰጣችሁ አገር ለመሄድ ይህም ሁሉ ወገን ይሻገረው።
ለሙሴ እንደ ነገርሁት እግሮቻችሁ የረገጡትን በታ
ሁሉ እነሆ ለናንተ እሰጣችኋለሁ። ዘዳ፡ ፲፩ ፳፬ ።
ከአንጢሊባኖን ምድረ በዳ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ
እስከ ኤፍራጥስ ድረስ የኬጥያውያንን አገር ሁሉ እሰጣች
ኋለሁ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስና እስከ ኋለኛይቱ ባሕር
ድረስ ወሰናችሁ ይሁን። ዘፍ፡ ፲፭ ፲፰ ፡ ዘፀ፡ ፳፫ ፴፩ ።
በሕይወት በኖርክበት ዘመን ሁሉ በፊትህ የሚከራ
ከር የለም ከሙሴ ጋር በረድኤት እንደ ኖርሁ ካንተም
ጋራ በረድኤት እኖራለሁ አልለይህም ቸልም አልልህም።
እሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማልኩላቸውን ም
ድር አንተ ለነዚህ ወገኖች ትከፍላቸዋለህና ጨክን ፡
በርታ አለው ። ዘዳ፡ ፴፩ ፫ ።
ነገር ግን ባለሟሉ ሙሴ እንዳዘዘህ ሕጉን ሁሉ ጠብ
ቀህ ታደርግ ዘንድ ፈጽመህ በርታ ጨክን ፡ የምታደርገ
ውን ሁሉ ታውቅ ዘንድ ከሱ ወደ ፊትም ወደ ግራም
አትበል ። ዘዳ፡ ፭ ፴፪ ፡ ኢያ፡ ፲፩ ፲፭ ።
ይህም መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ፡ ሥራህ ትቀናለችና
በሱም አዋቂ ትሆናለህና በሱ የተጻፈውን ሥራ ታውቅ
ዘንድ በመዓልትም በሌሊትም እሱን አንብብ ።
እነሆ አዝሃለሁ በሄድክበት ጐዳና ሁሉ ፈጣሪህ እግ
ዚአብሔር ካንተ ጋራ በረድኤት አለና ጨክን ፡ በርታ ፡
አትፍራ ፡ አትደንግጥ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፫ ፡ ኢያ፡ ፩ ፮ ።
ኢያሱም በሕዝቡ ላይ የተሾሙትን ሹማምንት ወደ
ሰፈር ገብታችሁ ለናንተ ስንቅ አዘጋጁ ብላችሁ እዘዙዋ
ቸው አላቸው ።
እስከ ሦስት ቀን ድረስ እናንተ ይህን ዮርዳኖስ ትሻገ
ሩታላችሁ ትወርሷት ዘንድ ያላችሁ ያባቶቻችሁ ፈጣሪ
እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣችሁ ምድርም ትገባላችሁ ብሎ
አዘዛቸው ። ኢያ፡ ፫ ፪ ።
ጋድንና ሮቤልን የምናሴን ነገድ እኩሌቶችንም ኢያሱ
እነሆ እግዚአብሔር ይህችን አገር ሰጥቶ እናንተን አሳረፋ

ለእግዚአብሔር ወይቤለክሙ ናሁ አዕረፈክሙ እግዚአብ
ሔር ለክሙ ወወሀበክሙ ዛተ ምድረ ።
፲፬ ወይንበራ አንስቲያክሙ ወደቂቅክሙ ወእንስሳክሙ
ውስተ ዛቲ ምድር ዘወሀበክሙ ሙሴ በማዕዶተ ዮርዳኖስ
ወአንትሙሰ ዕድው ዮርዳኖስ ቅኑታኒክሙ ቅድመ አኀዊ
ክሙ ኵሉ ጽኑዓኒክሙ ፡ ወተቃተሉ ሎሙ እስከ አመ
ያዐርፎሙ እግዚአብሔር አምላክነ ለአኀዊክሙ ከማክሙ ።

፲፭ ወይወርሱ እሙንቱኒ ምድሮሙ እንተ ይሁቦሙ እግዚ
አብሔር አምላክነ ፡ ወተአትዉ እንከ አሐዱ አሐዱ እም
ኔክሙ ውስተ ርስትክሙ ፡ ወትወርስዋ አንትሙ ለዛቲ
ምድር ዘወሀበክሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር በማ
ዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ምሥራቀ ፀሐይ ።
፲፮ ወአውሥእዎ ለኢያሱ ወይቤልዎ ንገብር ኵሉ ዘአዘ
ዝከነ ፡ ወንሖውር መከነ ኀበ ፈነውከነ ።
፲፯ ወበከመ ተአዘዝነ ለሙሴ በኵሉ ፡ ከማሁ ንትኤዘዝ
ለከሂ ፡ ወባሕቱ ምስሌከሂ የሀሉ እግዚአብሔር በከመ
ሀለወ ምስለ ሙሴ ።
፲፰ ወብእሲ ዘኢተአዘዘ ለከ ወዘክሕደከ ወዘኢሰምዐ ቃ
ለከ ዘአዘዝከሁ ለይሙት ፡ ወይእዜኒ ጽናዕ ወትባዕ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

፩ ወፈነወ ኢያሱ እምሰጢን ክልኤተ ወራዙተ ሰብአ
ዐይን ጽሚተ ወይቤሎሙ ዕርጉ ወረአይዋ ለይእቲ ምድር
ወለኢያሪኮሂ ።
፪ ወሖሩ እልክቱ ክልኤቱ ወራዙት ወበጽሑ ኢያሪኮ
ወቦኡ ውስተ ቤተ አሐቲ ብእሲት ዘማ እንተ ስማ ራኬብ
ወኀደሩ ህየ ።
፫ ወአይድዕዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ወይቤልዎ ቦኡ ዝየ እደ
ው በሌሊት እምደቂቀ እስራኤል ሰብአ ዐይን ከመ ይር
አዩ ብሔረነ ።
፬ ወለአከ ንጉሠ ኢያሪኮ ኀበ ራኬብ ወይቤ በልዋ ለራ
ኬብ ፡ አውፅኢ እደወ እለ ቦኡ ኀቤኪ ሰብአ ዐይን እሙ
ንቱ ወከመ ይርአዩ ብሔረነ መጽኡ ።
፭ ወነሥአቶሙ ይእቲ ብእሲት ለእልክቱ እደው ወኀብ
አቶሙ ወትቤ እደውሰ ቦኡ ኀቤየ ወኢያአመርኩ እም
አይቴ እሙንቱ ።
፮ ወእንዘ ዕፅው ኆኅት ወበጽልመት ወፅኡ ውእቶሙ
እደው ወኢያአመርኩ አይቴ እንከ ሖሩ ፡ ወሑሩ እንከ
ፍጡነ ትልውዎሙ ወዴግንዎሙ ዮጊ ትረክብዎሙ ።
፯ ወይእቲሰ አዕረገቶሙ ውስተ ናሕስ ወኀብአቶሙ
ማእከለ ዕፀው ውስተ ሐሰት ዘወጡሕ ።
፰ ወዴገንዎሙ ውእቶሙ እደው እንበለ ይቢቱ ፡ ወይ
እተ ጊዜ ዐርገት ኀቤሆሙ ውስተ ናሕስ ፡ ወትቤሎሙ
አአምር ከመ አግብአ እግዚአብሔር ለብሔር ለክሙ ።
፱ እስመ አምጽአ እግዚአብሔር ፍርሀተክሙ ላዕሌነ ወተ
መንሰዉ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ብሔር እምገጽክሙ ።
፲ እስመ ሰማዕነ ከመ አይበሳ እግዚአብሔር ለባሕረ ኤር
ትራ እምቅድመ ገጽክሙ አመ አውፅአክሙ እምድረ ግብ

ችሁ ብሎ የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ ያዘዛችሁን ቃል
አስታውሱ ። ዘኍ፡ ፴፪ ፳ - ፴፫ ።
ሚስቶቻችሁ ፥ ልጆቻችሁና ከብቶቻችሁ ሙሴ በዮር
ዳኖስ ወድያ ማዶ በሰጣችሁ በዚች አገር ይቀመጡ ፥ እና
ንተ ግን እፉ - እፋችሁን ታጥቃችሁ አርበኞቻችሁ ሁሉ
ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንደናንተ እስኪያሳርፋቸው
ድረስ በወንድሞቻችሁ ፊት ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ
ተዋጉዋቸው ።
እነሱቸውም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን
ምድራቸውን ይወርሳሉ ከዚህ በኋላ ከናንተ አንዱም አን
ዱም ወደ ርስታችሁ ትመለሳላችሁ ፥ እናንተም የእግዚአ
ብሔር ባለሟል ሙሴ በፀሐይ መውጫ በኩል በዮርዳኖስ
ማዶ የሰጣችሁ ይህችን ምድር ትወርሷታላችሁ አላቸው።
እነሱም ያዘዝከንን ሁሉ እናደርጋለን ወዳልከንም ቦታ
እንሄዳለን ብለው መለሱለት ።
ለሙሴ በሁሉ እንደታዘዝን ላንተም እንደሱ እንታዘ
ዛለን ብቻ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በረድኤት እንደኖረ
ከንተም ጋራ በረድኤት ይኑር ። ኢያ፡ ፩ ፭ ።
ላንተ ያልተዘዘ አንተን ክዶ ያዘዝከውን ቃል ያልሰማ
ሰው ይሙት ፥ አሁንም ጨክን በርታ ።

## ምዕራፍ ፪ ።

ኢያሱ ሁለቱን ጒብኞች ሰውሮ ከሰጢን ልኮ ወጥ
ታችሁ ያችን ምድር እዩዋት ኢያሪኮንም እዩዋት አላ
ቸው ።
እነዚያም ሁለት ጐልማሶች ሂደው ኢያሪኮ ደርሰው
ስሟ ራዓብ ወደምትባል ወደ አንዲት ዘማ ሴት ቤት ገብ
ተው በዚያ አደሩ ። ኢያ፡ ፩ ፲፩ ፡ ፫ ፪ ፡ ማቴ፡ ፩ ፭ ።
አገራችንን ያዩ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች ጒብኝዎች
ሰዎች እነሆ በሌሊት ገቡ ብለው ለኢያሪኮ ንጉሥ ነገሩት።

የኢያሪኮም ንጉሥ ዘማ ወደምትሆን ወደ ራዓብ ልኮ
ራዓብን አገራችንን ያዩ ዘንድ መጥተው ከንቺ ዘንድ የገቡ
እነዚያን ጒብኝዎች ሰዎች አውጪ በሏት አለ ።
ያችም ሴት እነዚያን ሁለቱን ጐልማሶች ወስዳ ሠወረ
ቻቸው ፥ ሰዎች ከኔ ዘንድ ገብተው ነበር ፥ ነገር ግን ወዴ
ት እንደ ሄዱ አላወቅሁም ። ፪ ሳሙ፡ ፲፯ ፲፱ ።
ደጃፉ ተዘግቶ ሳለ እነዚያ ሰዎች በጨለማ ወጡ ፥ ወ
ዴት እንደ ሄዱም አላውቅሁም ፥ ፈጥናችሁ ሂዱችሁ ተከ
ተሏቸው ወይ ታገኙዋቸው ይሆናል አለቻቸው ።
እሷ ግን ወደ ሰገነት አውጥታ በተከመረ ዕንጨት
መካከል በቀርቅሃ ጠቅልላ አቆመቻቸው ።
እነዚያም ሰዎች ሳያድሩ ተከሏቸው ፥ ያን ጊዜ ወደነ
ሳቸው ወደ ሰገነት ወጥታ እግዚአብሔር አገሪቱን ለናንተ
አሳልፎ እንደ ሰጣት አውቃለሁ ።
መፈራታችሁን በኛ ላይ አምጥቶ ብናልና ከናንተ ፊት
የ ኮነማም በአገር የሚኖሩ ሰዎች እንደ ሰም ቀልጠዋልና ።
ከግብጽ ምድር በወጣችሁ ጊዜ ከፊታችሁ የኤርትራን
ባሕር እግዚአብሔር እንዳደረቀላችሁ በዮርዳኖስ ማዶም

ጽ ወኵሎ ዘገብረ ላዕለ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕ
ዶተ ዮርዳኖስ ለሴዎን ወለዖግ እለ ሠረውክምዎሙ ።

፲፩ ወሰበ ሰማዕነ ንሕነ ደንገፅነ በልብነ ወኢተርፈ ነፍስ
አሐዱ እምኔነ እምቅድመ ገጽክሙ እስመ እግዚአብሔር
አምላክክሙ ውእቱ አምላክ በሰማይ በላዕሉ ወበምድር
በታሕቱ ።
፲፪ ወይእዜኒ መሐሉ ሊተ በእግዚአብሔር በከመ ገበርኩ
ምስሌክሙ ምሕረተ ከመ ትግበሩ ምስሌየ ምሕረተ ወም
ስለ ቤተ አቡየ ወተሀቡኒ ተአምረ በጽድቅ ።
፲፫ ወአሕይዉ ቤተ አቡየ ወእምየኒ ወአኀውየኒ ወኵሎ
ቤትየ ወኵሎ ዘዚአሆሙ ወአድኅኑ ነፍሰነ እሞት ።

፲፬ ወይቤልዋ እሙንቱ እደው ነፍስነ ህየንቴክሙ ውስተ
ሞት ።
፲፭ ወትቤሎሙ ይእቲ አመ አግብአ እግዚአብሔር ለሀ
ገርነ ውስተ እደዊክሙ ግበሩ ምስሌየ ምሕረተ ወጽድቀ።
፲፮ ወይቤልዋ እሙንቱ እደው ለእመ ኢያየ ዳዕኪ በእን
ቲአነ ንገብር ምሕረተ ምስሌኪ ለእመ አግብአ እግዚአብ
ሔር ለሀገርክሙ ለነ በጽድቅ ።
፲፯ ወአውረደቶሙ በሐብል እንተ መስኮት እስመ ቤታ
በጥቅም ውእቱ ወትነብር ይእቲ ውስተ ሀረፍት ።
፲፰ ወትቤሎሙ ሑሩ እንተ ደብር ከመ ኢይርከቡክሙ
እለ ይዴግኑክሙ ወትኀብኡ ህየ ሠሉሰ መዋዕለ እስከ ይገ
ብኡ እለ ይዴግኑክሙ ወእምዝ ትገብኡ ውስተ ፍኖት
ክሙ ።
፲፱ ወይቤልዋ እሙንቱ እደው ፣ ንጹሓን ንሕነ እመሐ
ላኪ ዘአምሐልክነ ።
፳ ናሁ ንሕነ ንበውእ ውስተ ጽንፈ ሀገር ወደዪ ዘንተ
ፈትለ ቀይሐ ዘለይ ውስተ መስኮት እንተ ባቲ አውረድክነ
ወአበኪኒ ወእሙኪኒ ወአኀዊኪኒ አስተጋብኢ ኀቤኪ ው
ስተ ቤትኪ ።
፳፩ ወኵሉ ዘወፅአ አፍአ እምነ ኆኅተ ቤትኪ ይመውት ፣
ወንሕነሰ ንጹሓን ንሕነ እምዝንቱ መሐላ ዘአምሐልክነ
ወበሕቱ ኵሉ ዘሀለወ ምስሌኪ ውስተ ቤትኪ ለእመ ሞተ
ላዕሌነ ኀጢአት ።
፳፪ ወለእመሰ ከሠትኪ ነገረነ ንጹሓን ንሕነ እምዝንቱ
መሐላኪ ፣ ወትቤሎሙ ይኩን በከመ ትቤሉ ።
፳፫ ወፈነወቶሙ ወሖሩ ወአሰረት ዝክተ ፈትለ ዘለይ
በመስኮት ፣ ወወፅኡ ወሖሩ ውስተ ደብር ።
፳፬ ወነበሩ ህየ ሠሉሰ መዋዕለ እስከ ገብኡ እለ ዴገን
ዎሙ ወኀሠሥዎሙ ወኢረከብዎሙ ውስተ ፍናዊሆሙ ።

፳፭ ወገብኡ እልክቱ እደው ወወረዱ እምደብር ወኀለፉ
ወበጽሑ ኀበ ኢያሱ ወልደ ነዌ ወዜነውዎ ኵሎ ዘገብሩ ።
፳፮ ወይቤልዎ አግብአ እግዚአብሔር ኵሎ ምድረ ውስተ
እደዊነ ወደንገፁ ኵሎሙ አሕዛብ እለ ይነብሩ ውስተ ይእቲ
ምድር እምኔነ ።

በሉ ነገሥታት በጠፉችኋቸው በዓግና በሴዎን ላይ ያደረ
ገውን ሁሉ ስለ ሰማን ለናንተ አሳልፎ እንደ ሰጣት አው
ቃለሁ አለቻቸው ። ዘፀ፣ ፲፭ ፲፯ ፣ ፳፫ ፳፯ ።
እኛም በሰማን ጊዜ ልቡናችን ደነገጠ ፣ ከፊታችሁም
የተነሣ ከኛ ያንዱ ሰውነት ስንኳ ሳትደነግጥ አልቀረችም
ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከምድር በላይ ባለ በሰማይ ከሰ
ማይ በታች ባለ በምድር ፈጣሪ ነውና ።
አሁንም ለናንተ በጎ እንዳደረግሁላችሁ ለኔም ላባቴም
ወገን በጎ ታደርጉልኝ ዘንድ በእግዚአብሔር ማሉልኝ ፣
በእውነትም ምልክት ስጡኝ ። ዘፀ፣ ፲፭ ፲፬ ።
የናቴንና ያባቴን ወገን ወንድሞቼንም ወገኔንም ሁሉ
ወገናቸውንም ሁሉ አድኑ ፣ ሰውነታችንም ከሞት አድኑ
አለቻቸው ።
እነዚያም ሰዎች ሰውነታችንን ስለናንተ ለሞት አሳል
ፈን እንሰጣለን አሏት ።
ያችም ሴት እግዚአብሔር አገራችንን በእጃችሁ ከጣ
ላት ለኔ ቸርነትንና ይቅርታን አድርጉልኝ አለቻቸው ።
እነዚያም ሰዎች እግዚአብሔር በእውነት አገራችሁን
በእጃችን ከጣለልን የኛን ነገር (ምሥጢር) ካላወጣሽ ቸር
ነት እናደርግልሻለን አሏት ። መሳ፣ ፩ ፳፬ ።
ቤቷ በቅጥር አጠገብ ነውና ፣ እርሷም በቅጥር አጠ
ገብ ትኖራለችና ከመስኮቱ በገመድ አወረደቻቸው ።
የተከተሏችሁ ሰዎች እንዳያገኙዋችሁ ደጋ ደጋውን
ሂዱ ፣ የተከተሏችሁም ሰዎች እስኪመለሱ ድረስ ሦስት
ቀን በዚያ ተሠወሩ ፣ ከዚያ በኋላ ወደ ጉዳናችሁ ትመለ
ሳላችሁ አለቻቸው ።
እነዚያም ሰዎች እኛን ከማልሽልን መሐላ ንጹሐን ነን ፣
አሉዋት ። ዘፀ፣ ፳ ፯ ፣ ኢያ፣ ፯ ፳፫ ።
እነሆ እኛ ወደ አገር ዳርቻ እንገባለን ይህን የቀይ ሐር
ፈትል እኛን በወረድሽበት መስኮት አድርጊ (እሰሪ) እናት
ሽንና አባትሽን ወንድሞችሽንም ከንቺ ዘንድ በቤትሽ
ሰብስቢ ። ዘፍ፣ ፴፰ ፳፰ ፣ ኢያ፣ ፪ ፲፱ ።
ከቤትሽ ደጃፍ ወደ ውጪ የወጣው ሁሉ ይሞታል ፣
እኛ ከዚህ ከማልሽን መሐላ ንጹሐን ነን ፣ ካንቺ ጋራ በቤ
ትሽ ያለው ሁሉ ቢሞት ግን በኛ ዕዳ ይሆንብናል ።

ነገራችንን (ምሥጢራችንን) ብታወጪ ግን ከዚህ ከመ
ሐላሽ ንጹሐን ነን ፣ እንዳላችሁም ይሁን አለቻቸው ።
ሸኘታቸውም ሄዱ ያንንም ቀይ ሐር በመስኮት አሰ
ረች ፣ እነሱም ወጥተው ደጋደጋውን ሄዱ ።
የተከሉዋቸውም ሰዎች እስኪመለሱ ድረስ ሦስት ቀን
በዚያ አደሩ ፣ አሳዳጆቹ በመንገዶቹ ፈልገው አጥተዋ
ቸው ተመለሱ ።
ከዚህ በኋላ እነኛ ሰዎች ከተራራው ወርደው ሄዱ ፣
ከነዌ ልጅ ኢያሱም ዘንድ ደርሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት።
እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ በእጃችን ጣለልን ፣ በዚ
ያች አገር የሚኖሩ አሕዛብም ሁሉ ከኛ የተነሣ ደነገጡ
አሉት ። ኢያ፣ ፯ ፱ ፣ ፰ ፩ ።

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፫ ። | | ምዕራፍ ፫ ። |
| ወጌሠ በጽባሕ ኢያሱ ወግዕዙ እምሰጢን ወበጽሑ ዮርዳኖስ ፡ ውእቱ ወኵሉ እስራኤል ወኀደሩ ህየ እንበለ ይዕድዉ ። | ፩ | ኢያሱ ሲነጋ ገሥግሦ እሱና የእስራኤልም ልጆች ከሰጢን ተጕዘው ዮርዳኖስ ደረሱ ፡ ሳይሻገሩም በዚያ አደሩ ። |
| ወእምድኅረ ሠለስ መዋዕል በኡ ጸሐፍት ማእከለ ትዕይንት ፡ ወአስተጋብኡ ለሕዝብ ። | ፪ | ከሦስትም ቀን በኋላ ሹማምንቱ ከሰፈር ማኸል ገብተው ለሕዝቡ አዋጅ ነገሩ ። ኢያ፡ ፩ ፲፩ ። |
| ወይቤልዎሙ እምከመ ርኢክሙ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክነ ወካህናቲነ ወሌዋውያኒነ እንዘ ይፀውርዋ ግዕዙ እንትሙኒ እመካናቲክሙ ወትሉዉ ድኅሬሃ ። | ፫ | የፈጣሪያችን የእግዚአብሔር የሕጉን ማደሪያ ታቦትን ተሸክመዋት ሌዋውያንና ካህናትን ካያችሁ በኋላ እናን ተም ከበታችሁ ተነሥታችሁ እሷን ተከትላችሁ ተጓዙ ። |
| ወበሕቱ ርኁቀ ይኩን ማእከሌክሙ ወማእከሌሃ መጠነ ዕሥራ ምእት በእመት ወበመስፈርቱ ቀሙ ወኢትቅረብዋ ከመ ታእምሩ ፍኖተ እንተ ተሐውሩ እስመ ኢሐርክምዋ ለይእቲ ፍኖት ትካት ። | ፬ | ነገር ግን በእናና በኛንተ መካከል ሃያ ክንድ ያህል የራቀ ይሁን በመጠኑ ቁሙ ፡ ያችን መንገድ ቀድሞ አልሄዳችሁባትምና የምትሄዱበትን ጐዳና ታውቁ ዘንድ አትቀረቧት ። ዘፀ፡ ፲፱ ፲፪ ፡ ኢያ፡ ፬ ፲፰ ። |
| ወይቤሎሙ ኢያሱ ለሕዝብ አንጽሑ ርእሰክሙ ለጌሠም እስመ ጌሠመ ይገብር እግዚአብሔር መድምመ ለክሙ ። | ፭ | ኢያሱም እግዚአብሔር ለናንተ ነገ ድንቅ ነገር ያደርግላችኋልና ፡ ሕዝቡን ለነገ ራሳችሁን (ከኃጢአት) አንጹ አላቸው ። ዘሌ፡ ፳ ፯ ፡ ኢያ፡ ፯ ፲፱ ። |
| ወይቤሎሙ ኢያሱ ለካህናት ንሥኡ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወሑሩ ቅድመ ሕዝብ ፡ ወነሥኡ ካህናት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወሖሩ ቅድመ ሕዝብ ። | ፮ | ኢያሱም ካህናቱን የእግዚአብሔርን የሕጉን ማደሪያ ታቦትን ይዛችሁ በሕዝቡ ፊት ሂዱ አላቸው ፡ የሕጉንም ማደሪያ ታቦት ይዘው በሕዝቡ ፊት አለፉ ። |
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ በዛቲ ዕለት እኤኑዝ አዕቢዮ በቅድመ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ከመ ያእምሩ ከመ ሀሎኩ ምስሌከ በከመ ሀሎኩ ምስለ ሙሴ ። | ፯ | እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ ከሙሴ ጋር በረድኤት እንደኖርሁ ካንተም ጋር በረድኤት እንዳለሁ ያውቁ ዘንድ እነሆ በዚች ቀን በእስራኤል ፊት ሁሉ አከብርህ አገንህ ዘንድ እጀምራለሁ ። ኢያ፡ ፬ ፲፬ ። |
| ወይእዜኒ አዝዞሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ወበሎሙ እምከመ በጻሕክሙ ውስተ ጽንፈ ማዩ ለዮርዳኖስ ቁሙ ውስቴቱ ። | ፰ | አሁንም ታቦቲቱን የሚሸከሙ ካህናትን ወደ ዮርዳኖስ ዳርቻ በገባችሁ ጊዜ በውስጡ ቁሙ ብለህ እዘዛቸው አለው ። ኢያ፡ ፫ ፫ ፡ ፫ ፲፯ ። |
| ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል ቅረቡ ዝየ ወስምዑ ቃለ እግዚአብሔር አምላክነ ። | ፱ | ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች ወደዚህ ቀርባችሁ የፈጣሪያችን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ አላቸው ። |
| ወይቤሎሙ ኢያሱ በዝንቱ ተአምሩ ከመ ሕያው ውእቱ እግዚአብሔር ዘምስሌክሙ ወአጥፍኦ ያጠፍኦሙ እምቅድመ ገጽክሙ ለከናኔዎን ወለኬጤዎን ወለፌርዜዎን ወለኤዌዎን ወለአሞሬዎን ወለኢያቡሴዎን ወለጌርጌሴዎን ። | ፲ | ኢያሱ ከናንተ ጋራ በረድኤት ጸንቶ የሚኖር እግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ በዚህ ታውቃላችሁ ኬጤዎንን ከናኔዎንን ፌርዜዎንን ኤዌዎንን ኢያቡሴዎንን አሞሬዎንንና ጌርጌሴዎንን ከፊታችሁ ፈጽሞ ያጠፋቸዋል ። |
| ወናሁ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እግዚአ ኵሉ ምድር ተዐዱ ቅድሜክሙ ዮርዳኖስ ። | ፲፩ | የዓለሙ ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትም እነሆ በፊታችሁ ዮርዳኖስን ትሻገራለች ። |
| ወኅረዩ ለክሙ ዐሠርተ ወክልኤተ አደወ እምደቂቀ እስራኤል አሐደ አሐደ ብእሴ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ ። | ፲፪ | ከእስራኤል ልጆች ከአንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ሰው ዓሥራ ሁለት ሰዎች ምረጡ አላቸው ። ዘኍ፡ ፲፫ ፪ ። |
| ወሰበ አቀሙ እገሪሆሙ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ ማየ ዮርዳኖስ ይነጽፍ ማየ ዮርዳኖስ ወማይኒ ዘይወርድ እምላዕሉ ይቀውም ። | ፲፫ | የእግዚአብሔር ሕግ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ እግራቸውን ውኃ መካከል ባቆሙ ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ይደርቃል ፡ ከላይ የሚወርደውም ውኃ ይቆማል አላቸው ። ዘፀ፡ ፲፭ ፲፰ ፡ ኢያ፡ ፫ ፲፭ ። |
| ወእምዝ ሰበ ግዕዙ ሕዝብ እማኅደሪሆሙ ከመ ይዕድዉ ለዮርዳኖስ ወካህናትኒ ያሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወሖሩ ቅድመ ሕዝብ ። | ፲፬ | ከዚህ በኋላ ዮርዳኖስን ይሻገሩት ዘንድ በተጓዙ ጊዜ ካህናቱም የእግዚአብሔር የሕጉን ማደሪያ ታቦትን ተሸክመው በሄዱ ጊዜ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፯ ፵፭ ። |
| ወሰበ በኡ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ ዮርዳኖስ ወተጠምቃ እገሪሆሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕግ ውስተ ጽንፉ ለዮርዳኖስ ወምሉእ ውእቱ ዮርዳኖስ እስከ ድንጋጌሁ ከመ መዋዕለ ክረምት ወከመ አመ ይሠዊ ሥርናይ ። | ፲፭ | የእግዚአብሔር የሕጉን ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ካህናት ወደ ዮርዳኖስ በገቡ ጊዜ የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ የካህናቱ እግሮቻቸውም በተጠመቁ ጊዜ ዮርዳኖስ እንደ ክረምት ወራት ሥንዴም እንደ ሚሸት በት ወራት እስከ ዳርቻው ድረስ መልቶ ነበር ። |

፲፮ ወቆመ ማይ ዘይወርድ እምላዕሉ ወቆመ ከመ አረፍት እንዘ ይርኅቅ ቀዊመ ጥቀ እስከ ደወለ ቀርያታርም ወዘይወርድ ወረደ ውስተ ባሕር ወእስከ ባሕረ ኤሎን ነጽፈ ወየብሰ ወቆሙ ሕዝብ አንጻረ ኢያሪክ ።

፲፯ ወክህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ቆሙ ውስተ ይቡስ ማእከለ ዮርዳኖስ ርሡያኒሆሙ ወኵሉ ደቂቀ እስራኤል ዐደዉ እንተ ማእከለ የብስ እስከ ተገምሩ ኵሉ ሕዝብ ወዐደዉ ዮርዳኖስ ።

ምዕራፍ ፬ ።

፩ ወሶበ ተገምሩ ኵሉ ሕዝብ ወዐደዉ ዮርዳኖስ ይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ንሣእ ዐሠርተ ወክልኤተ እደወ አሐደ አሐደ ብእሲ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ ።

፪ ወአዝዞሙ ከመ ይንሥኡ ሎሙ እምዝየ እማእከለ ዮርዳኖስ እምኀበ ቆሙ እገሪሆሙ ለክህናት ዐሠርተ ወክልኤተ አእባነ ክዋቀተ ወንሥእዎን ምስሌክሙ ወዕቀብዎን በበነገድክሙ ኀበ ኀደርክሙ ህየ በሌሊት ።

፫ ወጸውዐ ኢያሱ ዐሠርተ ወክልኤተ እደወ እምክቡራኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፣ አሐደ አሐደ ብእሴ እምአሐዱ አሐዱ ነገድ ።

፬ ወይቤሎሙ ንዑ ወእምጽኡ ቅድሜየ ወቅድመ እግዚአብሔር እማእከለ ዮርዳኖስ ወንሥኡ እምዝየ አሐተ አሐተ እብነ ።

፭ ወፁሩ ውስተ መታክፍቲክሙ በከመ ኍለቊሆሙ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ ነገደ እስራኤል ፣ ከመ ይኩኑክሙ ተአምረ ወይንበሩክሙ ለዝሉፉ ።

፮ ከመ ሶበ ተስእለከ ወልድከ ጌሠመ ወይቤለከ ምንት እማንቱ እላንቱ አእባን ፣ ንግሮ አንተ ለወልድከ ወበሎ ፣ እስመ ነጽፈ ዮርዳኖስ ተከዚ እምቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንዘ ነዐዱ ።

፯ ወይኩናክሙ እላንቱ አእባን ተዝካረ ለክሙ ለደቂቀ እስራኤል እስከ ለዓለም ።

፰ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ኢያሱ ወነሥኡ ዐሠርተ ወክልኤተ አእባነ እማእከለ ዮርዳኖስ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወሶበ ተገምሩ ዐዲወ ደቂቀ እስራኤል ተዐቀብዎን ምስሌሆሙ ውስተ ተዓይኒሆሙ ወሤምዎን በህየ ።

፱ ወአቀመ በህየ ኢያሱ ካልአተ አእባነ ዐሠርተ ወክልኤተ ውስተ ዮርዳኖስ ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ቆማ እገሪሆሙ ለክህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕግ ወሀለዋ ህየ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ።

፲ ወቆሙ ክህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕግ ማእከለ ዮርዳኖስ እስከ ፈጸመ ኢያሱ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር ከመ ይንግሮሙ ለሕዝብ ወአፍጠኑ ዐዲወ ሕዝብ ።

፲፩ ወሶበ ተገምሩ ዐዲወ ሕዝብ ዐደወት ታቦተ ሕግሂ ወእልክቱሂ አእባን እለ ቅድሜሆሙ ።

፲፪ ወዐደዉ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ርሡያኒሆሙ ቅድመ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ሙሴ ።

ከላይ የሚወርደው ውኃ እስከ ቀርያታርም አውራጃ ድረስ ርቆ እንደ ግድግዳ ቆመ ፣ የሚወርደውም ውኃ ወደ ባሕር ወረደ ፣ እስከ ባሕረ ጼውም ድረስ ፈጽሞ ደረቀ ፣ ሕዝቡም በኢያሪኮ አንጻር ቆሙ ። ፩ ነገ፡ ፬ ፲፱ ።

የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ክህናትም አጊጠው በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ ቆሙ ፣ ሕዝቡም ሁሉ አክተው እስኪሻገሩ ድረስ ደርሰው የእስራኤል ልጆች ሁሉ በደረቅ ተሻገሩ ዮርዳኖስንም ተሻገሩ።

ምዕራፍ ፬ ።

ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ፈጽመው በተሻገሩ ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ ከነዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው መርጠህ ዓሥራ ሁለት ሰዎች አቅርብ ።

የካህናቱ እግሮች ከቆሙበት ከዚያ ከዮርዳኖስ እንክብል እንክብል የሆኑ ደንጊያዎችን ለነሳቸው ያመጡ ዘንድ እዘዛቸው ፣ ከናንተም ጋር ይዛችኋቸው ሂዱ ፣ ሌሊት በደራችሁበት በዚያ በየነገዳችሁ ጠብቋቸው ።

ኢያሱም ከእስራኤል ልጆች ሹማምንት ከነዳንድ ነገድ አንዳንድ ሰው መርጦ ዓሥራ ሁለት ሰዎችን ጠራ ። ዘኍ፡ ፲፫ ፪ ። ዘዳ፡ ፩ ፳፫ ።

ከዚህ ከዮርዳስ መካከል አንዳንድ ደንጊያ አንሥታችሁ ወደ እግዚአብሔርና ወደኔ አምጡ ። ኢያ፡ ፩ ፬ ፣ ፲፭ ። ፩ ነገ፡ ፲፰ ፴፩ ።

ምልክት ይሆናችሁ ዘንድ ለዘለዓለሙም ይኖሩላችሁ ዘንድ በዓሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቍጥር በጫንቃችሁ ተሸከሙ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፳፮ ፣ ኢያ፡ ፬ ፳፩ ።

ልጅህ ነገ እነዚህ ደንጊያዎች ምንድር ናቸው ፤ ብሎ ቢጠይቅህ ፡ ስንሻገር የዮርዳኖስ ፈሳሽ ከእግዚአብሔር ከሕጉ ማደሪያ ከታቦት ፊት ደርቋልና ስለዚህ ነው ብለህ አንተ ለልጅህ ንገረው ።

እነዚያም ደንጊያዎች ለናንተ ለእስራኤል ልጆች እስከ ዘለዓለም መታሰቢያ ይሁኑዋችሁ አላቸው ።

የእስራኤልም ልጆች ኢያሱ እንዳዘዛቸው እንዲሁ አደረጉ ፣ የእስራኤል ልጆች አክተው በተሻገሩ ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዳዘዘው ከዮርዳኖስ መካከል ዓሥራ ሁለት ደንጊያዎችን አመጡ ፣ ከነሱም ጋር በሰፈራቸው ጠበቋቸው በዚያም አኖሩዋቸው ።

ኢያሱም የሕጉን ታቦት የሚሸከሙ የካህናቱ እግሮች በቆሙበት በዚያ በዮርዳኖስ መካከል ሌሎች ዓሥራ ሁለት ደንጊያዎችን አቆመ ፤ እስካሁንም ድረስ እስከዚህችም ቀን በዚያ አሉ ።

የሕጉን ታቦት የተሸከሙ ካህናትም ኢያሱ ለሕዝቡ ይነግራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘውን እስኪጨርስ ድረስ በዮርዳኖስ መካከል ቆመው ነበር ሕዝቡም ፈጥነው ተሻገሩ።

ሕዝቡም አክተው በተሻገሩ ጊዜ የሕጉም ታቦት ተሻገረች በፊታቸው ያሉ እኒያ ደንጊያዎችም ተሻገሩ ።

የጋድና የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም እኩሌቶች ተሰልፈው ሙሴ እንዳዘዛቸው በእስራኤል ልጆች ፊት ተሻገሩ ። ዘዐ፡ ፲፫ ፲፰ ፣ ኢያ፡ ፩ ፲፬ ።

፲፫ አርባዕ ምእት ቅኑታኒሆሙ ለቀትል በዩዉ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ይትቃተልዋ ለኢያሪኮ ሀገር ።

፲፬ ወበይእቲ ዕለት አዕበዮ እግዚአብሔር ለኢያሱ በቅድመ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወፈርህዎ ከመ ሙሴ እምጣነ ሕያው ውእቱ ።

፲፭ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ፣ እዝዞሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ከመ ይዕኡ እማእከለ ዮርዳኖስ ።

፲፮ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለካህናት ወይቤሎሙ ዕኡ እምዮርዳኖስ ።

፲፯ ወኮነ ሶበ ወፅኡ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እማእከለ ዮርዳኖስ ወኬዱ በእገሪሆሙ ውስተ ምድር ሮጸ ማየ ዮርዳኖስ ወገብአ ውስተ መከናቲሁ ወሖረ ከመ ትካት ወበጽሐ እስከ ድንጋጌሁ ።

፲፰ ወእመ ፀሡሩ ለሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ ወፅኡ ሕዝብ እምዮርዳኖስ ወግዕዙ ውስተ ገልገላ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ እምኢያሪኮ ።

፲፱ ወአቀሞን ኢያሱ ለእማንቱ አእባን ዐሠርቱ ወክልኤቱ ውስተ ገልገላ ።

፳ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል ሶበ ተስእሉክሙ ደቂቅክሙ ወይቤሉክሙ ምንትኑ እላንቱ አእባን፣ ዜንውዎሙ ለደቂቅክሙ ወበልዎሙ እስመ ከመ የብስ ዐደውናሁ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ።

፳፩ እስመ አይበሳ እግዚአብሔር ለማየ ዮርዳኖስ ቅድሜነ እስከ ነዐዱ ።

፳፪ በከመ ገብራ እግዚአብሔር ለባሕረ ኤርትራ እንተ አይበሳ እግዚአብሔር አምላክነ እምቅድሜነ እስከ ኅለፍነ፣ ከመ ያአምሩ ኵሉ አሕዛበ ምድር ከመ ጽኑዕ ውእቱ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ወከመ ትፍርህዎ አንትሙኒ ለእግዚአብሔር አምላክነ በኵሉ ግብሩ ።

## ምዕራፍ ፭ ።

፩ ወእምዝ ሶበ ሰምዑ ኵሉ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ ዮርዳኖስ መንገለ ባሕር ወኵሉ ነገሥተ ፊንቂስ እለ መንገለ ባሕር ከመ አይበሳ እግዚአብሔር ለተከዜ ዮርዳኖስ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል ተመስወ ልበሙ ወተጠስየ ወኑኖኡ ዘይሐልዩ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፪ ወእምድኅረ እማንቱ መዋዕል ይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ግበር ለከ መጣብሐ ዘእብን እምእብነ እዝኅ ወንበር ወግዝሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ዳግመ ።

፫ ወገብረ ሎቱ ኢያሱ መጣብሐ ዘእብነ እዝኅ ወገዘሮሙ ለደቂቀ እስራኤል በውስተ መከን ዘስሙ ወግረ ቍልፈት ።

፬ ወበበይነ ዝንቱ ገዘሮሙ ኢያሱ ለኵሉ ሕዝብ እለ ወፅኡ እምግብጽ ኵሉ ተባዕቶሙ ወኵሉ ሕዝብ እደው

ለሰልፍ አሩቸውን ታጥቀው የኢያሪኮን አገር ያጠፉት ዘንድ አርባ መቶ ሰዎች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ተሻገሩ ። ዘኍ ፴፪ ፳፯፣ ኢያ፣ ፩ ፲ ።

በያዚችም ቀን እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤል ልጆች ሁሉ ፊት አከበረው፣ ከፍ ከፍ አደረገው፣ እሱ በሕይወት በኖረበት ዘመን ሁሉ ሙሴን ይፈሩት እንደነበረ ፈሩት ። ኢያ፣ ፫ ፯ ።

እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ ታቦትን የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል ይወጡ ዘንድ እዘዛቸው ። ዘፀ፣ ፳፫ ፲፯ ።

ኢያሱም ካህናቱን ከዮርዳኖስ ውጡ ብሎ አዘዛቸው። ዘፀ፣ ፳፭ ፲፯ ። ራእ፣ ዮሐ፣ ፲፩ ፲፱ ።

የእግዚአብሔር የሕጉን ማደሪያ ታቦትን የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል በወጡ ጊዜ እግሮቻቸውም የብሱን በረገጡ ጊዜ እንዲህ ሆነ የዮርዳኖስ ውኃ ፈጥኖ ወደ ቦታው ተመለሰ፣ እንደ ቀድሞውም ሄዶ እስከ ዳርቻው ደረሰ ። ኢያ፣ ፫ ፯፣ ፫ ፲፭ ።

ሚያዝያ በባተ በዓሥረኛው ቀን ሕዝቡ ከዮርዳኖስ ወጡ፣ ከኢያሪኮም ወደ ፀሐይ መውጫ ወደ ገልገላ ተጓዙ። ፩ ሳሙ፣ ፲፩ ፲፬ - ፲፭ ።

ኢያሱም እነዚያን ዓሥራ ሁለቱን ድንጊያዎች በገልገላ አቆማቸው ። ኢያ፣ ፬ ፱ ።

ኢያሱ የእስራኤል ልጆች እንዲህ አላቸው ፤ ልጆቻችሁ እነዚህ ድንጊያዎች ምንድር ናቸው ብለው በጠየቋችሁ ጊዜ፤ ይህን ዮርዳኖስን እንደ ደረቅ (ምድር) ተሻግረነዋልና ስለዚህ ነው ብላችሁ ለልጆቻችሁ ንገሩዋቸው ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እስክናልፍ ድረስ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቃት ይህችን ዮርዳኖስንም እስክንሻገር ድረስ ከፊታችን አድርቋታልና ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እስክንሻገር ድረስ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቃት በምድር ያሉ አሕዛብ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ጽኑ እንደሆነ ያውቁ ዘንድ እናንተም ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን በሥራው ሁሉ ትፈሩት ዘንድ ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻግረነዋልና ስለዚህ ነው።

## ምዕራፍ ፭ ።

ከዚህ በኋላ በባሕር አንጻር የሚኖሩ የፊንቂስ ነገሥታት ሁሉና ከዮርዳኖስ ማዶ በባሕር አንጻር የሚኖሩ የአሞሬዎን ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔር ከእስራኤል ልጆች ፊት የዮርዳኖስን ፈሳሽ እንዳደረቃት በሰሙ ጊዜ ልቡናቸው እንደ ሰም ቀለጠ፣ ጠፋም፣ በእስራኤልም ልጆች ፊት አስበው የሚናገሩትን አጡ ። ዘፀ፣ ፲፭ ፲፬ ።

ከነዚያ ወራቶችም በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን ከቡልጭት ድንጋይ የድንጋይ ሻፎ ሥራ፣ ተቀምጠህም የእስራኤልን ልጆች ዳግመኛ ግረዛቸው አለው ። ዘፀ፣ ፬ ፳፭ ።

ኢያሱም የድንጋይ ቡልጭት ሻፎን ሠርቶ የግርዛት ኮረብታ በሚባለው ቦታ የእስራኤልን ልጆች ገረዛቸው ።

ስለዚህም ከግብጽ የወጡት ወንዶች ሁሉ ከግብጽ ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ ጕዳና የሞቱም አርበኞች

መስተቃትላን እለ ሞቱ በገዳም በፍኖት ወፂአሙ እምግብጽ ከኑ ግዙራነ ።
፭ ወኵሉ ሕዝብ እለ ተወልዱ በፍኖት በገዳም ወፂአሙ እምድረ ግብጽ እስመ እሙንቱ ኢኮኑ ግዙራነ ።
፮ እስመ አርብዐ ዓመተ ሖዱ እስራኤል ውስተ ገዳም ዘመድበራ እስከ ተፈጸመ ኵሉ ሕዝብ መስተቃትላን እለ ወፅኡ እምድረ ግብጽ እለ ክሕዱ ትእዛዘ እግዚአብሔር ።
፯ ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ከመ ኢይርአይዋ ለይእቲ ምድር ዘመሐለ እግዚአብሔር ለአበዊነ ከመ የሀበነ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ ወመዓረ ።
፰ ወህየንተ ዚአሆሙ አቀመ ውሉዶሙ ዘገዘሮሙ ኢያሱ እስመ ኢኮኑ ግዙራነ እስመ በፍኖት ተወልዱ ወኢተገዝሩ ።
፱ ወእመ ተገዝሩ ነበሩ ትዕይንት ወወዓሉ እስከ የሐይዉ ።
፲ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ ዮም በዛቲ ዕለት አውፃእኩ ትዕይርቶሙ ለግብጽ እምኔክሙ ወሰመየ ስሞ ለውእቱ መከን ገልገላ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ።
፲፩ ወኀደሩ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ገልገላ ወገብሩ ፋሲካ አመ ፀሡር ወረቡዑ ለሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ በሠርክ በዐረቢሃ ለኢያሪኮ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በውስተ ገዳም ወበልዑ እምእክለ ምድር ናእተ ሐዲሰ ።
፲፪ ወበይእቲ ዕለት ኀልቀ መና በሳኒታ እምዘበልዑ እክለ ምድር ወኢረከቡ እንከ መና ደቂቀ እስራኤል ዳግመ እስመ አረሩ ብሔረ ፊንቆን በውእቱ ዓመት ።
፲፫ ወከነ እንዘ ሀለወ ኢያሱ ውስተ ኢያሪኮ ነጸረ በአዕይንቲሁ ወርእየ ብእሴ ይቀውም ቅድሜሁ ወሰይፍ ምሉሕ ውስተ እዴሁ ወቀርበ ኢያሱ ወይቤሎ እምሰብእ ዚአነኑ አንተ አው እምፀርነ ።
፲፬ ወይቤሎ አንሰ መልአከ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ወይእዜ በጻሕኩ ።
፲፭ ወወድቀ ኢያሱ በገጹ ወሰገደ ሎቱ ውስተ ምድር ወይቤሎ ምንት አቀመከ ኀበ ገብርከ ።
፲፮ ወይቤሎ መልአከ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ለኢያሱ ፍታሕ አሣእኒከ እምእገሪከ እስመ መከን ኀበ ትቀውም ምድር ቅድስት ይእቲ፣ ወገብረ ኢያሱ ከማሁ ።

ምዕራፍ ፮ ።

፩ ወኢያሪኮሰ ዕፁት ይእቲ ወጥቅም ላዕሌሃ ወአልቦ ዘይወፅእ እምውስቴታ ወአልቦ ዘይበውእ ኀቤሃ ።
፪ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ አገብአ ለኢያሪኮ ውስተ እደዊከሙ ወለንጉሥ ዘውስቴታ ወእለ ጽኑዓን እሙንቱ ወኃያላን ።

ሁሉ ተገርዘው ነበርና ። ዘኁ፡ ፲፬ ፳፱፣ ፳፮ ፷፬ ።
ዘዳ፡ ፩ ፫ ። ዕብ፡ ፫ ፲፩ ።

ከግብጽም ምድር ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ ጕዳና የተወለዱት ሕዝቡ ሁሉ እነሳቸው አልተገረዙም ነበርና ስለዚህ ነው ። ዘፀ፡ ፲፬ ፳፱፣ ዘዳ፡ ፪ ፲፮ ።

ከግብጽ የወጡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የካዱ አርበኞች ሰዎች ሁሉ እስኪጠፉ ድረስ መድበራ በሚባል ምድረ በዳ አርባ ዘመን ስለ ዞሩ ።

ተድላ ደስታ የሚገኝበትን አገር ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር ላባቶቻችን የማለላቸውን ያችን አገር እንዳያዩዋት እግዚአብሔር ነገራቸው ። ዘፀ፡ ፫ ፰፣ ዘኁ፡ ፲፬ ፴፫ ።

በመንገድ ተወልደው አልተገረዙም ነበርና፣ ኢያሱ የገረዛቸው ልጆቻቸውን ስለነሱ ፈንታ ተከ ።
ዘፍ፡ ፴፬ ፳፭ ። ሌዋ፡ ፲፰ ፫ ። ፩ ሳሙ፡ ፲፬ ፮ ።

እነዚህም በተገረዙ ጊዜ እስኪድኑ ድረስ ሠራዊቱ ሰፈር አድርገው ዋሉ ። ዘፍ፡ ፴፬ ፳፭ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ እነሆ ዛሬ በዚህች ቀን የግብጻውያንን ተግዳሮት ከናንተ አራቅሁላችሁ አለው፣ ኢያሱም የዚያን ቦታ ስም ገልገላ አለው፣ እስከዛሬ እስከዚችም ቀን ገልገላ ይባላል ።

የእስራኤልም ልጆች በገልገላ አደሩ፣ መጀመርያ ወር የሚሆን ሚያዝያ በባተ በሥራ አራተኛው ቀን በኢያሪኮ ምዕራብ በዮርዳኖስ ማዶ በምድረ በዳው በሠርክ ፋሲካን (በዓል) አደረጉ፣ ከምድሪቱም የተገኘውን አዲሱን እኽል ቂጣ አድርገው በሉ ። ዘፀ፡ ፲፪ ፮፣ ኢያ፡ ፭ ፰ ።

የዚያን አገር እኽል ከበሉ በኋላ በማግሥቱ በዚያች ቀን መናው ቀረ (ቆመ)፣ በዚያው ዓመት የፊንቆንን አዝመራ ዘርፈዋልና (በልተዋልና) ዳግመኛ የእስራኤል ልጆች መና አላገኙም ። ዘፀ፡ ፲፮ ፴፭ ።

ኢያሱም በኢያሪኮ ሳለ በእጁ የተመዘዘ ሰይፍን የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ በዓይኖቹ አይቶ፣ ኢያሱ ቀርቦ ከኛ ሰዎች ወገን ነህን፤ ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ፤ አለው ።
ዘኁ፡ ፩ ፳፫ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፩ ፲ ።

እኔስ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጥበት መልአክ ነኝ አሁንም ወዳንተ መጥቻለሁ አለው ።

ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደለት፣ በኔ በባሪያህ ዘንድ ምን አቁሞኻል፤ አለው ።

የእግዚአብሔር የሠራዊቱም አለቃ ኢያሱን የቆምክ በት ምድር የከበረች ምድር ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው፣ ኢያሱም እንዳለው አደረገ ።

ምዕራፍ ፮ ።

ኢያሪኮ ግን ተዘግታ ነበር ቅጥርም ነበራት፣ ከሷ የሚወጣ ወደሷም የሚገባ አልነበረም ።

እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ በውስጧ ያለውን ንጉሧን ከኃያላኑና ከአርበኞቹ ጋር በእጃችሁ እጥላታለሁ ። ዘዳ፡ ፯ ፳፬፣ ኢያ፡ ፪ ፳፬ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወአንተሰ አቅሞሙ ለዕሴሃ ውስተ ዐውዳ ለኵሎሙ መስተቃትላን ወይዑድዋ ለሀገር ኵሎሙ እደው መስተቃትላን ውስተ ዐውዳ ለይእቲ ሀገር በበምዕር ወከማሁ ግበሩ ሰዱሰ መዋዕለ። | ፫ | አንተ ግን በኢያሪኮ በዙርያዋ ኃያላኑን አቁማቸው፤ ኃያላኑ ሰዎች ሁሉ በዚያች አገር ዙርያ አገሪቱን አንድ አንድ ጊዜ ይዙርዋት እንደዚሁም ስድስት ቀን አድርጉ። ነሀ፡ ፱ ፳፬። ዳን፡ ፭ ፲፰ - ፲፱። |
| ወሰብዓቱ ካህናት ይንሥኡ ሰብዓተ አቅርንተ ዘኢዮቤል ቅድመ ታቦት፤ ወአመ ሳብዕት ዕለት ሰብዐ ይዑድዋ ለሀገር ወይንፍሑ ካህናት በእሙንቱ አቅርንት። | ፬ | ሰባቱም ካህናት በታቦት ፊት በኢዮቤል የሚነፋ ሰባት ቀንደ መለኸት ይያዙ፤ በሰባተኛይቱ ቀን ግን አገሪቱን ሰባት ጊዜ ይዙርዋት ካህናቱም ቀንደ መለኸቱን ይንፉ። |
| ወሶበ ነፍሑ በእሙንቱ አቅርንት ዘኢዮቤል እምከመ ሰማዕክሙ ቃለ ቀርን ለይወውዑ ኵሎሙ አሕዛብ ኅቡረ፤ ወእምከመ ወውዑ እሙንቱ ይወድቅ ለሊሁ አረፋቲሃ ለሀገር ታሕቲሆሙ ወይበእ እንከ ኵሉ ሕዝብ ወይሩጽ አሐዱ አሐዱ ቅድመ ገጹ ውስተ ሀገር። | ፭ | በአርበ ዘጠኝ ዘመን የሚነፋ እነዚያን ቀንደ መለኸት በነፉ ጊዜ የቀንደ መለኸቱን ድምፅ ከሰማችሁ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ አንድነት ይደንፉ፤ እነዚያም ከደነፉ በኋላ የአገሪቱ ቅጽር በበታቻቸው ይወድቃል፤ ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ ይግባ፤ አንዱም አንዱም በፊቱ ወደ አገሪቱ ይሩጥ አለው። ዘፀ፡ ፲፱ ፲፫፤ መሳ፡ ፯ ፴፮። |
| ወፀውዖሙ ኢያሱ ለካህናት ወይቤሎሙ ንሥኡ ታቦተ ሕግ ወሰብዐቱ ካህናት ይንሥኡ ሰብዓተ መጣቅዕተ ዘኢዮቤል በቅድመ እግዚአብሔር። | ፮ | ኢያሱም ካህናቱን ጠርቶ የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ይያዙ ሰባቱም ካህናት በአርበ ዘጠኝ ዘመን የሚነፋ ሰባቱን ቀንደ መለኸት በእግዚአብሔር ፊት ይያዙ አላቸው። |
| ወይቤሎሙ አዝዝዎሙ ለሕዝብ ከመ ይሑሩ ወይዑድዋ ለሀገር ወመስተቃትላንሂ ይሑሩ ምስለ ንዋየ ሐቅሎሙ ቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። | ፯ | ሕዝቡም ሂደው አገሪቱን ይከቧት ዘንድ እዘዟቸው አርበኞቹም ከሚጓዝ ጸብታቸው ጋራ በእግዚአብሔር ሕግ ማደሪያ ታቦት ፊት ይሄዱ ዘንድ እዘዙዋቸው አላቸው። |
| ወነሥኡ ሰብዐቱ ካህናት ሰብዓተ መጣቅዕት ቅዱሳነ በከመ ይቤሎሙ ኢያሱ ከመ ይሑሩ ቅድመ እግዚአብሔር ወሐዊሮሙ ይጠቅዑ በኃይል ወበትእምርት ወታቦተ ሕጉሂ ለእግዚአብሔር ትተልዎሙ። | ፰ | ኢያሱም በእግዚአብሔር ፊት ይሄዱ ዘንድ እንደ ነገራቸው ሰባቱ ካህናት ልዩ የሆኑ ሰባቱን ቀንደ መለኸት ይዘው ሄዱ፤ በሄዱም ጊዜ አሰምተው ምልክት አይተው ይምቱ፤ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትም ትከተላቸዋለች። ኢያ፡ ፬ ፲፫። |
| ወመስተቃትላንሰ ፍጽመ የሐውሩ ወካህናትኒ ይጠቅዑ በመጣቅዕት ወእለሂ ይትኬወሉ ድኅረ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር የሐውሩ እንዘ ይነፍሑ ቀርነ። | ፱ | አርበኞች ግን በፊት ይሄዱ ነበር፤ ካህናቱም ነጋሪቱን ይመቱ ነበር፤ ከእግዚአብሔር ከሕጉ ማደሪያ ከታቦት በኋላ የነበሩትም ቀንደ መለኸት እየመቱ ይሄዱ ነበር። |
| ወአዘዞሙ ኢያሱ ለሕዝብ ከመ ኢይወውዑ ወአልበ ዘይሰምዕ ቃሎሙ መኑሂ ከመ ኢይፃእ ቃል እምአፉሆሙ እስከ አመ ውእቱ ይኤዝዞሙ ከመ ይወውዑ። | ፲ | ኢያሱም ሕዝቡ ግርግር እንዳይሉ አዘዛቸው፤ ከአፋቸውም ቃል እንዳይወጣ ይደነፉም ዘንድ እሱ እስኪያዛቸው ድረስ ማንም ማን ቃላቸውን የሚሰማ እንዳይኖር አዘዛቸው። |
| ወሖረት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወዖደታ ለሀገር ወእምዝ ገብአት ውስተ ትዕይንት ወቤተት ህየ። | ፲፩ | የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትም ሄዳ አገሪቱን ዞረቻት፤ ከዚህ በኋላ ወደ ሰፈር ተመልሳ በዚያ አደረች። |
| ወበሳኒታ ዕለት ተንሥአ ኢያሱ በጽባሕ ወካህናትኒ ፆሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር። | ፲፪ | በማግሥቱም ሲነጋ ኢያሱ ተነሣ፤ ካህናቱም የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸከሙ። |
| ወሰብዐቱ ካህናት ነሥኡ ሰብዓተ መጣቅዕተ ቅዱሳነ ወሐሩ ቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወይተልዉ መስተቃትላን ወእምዝ ይተልዉ እለ ተርፉ ሕዝብ ወየሐውሩ ድኅረ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነፍኁ በአቅርንት ወካህናትኒ ይጠቅዑ በመጣቅዕት። | ፲፫ | ሰባቱም ካህናት ልዩ የሆኑ ሰባቱ ቀንደ መለኸት ይዘው በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ታቦት ፊት ይሄዱ ነበር አርበኞቹም ይከተሉ ነበር፤ ከዚህ በኋላ የቀሩት ወገኖች ቀንደ መለኸቱን እየነፉ በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ታቦት በኋላ ይሄዱ ነበር፤ ካህናቱም ቀንደ መለኸቱን ይመቱ ነበር። ፩ ዜና መዋ፡ ፲፭ ፳፮። |
| ወኵሉ ሕዝብ ዘተርፉ ዖድዋ ለሀገር አሐደ ጊዜ አመ ሳኒታ ዕለት እንዘ ይቀርብዋ ወእምዝ ከዐቡ ገብኡ ውስተ ትዕይንት ወከመዝ ገብሩ ሰዱሰ መዋዕለ። | ፲፬ | የቀሩት ሕዝቡ ሁሉ በማግሥቱ ቀርበው አገሪቱን አንድ ጊዜ ዞሯት ከዚህ በኋላ ዳግመኛ ወደ ሰፈር ተመለሱ ስድስትም ቀን እንዲህ አደረጉ። |
| ወኮነ አመ ሳብዕት ዕለት ተንሥኡ ጊዜ ይገውሕ ጽባሕ ወዖድዋ ከማሁ ለሀገር ሰብዐ ወዳእሙ በይእቲ ዕለት ዖድዋ ሰብዐ ለሀገር። | ፲፭ | በሰባተኛውም ቀን እንዲህ ሆነ፤ ጎሕ በቀደደ ጊዜ አገሪቱን እንደዚሁ ሰባት ጊዜ ዞሯት፤ በዚያች ቀን ብቻ አገሪቱን ሰባት ጊዜ ዞሯት። |
| ወሶበ ስዘ ዖድዋ ሰብዐ ለሀገር ጠቅዑ ካህናት በመጣ | ፲፮ | አገሪቱን ሰባት ጊዜ በዞሯት ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ ካህናቱ |

ቅዕቲሆሙ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል ወውዑ እስመ አግብአ እግዚአብሔር ለነ ።

፲፯ ወአሕረምናሃ ለዛቲ ሀገር ወኵሉ ዘውስቴታ ይኩን ለእግዚአብሔር ጸባኦት ዘእንበለ ራዓብ ዘማ እንተ ታሐይዉ ኪያሃ ወኵሎ ዘሀለወ ውስተ ቤታ እስመ ኀብአቶሙ ለሰብአ ዐይን እለ ፈነውነ ።

፲፰ ወአንትሙሰ ዑቁ ኢትንሥኡ እምዘሐረም ዘአሕረምነ ወኢትፍትዉ ወኢትንሥኡ እምኔሁ ወኢመአኮ ትገብርዋ ርግምተ ለትዕይንት ወትቀጠቅጡነ ።

፲፱ ወኵሉ ወርቅ ወብሩር ወብርት ወሐፂን ቅዱሰ ይኩን ለእግዚአብሔር ወውስተ መዝገቡ ይባእ ።

፳ ወወውዑ ሕዝብ ወካህናትኒ ጠቅዑ በመጣቅዕቲሆሙ ወነበረ ወወውዑ ሕዝብ በዐቢይ ውውዓ ወጽንዐ ወወድቀ ኵሉ ዓረፋቲሃ ዘዐውዳ ወቦኡ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ሀገር ወኵሎሙ ርቱዐ ውስተ ሀገር ቅድሜሆሙ ወረከብዋ ለሀገር ።

፳፩ ወአሕረማ ኢያሱ ወኵሎ ዘሀለወ ውስቴታ ለይእቲ ሀገር እምተባዕት እስከ አንስት እምንኡሶሙ እስከ ልሂቆሙ ወእስከ ላሕም ወበግዕ ወእስከ አድግ ቀተሎ በሐፂን ።

፳፪ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለእልክቱ ክልኤቱ ወራዙት ሰብአ ዐይን እለ ርእይዋ ለብሔር ሑሩ ውስተ ቤታ ለእንታክቲ ብእሲት ዘማ ወአውፅእዋ እምህየ ወኵሎ ዘሀለወ ምስሌሃ በከመ መሐልክሙ ላቲ ።

፳፫ ወቦኡ እልክቱ ክልኤቱ ወራዙት ሰብአ ዐይን እለ ርእይዋ ለይእቲ ሀገር ውስተ ቤተ ራዓብ ዘማ ወአውፅእዋ ወለአቡሃ ወለእማ ወለአኀዊሃ ወለኵሉ ዘመዳ ወኵሎ ዘባቲ ወአብጽሕዋ እስከ አፍአ ውስተ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል ።

፳፬ ወውዕየት ሀገር ምስለ ኵሉ ዘውስቴታ በእሳት ዘእንበለ ወርቅ ወብሩር ወኵሉ ብርት ወሐፂን ዘአብኡ ውስተ ዘአብኡ መዘግብተ ቤተ እግዚአብሔር ።

፳፭ ወራዓብ ዘማ ወኵሉ ቤተ አቡሃ ዘአሕየወ ኢያሱ ነበረት ውስተ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት እስመ ኀብአቶሙ ለሰብአ ዐይን እለ ፈነወ ኢያሱ ከመ ይርአይዋ ለሀገረ ኢያሪኮ ።

፳፮ ወአምሐለ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ወይቤ ርጉም ለይኩን ዘይነሥኣ ለዛቲ ሀገር፤ በበኵሩ ለይሣርራ፤ ወበደኃሪ ወልዱ ለያቅም ኖኀተ አንቀጺ ።

፳፯ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ኢያሱ ወበጽሐ ስሙ ውስተ ኵሉ ምድር ።

## ምዕራፍ ፯ ።

፩ ወአበሱ ደቂቀ እስራኤል ዐቢየ አበሳ ወነሥአ አካን ወልደ ከርሚ ወልደ ዘንበሪ ወልደ ዛራ ዘእምነገደ ይሁዳ እምዘአሕረሙ ወተምዐ እግዚአብሔር ላዕለ ደቂቀ እስራኤል ።

፪ ወፈነወ ኢያሱ አደወ ውስተ ጋይ እምኢያሪኮ እንተ መንገለ አዊን መንገለ ጽባሒሃ ለቤቴል ወይቤሎሙ ዕርጉ ወረአይዋ ለጋይ ወዐርጉ እሙንቱ አደው ወርአይዋ ለጋይ ።

ነጋሪታቸውን መቱ፤ ኢያሱም እግዚአብሔር በእጃችን ጥሎልናልና የእስራኤልን ልጆች ደንፉ አላቸው ።

ይህችንም አገር አጥፍተናታልና እነዚያን የላክናቸውን ጉብኝዎች ሠውራቸዋለችና በቤቷ ካለው ሰው ሁሉና እሷን ከምታድኑዋት ከራዓብ ዘማ በቀር በውስጧ ያለው ገንዘብ ሁሉ ለአሽናፊው ለእግዚአብሔር ይሁን ።

እናንተ ግን እርም ብለን ከተነውነው ገንዘብ እንዳትወስዱ ዕወቁ፤ ከዚህ ወዳችሁ አትውሰዱ፤ ብትወስዱ ግን ይህችን ወገን የተረገመች ታደርጓታላችሁ እኛንም ታጠፉናላችሁ ። ዘፍ፤ ፴፬ ፴፤ ኢያ፤ ፯ ፳፭ ።

ወርቁና ብሩ፤ ብረቱና ናሱ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን ወደ ዕቃ ቤቱም ይግባ ።

ሕዝቡም ደነፉ፤ ካህናቱም ነጋሪታቸውን መቱ፤ መገኖችም በብዙ በጽኑ ድንፋታ ደነፉ፤ በዙርያዋ ያለ ቅጥሯ ሁሉ ፈረሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ አገር ገቡ፤ ሁሉም ወደ ፊታቸው ሮጡ፤ አገሪቱንም እጅ አደረጓት ።

ኢያሱም አጠፋት፤ በዚያች አገር ያለውንም ሁሉ ከወንዱ እስከ ሴቱ፤ ከታናሹ እስከ ሽማግሌው፤ ከላሙ እስከ በጉ፤ እስከ አህያውም ድረስ በጦር አጠፋ ።

ኢያሱ አገሪቱን ያዩዋት እሊያን ሁለቱ ጐልማሶች ጉብኝዎች ወደዚያች ዘማ ሴት ሂዱ፤ ከዚያ አውጧት እንደ ማላችሁላት ከርሷ ጋር ያለውን ሁሉ አውጡ አላቸው ። ኢያ፤ ፪ ፲፬፤ ዕብ፤ ፲፩ ፴፩ ።

ያችን አገር ያዩዋት እነዚህ ሁለቱ ጐልማሶችም ወደ ራዓብ ዘማ ገብተው አወጧት፤ እናትና አባቷን ዘመዷን ሁሉና ወንድሞቿን ያላትን ሁሉ አወጧቸው ወደ እስራኤልም ሰፈር አደረሷት ። ኢያ፤ ፪ ፲፫ ።

ወደ ቤተ እግዚአብሔር ዕቃ ቤት ከገቡት ከወርቁና ከብሩ ከብረቱና ከናሱ ሁሉ በቀር አገሪቱ በእሳት ተቃጠለች ። ኢያ፤ ፯ ፲፱፤ ማቴ፤ ፩ ፭ ።

ራዓብ ዘማ ኢያሱ ከዳናቸው ከአባቷ ወገኖች ሁሉ ጋር የኢያሪኮን አገር ያዩዋት ዘንድ ኢያሱ የላካቸውን ጉብኝዎች ሠውራቸዋለችና እስከዚች ቀን ድረስ ከእስራኤል ልጆች ጋራ ኖረች ።

ኢያሱ በዚያች ቀን ይህችን አገር አቀናለሁ የሚል ሰው የተረገመ ይሁን፤ መሠረቷን ሲጀምር የበኩር ልጁ ይሙት፤ የደጃፏ በሯንም ሲያቆም ታናሽ ልጁ ይጥፋ ብሎ አማለ ። ዘኍ፤ ፩ ፳፩ ። ፩ ነገ፤ ፲፮ ፴፬ ።

እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋራ በረድኤት ኖረ፤ ስሙም በራቱ መዓዝነ ዓለም ደረሰ (ታወቀ) ። ኢያ፤ ፩ ፭፤ ፱ ፱ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

የእስራኤል ልጆች ብርቱ በደልን በደሉ፤ ከነገደ ይሁዳ የተወለደ የዛራ ልጅ የሚሆን የዘንበሪ ልጅ የከርሚ ልጅ አካን፤ እርም ከሉት ገንዘብ ወሰደ፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች ላይ ተቈጣ (ፈረደ) ። ኢያ፤ ፯ ፳፭ ።

ኢያሱ የቤቴል ምሥራቅ ከምትሆን በአዌን አጠገብ ካለች ከኢያሪኮ ወጥታችሁ ጋይን እዩዋት ብሎ ሰዎችን ላከ፤ እነዚያም ሰዎች ወጥተው ጋይን አዩዋት ።

፫ ወገብኡ ኀበ ኢያሱ ወይቤልዎ ኢይዕርግ ኵሉ ሕዝብ አላ ዕሥራ ምእት አው ሠላሳ ምእት አደው ይዕርጉ ወይትቃተልዋ ለይእቲ ሀገር ወኵሎ ሕዝበ እግዚአብሔር ኢትሰድ ህየ እስመ ውኁዳን እሙንቱ ።

ወደ ኢያሱም ተመልሰው ሁለት ሺሕ ወይም ሦስት ሺሕ ሰዎች ወጥተው ያችን አገር ይምቷት እንጂ ሕዝቡ ሁሉ አይውጡ ጥቂቶች ናቸውና የእግዚአብሔርን ሠኖች ግን ወደዚያ አትውሰድ አሉት ። ዘሌ፡ ፳፯ ፲፯ ።

፬ ወዐርጉ እምሕዝብ ዘየአክሉ ሠላሳ ምእት ወአንተዕዎሙ ሰብአ ጋይ ወጐዩ እምቅድመ ገጾሙ ።

ከሕዝቡም ሦስት ሺሕ ሰዎች ያህል ወጡ፥ በጋይ ያሉትም ሰዎች አበረሩዋቸው፥ ከፊታቸውም ሸሹ ።

፭ ወቀተሉ እምኔሆሙ በውስተ ጋይ ሠላሳ ወስድስተ አደወ፥ ወእምዝ ዴገንዎሙ እምኀበ አንቀጽ እስከ አጥፍእዎሙ ወቀተልዎሙ በውስተ ሙራድ ወደንገፀ ልበሙ ለሕዝብ፥ ወኮነ ከመ ማይ ።

ከነሱም በጋይ ሠላሳ ስድስት ሰዎች ገደሉ፥ ከዚህ በኋላ እስኪያጠፉዋቸው ድረስ ደርሰው ከአደባባዩ ጀምረው ተከተሏቸው፥ በቍልቍለቱም ገደሏቸው፥ የሕዝቡም ልቡና ደነገጠ፥ እንደ ውኃም ቀዘቀዘ ። ኢያ፡ ፲ ፲፩ ።

፮ ወሠጠጠ አልባሲሁ ኢያሱ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር ቅድመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር እስከ ሠርክ ውእቱ ወሊቃናቲሆሙ ለእስራኤል ወወደዩ መሬተ ውስተ ርእሶሙ ።

ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፥ በእግዚአብሔርም ማደሪያ በታቦት ፊት እስከ ሠርክ ድረስ እሱ ከእስራኤል አለቆች ጋራ በግንባሩ ወደ ምድር ወደቀ፥ በራሳቸውም ላይ ትቢያን ነሰነሱ ፤ ፩ ሳሙ፡ ፬ ፲፪፥ ፪ ሳሙ፡ ፩ ፲፩ ።

፯ ወይቤ ኢያሱ ገነይኩ ለከ እግዚኦ እግዚኦ! ለምንት አዕድዎ አዕደዎሙ ገብርከ ለእሉ ሕዝብ እምዮርዳኖስ ከመ ታግብኦሙ ውስተ እዴሆሙ ለአሞሬዎን ወከመ ያጥፍኡነ ሰበ ኀደርነ ወነበርነ ማዕዶተ ዮርዳኖስ እግዚኦ ።

ኢያሱ አቤቱ! አቤቱ! ተገዝሁልህ በአሞሬዎን እጅ ትጥላቸው ዘንድ ያጠፉንም ዘንድ እኔ አገልጋይህ እነዚህን ሰዎች ከዮርዳኖስ ለምን አሻገርኋቸው! እነዚህ ከሚያጠፉን በዮርዳኖስ ማዶ ብንኖር በተሻለን ነበር አለው።

፰ ወምንተ እንከ እብል ናሁ ሚጠ እስራኤል ዘባኖ ኀበ ፀሩ ።

እነሆ እስራኤል ጀርባውን ወደ ጠላቱ መለሰ እንግዲህ ወዲህ ምን እላለሁ፤ አለ ። ዘፀ፡ ፴፫ ፳፪ ።

፱ ወእምከመ ሰምዑ ከነዓን ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ዛቲ ምድር፥ የዐግቱነ ወያጠፍኡነ እምድር፥ ወምንተ ትሬሲ ለስምከ ዐቢይ ።

በዚች አገር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉና የከነዓን ሰዎች ጥፋታቸውን ከሰሙ ከበው ከአገር ያጠፉናል ለታላቁ ስምህስ ምን ታደርጋለህ፤ አለ ። ዘፀ፡ ፴፪ ፲፪ ።

፲ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ተንሥእ ወለምንት ትወድቅ አንተ በገጽከ ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን ተነሥ፥ ለምን በግንባርህ ትወድቃለህ፤ አለው ። ኢያ፡ ፯ ፯ ።

፲፩ አበሱ ሕዝብ ወክሕዱ ኪዳንየ ዘተከየድኩ ምስሌሆሙ ወነሥኡ እምዘሕሩም፥ ወሰረቁ ወወደዩ ውስተ ንዋያቲሆሙ ።

ሕዝቡ በደሉ ከነሱ ጋር የተማማልኩት መሐላዬን አፍርሰው እርም ከሉት ገንዘብ ወሰዱ፥ ሰርቀውም ከገንዘባቸው ጋር ጨመሩ ። ዘዳ፡ ፲፮ ፪ ።

፲፪ ወኢይክሉ እንከ ደቂቀ እስራኤል ቀዊመ ቅድመ ፀሮሙ ወይመይጡ ዘባናቲሆሙ ቅድመ ፀሮሙ እስመ ርጉማን ኮኑ፥ ወኢይደግም እንከ ሀልዎ ምስሌክሙ ለእመ ኢያውፃእክሙ እምኔክሙ ዘርጉም ።

እንግዲህ ወዲህ የእስራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት ቆመው መዋጋት አይችሉም የተረገሙ ሆነዋልና፥ ጀርባቸውን መልሰው ይሸሻሉ፥ አሁንም የተረገመውን ሰው ከናንተ ለይታችሁ ካላወጣችሁ እንግዲህ ወዲህ ከናንተ ጋር በረድኤት አልኖርም ። ዘኍ፡ ፲፬ ፵፭ ።

፲፫ ተንሥእ ወቀድሶሙ ወበሎሙ አንጽሑ ርእሰክሙ ለጌሠም፥ እስመ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘሕሩም ሀለወ ውስቴትክሙ ወኢትክሉ እንከ ቀዊመ ቅድመ ፀርክሙ እስከ ታሴስሉ እምኔክሙ ዘሕሩም ።

ከወደቅህበት ተነሥተህ ለያቸው፥ በውስጣቸውም የተረገመ ሰው አለና፥ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ራሳችሁን ለነገ አንጹ አለ በላቸው፥ የተረገመውን ከናንተ ለይታችሁ ካላስወገዳችሁ እንግዲህ ወዲህ በጠላቶቻችሁ ቁሞ መዋጋት አትችሉም አለ በላቸው አለው ።

፲፬ ወይጌሡ በጽባሕ ወይትጋብኡ ኵሎሙ በበሕዘቢሆሙ ወሕዝብ ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለይትፈለጡ በበ ነገዶሙ ወይቁሙ፥ ወነገድ ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለይትፈለጡ ወይቁሙ በበቤቶሙ፥ ወቤት ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለይትፈለጡ ወይቁሙ በበብእሲሁ ።

ሲነጋ ሂደው ሁሉም በየወገናቸው ይሰብሰቡ እግዚአብሔር በላያቸው ላይ ምልክት ያሳየባቸው ወገኖች ተለይተው በየነገዳቸው ይቁሙ፥ እግዚአብሔር በላያቸው ላይ ምልክት ያሳየባቸው ወገኖች አንዱም አንዱም ሰው ተለይተው ይቁሙ ። ፩ ሳሙ፡ ፩ ፲፥ ፲፬ ፵፩ ።

፲፭ ወብእሲ ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለያውዕይዎ በእሳት ሎቱ ወለኵሉ ዘዚአሁ እስመ ክሕደ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር ወገብረ ኀጢአተ ላዕለ እስራኤል ።

እግዚአብሔር በላዩ ላይ ምልክት ያሳየበትን ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፥ በእስራኤልም ላይ ኃጢአት ሠርቷልና እሱን ከወገኖቹ ጋር በእሳት ያቃጥሉት አለው ። ኢያ፡ ፯ ፲፩፥ ፩ ሳሙ፡ ፲፬ ፴፰ ።

፲፮ ወጌሠ ኢያሱ ወአስተጋብኦሙ ለሕዝብ በበሕዘቢሆሙ ወአስተርአየ ላዕለ ሕዝበ ይሁዳ ።

ኢያሱም ገሥግሦ ሕዝቡን በየወገናቸው ሰበሰባቸው በይሁዳም ወገኖች ላይ ምልክት ታየ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወተፈልጡ ሕዝበ ይሁዳ በበነገዶሙ ወአስተርአየ ላዕለ ነገደ ዛራ በቤቱ ወአስተርአየ ላዕለ ቤተ ዘንበሪ ። | ፲፯ | የይሁዳም ወገኖች በየወገናቸው ተለዩ ፡ በዛራም ወገን ላይ ምልክት ታየ ፡ የዛራም ወገን በየወገኑ ተለየ ፡ በዘንበሪ ወገን ላይ ምልክት ታየ ። ዘኁ፡ ፳፮ ፳ ። |
| ወተፈልጠ ቤተ ዘንበሪ በበብእሲሁ ወአስተርአየ ላዕለ አካን ወልደ ከርሚ ወልደ ዘንበሪ ወልደ ዛራ ዘእምሕዝበ ይሁዳ ። | ፲፰ | የዘንበሪም ወገን አንዱም አንዱም ሰው ተለየ ፡ ከነገደ ይሁዳ የተለየ የዛራ ልጅ የዘንበሪ ልጅ በሚሆን በከርሚ ልጅ በአካን ላይ ምልክት ታየ ። ኢያ፡ ፯ ፩ ። |
| ወይቤሎ ኢያሱ ለአካን ወልድየ አእኵቶ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወአመና ወአይድዐኒ ምንተ ገበርከ ወኢትኅባእ እምኔየ ። | ፲፱ | ኢያሱም አካንን ልጄ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔርን አመስግነው እመነውም ምን አድርገኸል ፣ አትሸሸገኝ ንገረኝ አለው ። ፩ ሳሙ፡ ፯ ፰፡ ኢሳ፡ ፵፪ ፲፪ ። |
| ወአውሥአ አካን ለኢያሱ ወይቤሎ አማን አነ አበስኩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፡ ከመዝ ወከመዝ ገበርኩ ። | ፳ | አካንም ለኢያሱ እንዲህ ብሎ መለሰለት በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ፊት እውነት በድያለሁ ፡ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ ። |
| ሶበ ርኢኩ በውስተ በርበር ልብሰ ዐሥቅ አሐደ ወክልኤተ ምእተ ጠፋልሐ ብሩር ወልሳነ አሐተ እንተ ወርቅ ተአከል ሐምሳ ዲድርከመ ወተውላጣ ፈተውኩ ወነሣእኩ ወናሁ ሀለወ ድፉነ ውስተ ደብተራየ ወጠፋልሐ ብሩርኒ ሀለወ መትሕቴሁ ። | ፳፩ | በዘረፋ መካከል አራት ኅብር አምስተኛ ወርቀ ዘቦ ፡ ሁለት መቶ ምዝምዝ ብር ፡ አምሳ ወቄት የምትሆን አንዲት ልሳነ ወርቅ በየሁ ጊዜ ለውጢን መስጠት ወድጄ ወሰጃሁ ፡ እነሆም በድንኳኔ ውስጥ ተቀብሯል ፡ ምዝምዙም ብር በበታቹ አለ ። ዘፀ፡ ፳ ፲፯ ፡ ምሳ፡ ፲፭ ፳፯ ። |
| ወፈነወ ኢያሱ ደቀ ወሮጹ ኀበ ትዕይንት ውስተ ደብተራሁ ወሀለወ ዝኩ ድፉን ውስተ ደብተራሁ ወብሩርኒ ሀለወ ምስሌሁ መትሕቶ ። | ፳፪ | ኢያሱም አሽከሮቹን ላከ ከሰፈርም ወደ ድንኳኑ ፈጥነው ሄዱ ፡ እሱም በድንኳኑ ውስጥ ተቀብሮ ብሩም በታች ሆኖ አገኘው ። ፩ ነገ፡ ፳፩ ። |
| ወአውፅእ እምውስተ ደብተራሁ ወወሰዱ ኀበ ኢያሱ ወኀበ ኵሉ ሊቃናተ እስራኤል ወአንበሩ ቅድመ እግዚአብሔር ። | ፳፫ | ከድንኳኑም አውጥተው ወደ እስራኤል ሁሉና ወደ ኢያሱ ወሰደው በእግዚአብሔር ፊት አኖሩት ። እንባ፡ ፩ ፱ ። ሉቃ፡ ፲፱ ፲፭ ። |
| ወነሥአ ኢያሱ ለአካን ወልደ ዛራ ወለውእቱ ብሩር ወለውእቱ ልብስ ወለይእቲ ልሳን እንተ ወርቅ ወወሰዶሙ ውስተ ቈለተ አኮር ለአካን ወደቂቁ ወለአዋልዲሁ ወለአልሕምቲሁ ወለአብግዒሁ ወለአእዱጊሁ ወለደብተራሁ ወለኵሉ ንዋዩ ወወሰዶሙ ውስተ ኤሜቃከር ። | ፳፬ | ኢያሱን የዛራን ልጅ አካንን ያዘው ያንን ልብስና ያንንም ብር ያችንም ልሳነ ወርቅ ይዞ አካንና ልጆቹን ላሞቹንና ሴቶች ልጆቹን አህዮቹንና በጎቹን ገንዘቡ ሁሉና ድንኳኑን ወስዶ በኤሜቃከር ጣላቸው ። ፩ ሳሙ፡ ፲፰ ፲፯ ። ሰቆ፡ ኤር፡ ፫ ፶፫ ። |
| ወይቤሎ ኢያሱ ለአካን ለምንት ሠሮከነ ለይሥሩከ እግዚአብሔር በከመ ዮም ፡ ወወገርዎ በእብን ኵሎሙ እስራኤል ወአውዐይዎሙ በእሳት ወወገርዎሙ በእብን ። | ፳፭ | ኢያሱ አካንን ለምን አጠፋኸን እኛን ዛሬ እንዳጠፋኸን እግዚአብሔር ያጥፋህ አለው ፡ እስራኤልም ሁሉ በድንጋይ ወግረው ገደሉት ፡ በድንጋይ ወግረው በእሳት አቃጠሏቸው ። |
| ወአቀሙ ሎቱ ሐውልተ እንተ እብን እስከ ዛቲ ዕለት ወአኅደገ እግዚአብሔር መንሱተ መዐቱ ወበበይነ ዝንቱ ሰመዮ ኤሜቃከር እስከ ዛቲ ዕለት ። | ፳፮ | እስከዚህችም ቀን ድረስ የደንጊያ ሐውልት አቆሙበት ፡ እግዚአብሔርም ፈርዶ ያመጣውን መቅሠፍት ተወ ስለዚህም እስከዚች ቀን ድረስ ኤሜቃከር (የአኮር ሸለቆ) ብሎ ጠራው ። ኢያ፡ ፰ ፳፱ ፡ ፲ ፳፮ ። |

## ምዕራፍ ፰ ።

| | | |
|---|---|---|
| ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ኢትፍራህ ወኢትደንግፅ ንሥኦሙ ምስሌከ ለኵሎሙ እደው መስተቃትላን ወተንሥአ ወዕርግ ውስተ ጋይ እስመ ናሁ አግባእክዎ ውስተ እዴከ ለንጉሠ ጋይ ወለሕዝቡኒ ወለሀገሩኒ ወለምድሩኒ ። | ፩ | እግዚአብሔር ኢያሱን አትፍራ ፡ አትደንግጥ እነሆ የጋይን ንጉሥ ከሠራዊቱ ፡ ከአገሩ ከምድሩ ጋር በእጅህ ጥየዋለሁና አርበኞችን ጕልማሶችን ሁሉ ይዘኻቸው ተነሥተህ ወደ ጋይ ውጣ አለው ። ዘዳ፡ ፴፩ ፰ ። ኢያ፡ ፩ ፳፱ ፯ ፪ ። መዝ፡ ፵፱ ፫ ። |
| ወትገብራ ለጋይ ወለንጉሣ በከመ ገበርካ ለኢያሪኮ ወለንጉሣ ወበርበረ እንስሳ በርብሩ ለርእስክሙ ወበሕቱ ፈኑ ይዕግትዋ ለሀገር እንተ መንገለ ከዋላሃ ። | ፪ | ኢያሪኮን እንዳጠፋኸት ጋይን ንጉሧንም እንዳጠፋህ ንጉሧን ታጠፋለህ ፡ የከብቱንም ምርኮ ለራሳችሁ ዝረፉ ፡ ነገር ግን አገሪቱን በኋላዋ ይከቧት ዘንድ ሰው ላክ አለው ። |
| ወተንሥአ ኢያሱ ወኵሉ ሕዝብ መስተቃትላን ወዐርጉ ውስተ ጋይ ወኀረየ ኢያሱ ሠለስተ እልፈ እደወ ጽኑዓነ ወመስተቃትላነ ወኃያላነ ወፈነዎሙ በሌሊት ። | ፫ | ኢያሱም ከአርበኞች ወገኖቹ ሁሉ ጋር ተነሣ ፡ ወደ ጋይም ወጡ ፡ የጸኑ አርበኞች ኃያላን የሚሆኑ ሦስት እልፍ ሰዎችን መርጦ በሌሊት ላካቸው ። |

፬ ወአዘዞሙ ወይቤሎሙ ሑሩ ከመ ታእምሩ ዕማትዋ ለሀገር እንተ መንገለ ከዋላሃ ወኢትርኀቁ ፈድፋደ እምሀገር ወንበሩ ኵልክሙ ድልዋኒክሙ ።

፭ ወአንሰ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌየ ንቀርብ ኀበ ሀገር ወሶበ ወፅኡ ሰብአ ጋይ ወተቀበሉነ ከመ ቀዲሙ ንጐይይ እምቅድመ ገጾሙ ።

፮ ወሶበ ወፅኡ ወዴገኑነ ናርኅቆሙ እምሀገር ወይብሉ ነትዑ እሉሂ እምቅድመ ገጽነ ከመ ቀዲሙ ወንሕነሂ ንጐይይ እምቅድመ ገጾሙ ።

፯ ወእምዝ እንከ ትትነሥኡ እንትሙሂ ወእኀዝዋ ለሀገሮሙ ወይገብኦ እግዚአብሔር እምላክክሙ ውስተ እዴክሙ ።

፰ ወእምከመ በእክምዋ ለሀገሮሙ አውዕይዋ በእሳት ወግበሩ በከመ እቤለክሙ ናሁ አዘዝኩክሙ ።

፱ ወፈነዎሙ ኢያሱ ወሖሩ ይዕግትዋ ለሀገር ወነበሩ ማእከለ ቤቴል ወማእከለ ጋይ እምበሕረ ጋይ ወቤተ ኢያሱ ሀየ በይእቲ ሌሊት ማእከለ ሕዝብ ።

፲ ወጌሠ በጽባሕ ወርእዮሙ ለሕዝብ ወዐርጉ ውእቱ ወሊቃውንቲሆሙ ለእስራኤል ፍጽመ ቅድመ ሕዝብ ላዕለ ጋይ ።

፲፩ ወዐርጉ ኵሎሙ ሕዝብ መስተቃትላን ምስሌሁ ወበጽሑ ወቀርቡ ቅድመ ሀገር እንተ መንገለ ጽባሒሃ ወዲእቶ ማእከሎሙ ወማእከለ ጋይ ።

፲፪ ወነሥአ ኢያሱ ኃምስ ምእተ ብእሴ ወአንበሮሙ ይዕግቱ ማእከለ ቤቴል ወማእከለ ጋይ መንገለ በሕረ ጋይ ።

፲፫ ወአንበሩ ኵሉ ሕዝብ ተዓይኒሆሙ እንተ መንገለ መስዕ ለሀገር ወጽንፉ እስከ በሕረ ሀገር ፡ ወሖረ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ማእከለ ውእቱ ጊአት ።

፲፬ ወሶ ሰምዐ ንጉሠ ጋይ ጌሠ ፍጡነ ወወፅኡ ሰብአ ሀገር ወተቀበልዎሙ እንተ ቅድሜሆሙ ከመ ይትቃተልዎሙ ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌሁ በጊዜሃ መንጸረ ዐረባ ወኢያእመረ ውእቱሰ ከመ ዐገትዎሙ እንተ መንገለ ከዋላሃ ለሀገር ።

፲፭ ወሶበ በጽሕዎሙ ጕዩ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል እምቅድመ ገጾሙ ወነትዑ ውስተ ፍኖተ ገዳም ።

፲፮ ወኄሉ ኵሉ ሕዝበ ብሔር ወተለውዎሙ ወሰደድዎሙ ወዴገንዎሙ እምድኅሬሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፲፯ ወርኅቁሙ እሙንቱ እምሀገር አልቦ ዘተርፈ ወኢመኑሂ ውስተ ጋይ ወውስተ ቤቴል ዘኢተለዎሙ ወዘኢዴገኖሙ ለእስራኤል ወኀደግዋ ለሀገር ርኅዎ ።

፲፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ አልዕል እዴከ በጋይስ ዘውስተ እዴከ ላዕለ ጋይ እስመ ውስተ እዴከ አግ ብእክዋ ።

፲፱ ወእለሂ ዐገቱ ይትነሥኡ ፍጡነ እመከናቲሆሙ ፡ ወአልዐለ ኢያሱ እዴሁ በጋይስ ላዕለ ሀገር ፡ ወእለሂ ዐገቱ ተንሥኡ ፍጡነ እመከናቲሆሙ ወወፅኡ ሶበ አልዐለ እዴሁ በጋይስ ወበኡ ሀገረ ወአኀዝዋ ወአውዐይዋ ፍጡነ በእሳት ።

እንደምታውቁ ሂዱባት አገሪቱን በኋላዋ ከበቧት ፤ ከአገሪቱም ፈጽማችሁ አትራቁ ሁላችሁም የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ተደበቁ ብሎ አዘዛቸው ።

ከኔ ጋራ ያሉ ሕዝብ ሁሉና እኔ ግን ወደ ከተማይቱ እንቀርባለን ፤ ወጥተው በጦርነት በተቀበሉን ጊዜ እንደ ቀድሞአችን ከፊታቸው እንሸሸለን ። መሳ፡ ፳ ፴፪ ።

ወጥተው በተከተሉንም ጊዜ ከከተማይቱ እናርቃቸዋለን እነዚህም እንደ ቀድሞው ከፊታችን ሸሹ ይላሉ ፤ እኛም ከፊታቸው እንሸሻለን ። ኢያ፡ ፫ ፲፯ ።

ከዚህም በኋላ እናንተ ተነሥታችሁ አገራቸውን ያዟት ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርም በእጃችሁ ይጥላታል ። ኢያሱ ፩ ፲፯ ። ፪ ... ፲፫ ፳ ።

አገራቸውንም ከገባችኋት በኋላ በእሳት አቃጥሏት ፤ እነሆ አዝዠኋችኋለሁ እንዳዘዝኋችሁም አድርጉ ።

ኢያሱም ላካቸው እነሱም አገሪቱን ይከቧት ዘንድ ሄዱ ፤ በጋይና በቤቴል መካከል በጋይ በምዕራብ በኩል ተቀመጡ ፤ ኢያሱም በዚያች ሌሊት በሕዝቡ መካከል አደረ ። ዘፍ፡ ፲፪ ፰፡ ፲፫ ፫ ።

ሲነጋም ገሥግሦ ሂዶ ሕዝቡን አያቸው የእስራኤል አለቆችና እሱ እስቀድመው በሠራዊቱ ፊት ወደ ጋይ ወጡ። ዘፍ፡ ፳፪ ፫ ። መዝ፡ ፻፩ ፰ ። ኤር፡ ፳፩ ፲፪ ።

አርበኞች ወገኖች ሁሉ ከሱ ጋራ ወጡ ፤ በምሥራቅ በኩል ፊት ለፊት ደርሰው ቀረቡ ፤ በጋይና በእስራኤልም መካከል ዱር (ሸለቆ) ነበር ።

ኢያሱ አምስት ሺሕ ሰዎች ወስዶ ይከቡ ዘንድ በጋይና በቤቴል መካከል በጋይ ምዕራብ በኩል አኖራቸው ።

ሕዝቡ ሁሉ ሠራዊቶቻቸውን በአገሩ በቀኝ በኩል አኖሩ ዳርቻውም እስከገሩ ምዕራብ ድረስ ነው ፤ ኢያሱም በዚያች ቀን በዱር መካከል ሄደ ። ዘፍ፡ ፵፱ ፲፱ ።

የጋይ ንጉሥም በሰማ ጊዜ ፈጥኖ ገሥግሦ ሂዶ ከርሱ ጋራ ያሉ ሠራዊቱ ሁሉና እሱም ወድያው በዐረብ አፍ ዘገር ሊዋጓቸው ወጥተው ያገሪቱ ሰዎች በፊታቸው ተቀበሏቸው እሱ ግን አገሪቱን በኋላዋ እንደ ከበቧት አላወቀም ነበር ። መሳ፡ ፳ ፴፬ ።

በደረሱባቸውም ጊዜ ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ከፊታቸው ወደ ምድረ በዳው መንገድ ፈጽመው ሸሹ ።

በአገር ያሉም ሰዎች ዕልል አሉ፡ ተከትለውም አባረሯቸው የእስራኤልን ልጆች በኋላቸው ተከተሉዋቸው ።

እነዚያ ከገር በራቁ ጊዜ እስራኤልን ያልተከተላቸው በቤቴልና በጋይ ማንም ማን የቀረ አልነበረም ፤ አገሪቱን ክፍቷን ተዉዋት ።

እግዚአብሔር ኢያሱን በእጅህ ጥያታለሁና ፤ በእጅህ በያዝከው ጋሻ (ጦር) ወደ ጋይ ጥቀሳቸው አለው ።
ዘዳ፡ ፯ ፳፫ - ፳፬ ። ኢያሱ ፴፱ ፫ ።

የከበቡትም ሰዎች ከበታቸው ፈጥነው ይነሡ አለው ፤ በእጁም በያዘው ጋሻ ወደ ጋይ ጠቀሳቸው ፤ በእጁም በያዘው ጋሻ በጠቀሳቸው ጊዜ የከበቡት ሰዎች ከበታቸው ፈጥነው ተነሥተው ወጡ ፤ ወደ አገሪቱም ገብተው ያዙዋት ፤ ፈጥነውም በእሳት አቃጠሏት ።

፳ ወሰበ ነጸሩ ድኅሬሆሙ ሰብአ ጋይ ወርእዩ ጢሰ የዐ
ርግ ውስተ ሰማይ እምውስተ ሀገሮሙ ኀጥኡ እንከ ኀበ
ይጕየዩ ኢ ለፌ ፡ ወኢ ለፌ ወሕዝብኒ እለ ጐዩ ውስተ
ገዳም ተመይጥዎሙ ፡ ለእለ ዴገንዎሙ ።

፳፩ ወርእየ ኢያሱ ከመ ረከብዋ ለሀገር እለ ዐገትዋ ወእለ
መሩ ሰበ ርእዩ ጢሰ የዐርግ ውስተ ሰማይ እምሀገር ወእ
ምዝ ተመይጡ እስራኤል ወቀተልዎሙ ለሰብአ ጋይ ።

፳፪ ወእልክቱሂ ወፅኡ እምሀገር ወተቀበልዎሙ ወእግብ
እዎሙ ማእከለ ትዕይንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወቀተል
ዎሙ ወእልክቱሂ እምከሐ ወእሉሂ እምለፌ እስከ ኢያት
ረፉ እምኔሆሙ ነፋጺተ ዘድኅነ ።

፳፫ ወአኀዝዎ ለንጉሠ ጋይ ሕያዎ ወወሰድዎ ኀበ ኢያሱ ።

፳፬ ወሰበ አኅለቁ ቀቲሎቶሙ ለሰብአ ጋይ በገዳም ወበ
ሙራደ ደብር በኀበ ዴገንዎሙ ወቀተልዎሙ ለኵሎሙ
በሐፂን ወአጥፍእዎሙ ተመይጠ ኢያሱ በጊዜሃ ውስተ
ጋይ ወቀተለ በሰይፍ ።

፳፭ ወኮኑ ኵሎሙ ሰብአ ጋይ እለ ሞቱ ይእተ አሚረ ተባ
ዕት ወአንስት እልፈ ወዕሥራ ምእተ ።

፳፮ ወኢሜጠ ኢያሱ እዴሁ እንተ አልዐለ በጋይሶ እስከ
አጥፍአሙ ለሰብአ ጋይ ።

፳፯ ዘእንበለ እንስሳ ወበርበረ ሀገር ኵሎ ዘበርበሩ ደቂቀ
እስራኤል ለርእሶሙ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኢያሱ ።

፳፰ ወአውዐያ ኢያሱ ለሀገር በእሳት ወከነት ሐመደ ወረ
ሰያ ከመ አልበ ዘይነብራ ለዝሉፉ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፳፱ ወለንጉሠ ጋይ ሰቀሎ ዲበ ዕፀ ዘማበ ወነበረ ዲበ
ዕፅ እስከ ሠርክ ወሰበ ዐርበ ፀሐይ ኤዘዘ ኢያሱ ያው
ርድዎ ፡ ወአውረድዎ እምዲበ ዕፅ ወወገርዎ ውስተ ግብ
ቅድመ አንቀጸ ሀገር ወአንበሩ ላዕሌሃ አእባነ ዐበይተ
እስከ ዛቲ ዕለት ።

፴ ወነደቀ ኢያሱ ምሥዋዐ ይእተ አሚረ ለእግዚአብሔር
አምላከ እስራኤል በደብረ ጌባል በከመ አዘዞሙ ሙሴ
ቍልዔሁ ለደቂቀ እስራኤል ።

፴፩ በከመ ጽሑፍ ውስተ ሕገ ሙሴ ምሥዋዐ ዘእብን በመ
ጥበሕት ዘኢተወቅረ ወዘኢተገብረ በሐፂን ወአዕረገ ቍር
ባነ ወመሥዋዕተ መድኀኒት ለእግዚአብሔር ።

፴፪ ወጸሐፎ ኢያሱ ውስተ እእባን ለዳግም ኦሪት ዘጸሐፈ
ሙሴ በቅድሜሆሙ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ።

፴፫ ወኵሉ እስራኤል ወመኳንንቲሆሙ ወጸሐፍቶሙ ይቀ
ውሙ እምጸጋም ወእምየማን ቅድመ ታቦት ወካህናትሰ
ወሌዋውያን ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ።

፴፬ ወመንፈቆሙ ለግዩራን ወእለሂ እምፍጥረቶሙ መንፈ
ቆሙ ጥቃ ደብረ ጌባል ወመንፈቆሙ ጥቃ ደብረ ገሪዛን
እለ አዘዞሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ከመ ይባር

የጋይ ሰዎችም ወደ ኋላቸው ተመልሰው በዩ ጊዜ
ጢስ ከአገራቸው ወደ ሰማይ አቅንቶ ሲወጣ ተመለከቱ ፡
ከዚያ በኋላ ወድያና ወዲህ የሚሸሹበትን አጡ ወደ ምድ
ረ በዳ የሸሹትም ወገኖች የተከተሏቸውን ሰዎች ተመለሱ
ባቸው ። ኢያ፡ ፰ ፲፩ ፳፬ ፡ መሳ፡ ፲፰ ፲ ።

ኢያሱም የከበቧት ሰዎች አገሪቱን እንዳገኙዋት አየ ፡
ከአገር ወደ ሰማይ ጢስ አቅንቶ ሲወጣ በዩ ጊዜ አገሬ
ቸው እንደ ተያዘች አወቁ ፡ ከዚህ በኋላ እስራኤል ተመ
ልሰው የጋይን ሰዎች ወጉዋቸው ።

እነዚያም ከገር ወጥተው ተቀበሏቸው በእስራኤል ሰ
ፈር መክከል አግብተው ሸሽቶ የዳነውን የማያስቀሩ እስ
ኪሆኑ ድረስ እኒያ ከወዲያ እኒህ ከወዲህ ሁነው ወጉዋቸው።
ዘሌዋ፡ ፳፯ ፳፱ ። ኢዮብ ፳ ፩ ።

የጋይን ንጉሥ ደኅነኛውን (ሳይሞት) ይዘው ወደ
ኢያሱ ወሰዱት ።

በተከተሏቸው ቍልቍለትና በምድረ በዳ የጋይን ሰ
ዎች መውጋት ከጨረሱ በኋላ ሁሉንም በጦር ወግተው
ከጠፉዋቸው በኋላ ኢያሱ ወድያው ወደ ጋይ ተመልሶ
በሰይፍ አጠፋቸው ።

ያን ጊዜ የሞቱ የጋይ ሰዎች ሴትና ወንድ ሁሉ አል
ፍ ከሁለት ሺሕ ሆኑ ።

ኢያሱም የጋይን ሰዎች እስኪያጠፋቸው ድረስ በጋ
ሻው የጠቀሰበት እጁን አላጠፈም (አልመለሰም) ።

እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዳዘዘው የእስራኤል ልጆች
ለራሳቸው ከአገር ከዘረፉት ገንዘብ ሁሉና ከከብቱ በቀር
አልፍ ከሁለት ሺሕ ሆኑ ። ዘኍ፡ ፴፩ ፳፪ ፳፮ ።

ኢያሱም አገሪቱን በእሳት አቃጠላት ፡ አመድም ሆነች
እስከዛችም ቀን ድረስ ለዘለዓለሙ የሚኖርባት እንዳይኖር
አደረጋት ። ዘዳ፡ ፲፫ ፲፮ ።

የጋይንም ንጉሥ በዝግባ ዕንጨት ላይ ሰቅለው እስከ
ሠርክ ድረስ በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ ዋለ ፡ ፀሐይ ከገባ
በኋላም ኢያሱ ያወርዱት ዘንድ አዘዘ ፡ ከዕንጨት ላይ
አውርደው በአገሩ አደባባይ ፊት ለፊት ባለ ጕድጓድ ው
ስጥ ጣሉት እስከዚችም ቀን ድረስ ታላላቅ ደንጊያዎችን
በጕድጓዱ አፍ ገጠሙት ። ኢያ፡ ፺ ፳፯ ።

ያን ጊዜ ኢያሱ ጌባል በሚባል ተራራ ለእስራኤል
ፈጣሪ ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ ፡ የእግዚአብሔር
ባለሟል ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንዳዘዛቸው ።

በሙሴ መጽሐፍ በዳግም ሕግ እንደ ተጻፈ በመጥረ
ቢያ ባልተጠረበ በብረትም ባልተቀረጸ መሠውያ ላይ የድ
ኅነት መሥዋዕትንና ቍርባንን ለእግዚአብሔር አቀረበ ።

ሙሴ በእስራኤል ልጆች ሁሉ ፊት የጻፈው ዳግም
ሕግን ኢያሱ በደንጊያዎች ላይ ጻፈው ። ዘዳ፡ ፳፯ ፳፰ ።

መኳንንቱና እስራኤል ሁሉ ሹማምንቱም በታቦት ፊት
በቀኝ በግራ ቁመው ነበር ፡ የሌዊ ወገኖችና ካህናቱ ግን
የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸክመው ነበር ።

የእስራኤልን ወገኖች ይመርቁዋቸው ዘንድ የእግዚአ
ብሔር ወዳጅ ሙሴ ያዘዛቸው ከመጻተኞችም ፍጥረታ
ቸው ከእስራኤል የሆኑትም ወገን እኩሌታዎች በጌባል

ክዎሙ ለሕዝበ እስራኤል ወእሙንቱ ይቀድሙ ።

አጠገብ እኩሌታዎች በገሪዛን አጠገብ ቆመው ነበር ።

፴፭ ወእምድኅረ ዝንቱ አንበበ ኢያሱ ኵሎ ነገሮ ለዝንቱ ሕግ በረከቶሂ ወመርገሞሂ ኵሎ ዘጽሑፍ ውስተ ዝንቱ ሕገ ሙሴ ።

ከዚህ በኋላ ኢያሱ የዚህን የዳግም ሕግን ነገር ሁሉ በረከቱንም መርገሙንም አነበበላቸው ፤ በሙሴ መጽሐፍ በዳግም ሕግ የተጻፈውን ሁሉ ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፩ ።

፴፮ ወአልቦ ቃል እምኵሉ ዘአዘዘ ሙሴ ለኢያሱ ዘኢያን በበ ወዘኢያስምዖሙ ኢያሱ ለኵሉ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል ለእደዊሆሙ ወለአንስትያሆሙ ወለደቂቆሙ ወለግዩራን እለ ሖሩ ምስሌሆሙ ።

ሙሴ ለኢያሱ ካዘዘው ሁሉ ፤ ኢያሱ ለእስራኤል ልጆች ወገን ሁሉ ለሴቶችና ለወንዶች ከእስራኤል ጋራ ለሄዱት መጻተኞችና ለልጆቻቸውም ያላሰማቸውና ያላነበበላቸው ቃል የለም ። ዘዳ፡ ፴፩ ፲፪ ፤ ኢያ፡ ፰ ፴፪ ።

## ምዕራፍ ፱ ።

፩ ወሶበ ሰምዑ ኵሎሙ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ ዮርዳኖስ እለ ውስተ አድባር ወእለ ውስተ ገዳም ወእለ ውስተ ኵሉ ሐይቀ ባሕር ዐቢይ ወእለ ውስተ አንጢሊባኖን ወኬጤዎን ወከናኔዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወአሞሬዎን ወጌርጌሴዎን ወኢያቡሴዎን ተጋብኡ ኅቡረ ከመ ይፅብእዎሙ ለኢያሱ ወለኵሉ እስራኤል ።

በዮርዳኖስ ማዶ በቈላው በደጋው በታላቁ በሕር ዳር ያሉ የአሞሬዎን ነገሥታት ሁሉ በሊባኖስም አቅራቢያ የሚኖሩ የኬጤዎን የከናኔዎን የፌርዜዎን የኤዌዎን የአሞሬዎን የጌርጌሴዎንና የኢያቡሴዎን ሰዎች የእስራኤልን መምጣት በሰሙ ጊዜ ኢያሱንና እስራኤልን ሁሉ ለመውጋት አንድነት ተሰበሰቡ ። ዘዳ፡ ፩ ፯ ፤ ኢያ፡ ፲፪ ፰ ።

፪ ወሰምዑ እለ ይነብሩ ውስተ ገባኦን ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር ላዕለ ኢያሪኮ ወላዕለ ጋይ ።

በገባኦን የሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር በኢያሪኮና በጋይ ያደረገውን ሁሉ ሰሙ ። ኢያ፡ ፲፩ ፲፪ ።

፫ ወገብሩ እሙንቱሂ በጕሕሉት ወመጽኡ ሰኰቆሙ ወአስተዳሊዎሙ ወፆሩ መሰንቅቲሆሙ ብሉያተ ዲበ መታክፍቲሆሙ ወዝቃቀ ወይን ብሉያተ ወሥጡጣተ ወጥቁባተ ።

እነሱም ተንኰል አድርገው መጡ ፤ ስንቃቸውን ሰንቀው አዘጋጅተው ያረጁ አቁማዶቻቸውን በትከሻቸው ተሸክመው ተቀደው የተጠቀሙና ያረጁ የወይን ረዋቶችን ።

፬ ወብቱከ ቶታነ አሣእኒሆሙ ወብሉይ አሣእኒሆሙ ወግቱት ውስተ እገሪሆሙ ወአልባሲሆሙኒ ብሉይ በላዕሌሆሙ ወኅብስተ ስንቆሙኒ ይቡስ ወስሑብ ።

የጫማዎቻቸው ማዘቢያ ተቈርጦ ጫማቸው አርጅቶ በእግሮቻቸው ማትቻ ሆኖ በላያቸውም ላይ ልብሳቸው ያረጀ ሆኖ የሰንቅትም እንጀራ ደርቆ ሻግቶ ።

፭ ወመጽኡ ኀበ ኢያሱ ወኀበ እስራኤል ውስተ ገልገላ ወይቤልዎሙ ለኢያሱ ወለኵሉ እስራኤል እምርኁቅ ብሔር መጻእነ ወይእዜኒ ተማሐሉ ምስሌነ ።

ከኢያሱና ከእስራኤል ዘንድ ወደ ጌልገላ መጥተው ለኢያሱና ለእስራኤል ልጆች ሁሉ እኛ ከሩቅ አገር መጥተናል አሁንም ከኛ ጋራ ተማማሉ አሏቸው ።

፮ ወይቤልዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለኤዎዋውያን እፎ ንትማሐል ምስሌክሙ መሐላ ሁቁ ዮጊ ቅሩባነ ትነብሩ ።

የእስራኤልም ልጆች የኤዌዎንን (የገባኦን) ከናንተ ጋራ እንዴት መሐላ እንማማላለን ፤ አሁንም በአቅራቢያችን ትኖሩ እንደሁ ዕወቁ አሉዋቸው ።

፯ ወይቤልዎ ለኢያሱ ንሕነሰ አግብርቲከ እምርኁቅ ብሔር ንሕነ ፤ ወይቤሎሙ እምአይቴ አንትሙ ወእምአይቴ መጻእክሙ ።

ኢያሱን እኛ ከሩቅ አገር የመጣን ባሮችህ ነን አሉት እርሱም ከወዴት ናችሁ ፤ ከወዴትስ አገር መጣችሁ ፤ አላቸው ። ኢያ፡ ፱ ፲፩ ፤ ፪ ነገ፡ ፲ ፭ ።

፰ ወይቤልዎ እምርኁቅ ብሔር ጥቀ መጻእነ ንሕነ አግብርቲከ በስመ እግዚአብሔር አምላክከ እስመ ሰማዕነ ዘበእንቲአሁ ኵሎ ዘገብረ በግብጻውያን ።

እነሱም እኛ ባሮችህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም አምነን እጅግ ከሩቅ አገር መጥተናል ፤ በግብጻውያን ላይ ያደረገውን ሁሉ ። ኢያ፡ ፪ ፲ ፤ ፮ ፳፯ ።

፱ ወኵሎ ዘገብረ በክልኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤ በሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ፤ ወበዖግ ንጉሠ ባሳን ዘይነብር ውስተ አስጣሮት ወውስተ ኤንድራይን ።

በዮርዳኖስ ማዶ በሚኖሩ በሁለቱ በአሞሬዎን ነገሥታት በኤንድራይንና በአስጣሮት በሚኖሩ በባሳን ንጉሥ በዓግና በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን ያደረገውን ሁሉ ሰምተን መጥተናል አሉት ። ዘኁ፡ ፳ ፳፩ ፤ ፳ ፲፩ ።

፲ ወይቤሉነ ሊቃናቲነ ወኵሉ ሰብአ ብሔርነ ንሥኡ ስንቀ ለፍኖት ወሑሩ ትትቀበልዎሙ ወበልዎሙ አግብርቲክሙ ንሕነ ወይእዜኒ ተማሐሉ ምስሌነ ።

የአገራችን ሰዎች ሁሉና አለቆቻችን ትቀበሏቸው ዘንድ እንግዲህ ለመንገዳችሁ ስንቅ ይዛችሁ ሂዱ እኛ ባሮቻችሁ ነን አሁንም ከኛ ጋር ተማማሉ በሉዋችሁ አሉን ።

፲፩ ወናሁ ዝንቱ ኅብስትነ እንዘ ምውቅ ውእቱ ነሣእናሁ እምአብያቲነ በዕለተ ወፃእነ ከመ ንምፃእ ኀቤክሙ ወይእዜሰ ነቅዘ ወየብሰ ።

እነሆ ይህ እንጀራችን ወደናንተ እንመጣ ዘንድ ከቤታችን በወጣንበት ቀን ትኩሱን የያዝነው አሁን ግን ሻገተ ደረቀ ።

፲፫ ወዝንቱኒ ዝቁ ወይን ዘመላእናሁ ሐዲስ ይእዜሰ ዐርቀ ወበልየ ወተሠጠ ፥ ወዝንቱ አልባሲነ ወአሣእኒነ በልየ እስመ ጥቀ ርኁቅ ፍኖትነ ።

ይህም የወይናችን ረዋት አዲሱን መላነው አሁን ግን ተራቈተ አርጅቶም ተቀደደ ፥ መንገዳችን እጅግ የራቀ ነውና ይህም ልብሳችን አዲሱን ለብሰነው ፥ ይህም ጫማችን አዲሱን ተጫምተነው አረጀ በሰ.ቸው አሉን አሉት ።

፲፬ ወነሥኡ መኳንንት ስንቆሙ ወኢተስእሉ በኀበ እግዚአብሔር ።

መኳንንቱም ስንቃቸውን ተቀብለው አዩ ፥ የእግዚአብሔርንም ቃል አልጠየቁም ። ዘኍ ፳፯ ፳፩ ።

፲፭ ወገብረ ኢያሱ ሰላመ ምስሌሆሙ ወተማሐለ ምስሌሆሙ ከመ ያድኅኖሙ ወመሐሉ ሎሙ መላእክተ ተዓይን ።

ኢያሱም ከነሱ ጋራ ዕርቅ አድርጎ ያድናቸው ዘንድ ከነሱ ጋር ተማማለ ፥ የሕዝቡም አለቆች ማሉላቸው ።

፲፮ ወእምድኅረ ሠሉስ መዋዕል እምድኅረ ተማሐሉ ምስሌሆሙ መሐላ ሰምዑ ከመ እምቅሩብ እሙንቱ ወከመ ኀቤሆሙ እሙንቱ ይነብሩ ።

ከነሱ ጋር መሐላን ከተማማሉ ከሦስት ቀን በኋላ ከቅርብ (ጐረቤታቸው) እንደሆኑ እነዚያም በአጠገባቸው እንደሚኖሩ ሰሙ ።

፲፯ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወበጽሑ ውስተ አህጉሪሆሙ አመ ሣልስት ዕለት ወአላንቱ አማንቱ አህጉሪሆሙ ገባኦን ፥ ወፌራ ፥ (ፋራ) ወቤሮት ፥ ወኢያርም ።

የእስራኤልም ልጆች ተጕዘው በሦስተኛው ቀን ወደ አገራቸው ደረሱ ፥ እነዚያም አገሮች ገባኦን ፋራን ቤሮት ኢያርም ናቸው ። ኢያ፥ ፲፰ ፳፭ ። ሕዝ፥ ፱ ፳፭ ።

፲፰ ወኢቀተልዎሙ ደቂቀ እስራኤል እስመ መሐሉ ሎሙ ኵሎሙ መላእክተ ተዓይን በእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወአንጐርጐሩ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ላዕለ ኵሉ መላእክቲሆሙ ።

የሕዝቡም አለቆች ሁሉ በእስራኤል ፈጣሪ ስም ምለዉላቸዋልና የእስራኤል ልጆች አልወጉዋቸውም ፥ የእስራኤል ልጆች ወገኖችም ሁሉ በአለቆቻቸው ሁሉ ላይ አንጐራጐሩ ።

፲፱ ወይቤልዎሙ ኵሉ መላእክት ለኵሉ ተዓይን ንሕነ መሐልነ ሎሙ በእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወይእዜኒ ኢንክል ለኪሮቶሙ ወኢ.ቦምንትኒ ።

አለቆቻቸውም ሁሉ ሕዝቡን ሁሉ እኛ በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ስም ምለንላቸዋል ፥ አሁንም ምንም ምን ልንነካቸው አንችልም አሉዋቸው ።

፳ ወከመዝ ባሕቱ ንግበር ናሕይዎሙ ወንቅንዮሙ ወኢ.ይከውን ላዕሌነ መንሱት በበይነ ዘመሐልነ ሎሙ ።

ነገር ግን እንዲህ እናድርግ ፥ ስለ ማልንላቸው አድነን እንግዛቸው ስለ ማልንላቸውም መቅሠፍት አይደረግብንም ፤

፳፩ ወይቤልዎሙ መላእክት አሕይውኖሙ ወሜምኖሙ ትሕጥቡ ዕፀወ ፥ ወትቅድሑ ማየ ፥ ለኵሉ ተዓይን ፥ ወከመዝ አዘዝዎሙ መላእክት ።

አለቆቹም ለሰፈሩ ሁሉ ውኃ እንድትቀዱ ፥ ዕንጨት እንድትሰብሩ አድነን እኖርናችሁ አለቆቹ እንዲህ አድርገው አዘዟቸው ። ኢያ፥ ፱ ፳፫ ፥ ፱ ፲፭ ።

፳፪ ወጸውዖሙ ኢያሱ ወይቤሎሙ ለምንት ተማለቅሙ ላዕሌነ ወትቤሉነ ርኁቃን ንሕነ ጥቀ እምኔክሙ ፥ ወናሁ አንትሙ ትነብሩ ውስቴትነ ።

ኢያሱም ጠርቶ ከናንተ እጅግ የራቅን ነን ብላችሁ ለምን ዘበታችሁብን እነሆ እናንተ በጠገባችን ትኖራላችሁ እንዲህ ስትሆኑ ለምን ዘበታችሁብን ፤ አላቸው ።

፳፫ ወይእዜኒ ርጉማን ኩኑ ወኢ.ይሰዐር እምኔክሙ ገብር ዘየሐጥብ ዕፀ ወዘይቀድሕ ማየ ለአምላኪየ ወሊ.ተኒ ።

አሁንም የተረገማችሁ ሁኑ ለኔና ለፈጣሪዬ ውኃ የሚቀዳና ዕንጨት የሚሰብር አገልጋይ ከናንተ አይታጣ አላቸው።

፳፬ ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ዜና ዜነዉነ ኵሎ ዘይቤሎ እግዚአብሔር አምላክከ ለሙሴ ቍልዔሁ ከመ የሀብክሙ ዘተ ምድረ ወከመ ያጥፍእነ ለነ ወለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ እምቅድመ ገጽክሙ ወበበይነዝ ገበርነ ዘንተ ነገረ ።

እነሱም እንዲህ ብለው መለሱለት ፥ ይህችን ምድር ይሰጣችሁ ዘንድ እኛንም ያጠፋን ዘንድ በውስጧ የሚኖሩ ሰዎችንም ሁሉ ከፊታችሁ ያጠፋቸው ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር ለወዳጁ ለሙሴ የነገረውን ነገር ሁሉ ነገሩን ስለዚህ ይህን ነገር አደረግን ። ዘፀ፥ ፲፰ ፲፬ ።

፳፭ ወይእዜኒ ናሁ ንሕነ ውስተ እዴክሙ ዘከመ ፈቀድክሙ ወዘከመ ይኤድመክሙ ትረስዩነ ረስዩነ ።

አሁንም እነሆ እኛ በእጃችሁ ነን እንደ ወደዳችሁ ደስ እንደሚላችሁም ታደርጉን ዘንድ አድርጉን አሉት ።

፳፮ ወአድኅኖሙ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ወረሰዮሙ ሐጣብያነ ዕፀው ወሐዋርያነ ማይ ለምሥዋዐ እግዚአብሔር ወለኵሉ ተዓይን ።

ኢያሱም በዚያች ቀን አዳናቸው ለሰፈሩ ሁሉና ለእግዚአብሔርም መሠውያ ውኃ ቀጅና ዕንጨት ሰባሪ አደረጋቸው ። ፩ ዜና መ፥ ፱ ፪ ። ዕዝ፥ ፪ ፵፫ ።

፳፯ ወበበይነ ዝንቱ ኮኑ ሰብአ ገባኦን ሐጣብያነ ዕፀው ፥ ወሐዋርያነ ማይ ለኵሉ ተዓይን ወለምሥዋዐ እግዚአብሔር እስከ ዛቲ ዕለት ።

ስለዚህም ነገር የገባኦን ሰዎች ለሰፈሩ ሁሉና ለእግዚአብሔር መሠውያ ዕንጨት ሰባሪዎችና ውኃ ቀጂዎች ሆኑ ።

## ምዕራፍ ፲ ።

፩ ወሰበ ሰምዐ አዶንቤዜቅ ንጉሠ ኢየሩሳሌም ከመ ነሥአ ኢያሱ ለጋይ ወአጥፍኣ በከመ ገብራ ለኢያሪኮ ወለንጉሣ ወከመ ለሊሆሙ ሖሩ ሰብአ ገባኦን ኀበ ኢያሱ ወኀበ

የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶንቤዜቅ ፥ ኢያሱ ኢያሪኮን እንዳጠፋት ንጉሧንም እንዳጠፋው ፥ ጋይንም እጅ እንደ አደረጋት የገባኦን ሰዎችም ወደ እስራኤልና ወደ ኢያሱ

እስራኤል ወገረሩ ሎሙ ወነበሩ ማእከሎሙ፤ ፈርሁ እም
ኔሆሙ ጥቀ።

ሂደው በፊታቸው ተገዝተው በመካከላቸው እንደ ኖሩ
በሰማ ጊዜ ከነው የተነሣ ፈጽሞ ፈራ።

፪ እስመ የአምር ከመ ዐበይ ሀገር ይእቲ ጥቀ ገባኦን
በከመ አሐቲ እምአህጉረ መንግሥት እስመ ይእቲ ተዐ
ቢ እምጋይ፤ ወጽኑዓን እሙንቱ ኵሎሙ እደዊሃ።

ገባኦን ከሚገዙቸው አገሮች እንደ አንዲቱ አገር እጅ
ግ ታላቅ አገር እንደ ሆነች ያውቅ ነበርና ከጋይም ትበ
ልጥ ነበርና ሰዎቿም ሁሉ አርበኞች እንደ ነበሩ ያውቅ
ነበርና። ዘዳ፥ ፲፩ ፳፫።

፫ ወለአከ አዶንቤዜቅ ንጉሠ ኢየሩሳሌም ኀበ ኤላም
ንጉሠ ኬብሮን ወኀበ ፌዶን ንጉሠ ኢያሬሞት ወኀበ ያፍ
ታ (ዮፍታሔ) ንጉሠ ለኪስ ወኀበ ዳቤር ንጉሠ አዶላም።

የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶንቤዜቅም ወደ ኬብሮን ንጉ
ሥ ወደ ኤላም፤ ወደ ኢያሬሞት ንጉሥ ወደ ፌዶን ወደ
ዳቤርና ወደ ለኪስ ንጉሥ ወደ ያፍታ (ዮፍታሔ) ላከ።

፬ ወይቤሎሙ ንዑ ኀቤየ ወርድኡኒ ከመ ንፅባእሙ ለገ
ባኦን እለ ገብኡ ለሊሆሙ ኀበ ኢያሱ ወኀበ ደቂቀ እስ
ራኤል።

በፊታቸው ወደ እስራኤልና ወደ ኢያሱ የገቡ የገባ
ኦንን ሰዎች እንወጋቸው ዘንድ ወደኔ መጥታችሁ ር
ዱኝ አላቸው። ዘፍ፥ ፳፫ ፫-፲።

፭ ወተጋብኡ ወዐርጉ እሉ ኀምስቱ ነገሥተ አሞሬዎን
ንጉሠ ኢየሩሳሌም፤ ወንጉሠ ኬብሮን፤ ወንጉሠ ኢያሬ
ሞት፤ ወንጉሠ ለኪስ፤ ወንጉሠ አዶላም፤ ወበጽሑ እሙ
ንቱኒ ወኵሎሙ አሕዛቢሆሙ ወዐገትዋ ለገባኦን ወተቃ
ተልዋ።

የኬብሮን ንጉሥና የኢየሩሳሌም ንጉሥ የለኪስና የኢ
ያሬሞት ንጉሥ፤ የአዶላምም ንጉሥ፤ እሊህ አምስቱ የአ
ሞሬዎን ነገሥታት ተሰብሰበው ዘመቱ፤ እነሱም ሠራዊቶ
ቻቸውም ሁሉ ደርሰው ከብበው ተዋጓት።

፮ ወለአኩ ሰብአ ገባኦን ኀበ ኢያሱ ውስተ ትዕይንተ
እስራኤል ውስተ ገልገላ፤ ወይቤሉ ኢትትሀከይ እዴከ
በእንተ አግብርቲከ ዕርግ ኀቤነ ወፍጡነ ርድአነ ወአድኅ
ነነ እስመ ተጋብኡ ላዕሌነ ኵሎሙ ነገሥተ አሞሬዎን እለ
ይነብሩ ውስተ አድባር።

በደጋ የሚኖሩ የአሞሬዎን ነገሥታት ሁሉ በኛ ላይ
ተሰብስበዋልና ስለኛ ስለባሮችህ ሥልጣንህ ቸል አትበል
ወደኛ መጥተህ ፈጥነህ ርዳን አድነን ብለው ከእስራኤል
ወገኖችና ከኢያሱ ዘንድ ወደ ገልገላ ላኩ።

፯ ወዐርገ ኢያሱ እምገልገላ ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ መስ
ተቃትላን ምስሌሁ ወኵሉ ዘጽኑዕ ኀይሉ።

እሱ ኢያሱም ከገልገላ ወጣ፤ ኃይሉ ጽኑ የሆነው ሁሉ
ከሱም ጋር የአርበኞች ወገኖች ሁሉ ወጡ።

፰ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ኢትፍርሆሙ እስመ
ውስተ እዴከ አገብኦሙ ወአልበ ዘይተርፍ እምኔሆሙ
ቅድሜከሙ ወኢ አሐዱ።

እግዚአብሔርም ኢያሱን በእጅህ እጥላቸዋለሁና በፊ
ታችሁም አንድ ስንኳ ከነሱ የሚቀር የለምና አትፍራ
ቸው አለው። ኢያ፥ ፲፩ ፯። መሳ፥ ፬ ፲፬።

፱ ወበጽሖሙ ኢያሱ ግብተ በሌሊት ወዒአ እምገልገላ።

ኢያሱም ከገልገላ ወጥቶ ሲገሠግሥ አድሮ ድንገት
በሌሊት ደረሰባቸው።

፲ ወአደንገፆሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጸሙ ለእስ
ራኤል ወቀጥቀጦሙ እግዚአብሔር ዐቢየ ቅጥቃጤ በገባ
ኦን ወጐዩ ውስተ ፍኖተ ምዕራገ ቤቶሮን ወዴገንዎሙ
ወወግእዎሙ እስከ አዜቃ ወእስከ መቄዳ።

ከእስራኤልም ፊት የተነሣ እግዚአብሔር አስደነገጣ
ቸው በገባኦን ብርቱ ጥፋት አጠፋቸው፤ ወደ ቤቶሮን ዓቀ
በት መንገድም ሸሹ፤ ተከትለውም እስከ መቄዳና እስከ
አዜቃ ድረስ ወጉዋቸው። ኢያ፥ ፲፫ ፴፩። መሳ፥ ፬ ፲፭።

፲፩ ወሶበ ነትዑ እምቅድመ ገጸሙ ለደቂቀ እስራኤል
በውስተ ሙራዲሁ ለቤቶሮን ወገሮሙ እግዚአብሔር እም
ሰማይ በእብነ በረድ እስከ አዜቃ ወፈድፈዱ እለ ሞቱ በእ
ብነ በረድ እምእለ ቀተሉ ደቂቀ እስራኤል በሐፂኖሙ
በውስተ ቀትል።

ከእስራኤል ልጆች ፊት የተነሣም ወደ ቤቶሮን ቊል
ቊለት በሸሹ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ አውርዶ በደን
ጊያ በረዶ እስከ ዓዜቃ ድረስ መታቸው፤ የእስራኤል ልጆ
ች በሰልፍ በጦራቸው ከገደሉዋቸውም በደንጊያ በረዶ
የሞቱ በዙ። መዝ፥ ፲፰ ፲፪። ራእ፥ ፲፮ ፳፩።

፲፪ ወይእተ አሚረ ተናገረ ኢያሱ ምስለ እግዚአብሔር
አመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ለአሞሬዎን ውስተ እዴ
ሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፤ ወይቤ ኢያሱ ለትቁም ፀሐይ
መንገለ ገባኦን፤ ወወርኅኒ መንገለ ቈላተ ኤሎም።

እግዚአብሔር አሞሬዎንን በእስራኤል ልጆች እጅ
በጣላቸው ጊዜ ኢያሱ ያን ጊዜ ፀሐይ በገባኦን ጨረቃም
በኤሎም ቈላ ትቁም ብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ፤
(ትቁም ብሎ አመነው)። ኢያ፥ ፲፱ ፶፪። እንባ፥ ፫ ፲፩።

፲፫ ወቆሙ ፀሐይ ወወርኅ በምቅዋሞሙ በኀበ ሀለዉ
እስከ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር ለፀሮሙ፤ ወናሁ ተጽሕፈ
ዝንቱ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ በጊዜሃ፤ ወቆመት ፀሐይ
ማእከለ ሰማይ ወኢሖረት መንገለ ምዕራብ እምጣነ አሐቲ
ዕለት ፍጽምት።

እግዚአብሔርም ጠላቶቻቸውን እስኪያጠፋቸው ድረ
ስ ፀሐይና ጨረቃ በያሉበት ቆሙ፤ ወድያውም ይህ ነገር
በዚህ መጽሐፍ ተጻፈ፤ በሰማይ መከከል ፀሐይ ቆመች፤
አንድ ቀን ያህል ፈጽሞ ወደ መግቢያዋም አልሄደችም።
፪ ሳሙ፥ ፩ ፲፰።

፲፬ ወኢኮነት ከመ ይእቲ ዕለት ኢ እምቅድሜሃ፤ ወኢ
እምድኅሬሃ ከመ ያውሥእ እግዚአብሔር ለቃለ እጓለ እመ

እግዚአብሔር የሰውን ጸሎቱን ይሰማው ዘንድ ከሷ
ም በፊት ከሷም በኋላ እንደዚህ የተደረገበት ቀን የለም

ሐያሙ ወእግዚአብሔር ፀብአ ሎሙ ለእስራኤል ።
፲፭ ወገብኡ ዳግመ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ ውስተ ገልገላ ትዕይንቶሙ ።
፲፮ ወጐዩ እልክቱ ኀምስቱ ነገሥት ወተኀብኡ ውስተ በዓት ዘመቄዳ ።
፲፯ ወዜነውዎ ለኢያሱ ወይቤልዎ ተረክቡ እልክቱ ኀምስቱ ነገሥት ውስተ በዓተ መቄዳ ኅበ ተኀብኡ ።
፲፰ ወይቤሎሙ ኢያሱ አንከባልሉ እብነ ዐቢየ ውስተ አፉሃ ለይእቲ በዐት ወእንብሩ አደወ ላዕሌሆሙ እለ የዐቅብዎሙ ።
፲፱ ወአንትሙሰ ኢትቁሙ ዴግኑ ፀሮሙ ኵሎ እስከ ጽንፎሙ ወኢታብሕዎሙ ይባኡ ውስተ አህጉሪሆሙ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ።

፳ ወእምዝ ሶበ አኅለቁ ቀቲሎቶሙ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ቀትለ ዐቢየ ጥቀ ዘእልቦ ማኅለቅት ወእለሂ ድኅኑ እምኔሆሙ ቦኡ ውስተ አህጉር ጽኑዓት ።
፳፩ ወገብኡ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ትዕይንት ኅበ ኢያሱ ውስተ መቄዳ ድኅኖናሂሆሙ ወአልቦ ዘለሐሶሙ በልሳኑ መኑሂ ለደቂቀ እስራኤል ።
፳፪ ወይቤሎሙ ኢያሱ አርኅውዋ ለዛቲ በዓት ወአምጽእዎሙ ኀቤየ ለእልክቱ ኀምስቱ ነገሥት እምዛቲ በዓት ወገብሩ ከማሁ ።
፳፫ ወአውፅእዎሙ ለእልክቱ ኀምስቱ ነገሥት እምውስተ ይእቲ በዓት ለንጉሠ ኢየሩሳሌም ፡ ወለንጉሠ ኬብሮን ፡ ወለንጉሠ ኢያሪሙት ፡ ወለንጉሠ ለኪሶን ወለንጉሠ አዶላም ፡ ወወሰድዎሙ ኅበ ኢያሱ ።
፳፬ ወጸውዖሙ ኢያሱ ለኵሉ እስራኤል እለ ተቃተሉ ወለእለ ሖሩ ምስሌሁ ወይቤሎሙ ደዩ እገሪክሙ ላዕለ ክሳዳቲሆሙ ፡ ወወደዩ እገሪሆሙ ላዕለ ክሳዳቲሆሙ ።
፳፭ ወይቤሎሙ ኢያሱ ኢትፍርህዎሙ ወኢትደንግፁ እምኔሆሙ ትብዑ ወጽንዑ እስመ ከመዝ ይገብሮሙ እግዚአብሔር ለኵሎሙ ፀርክሙ እለ ትፀብእዎሙ አንትሙ ።
፳፮ ወእምዝ ቀተልዎሙ ወረገዝዎሙ ወሰቀልዎሙ ላዕለ ኀምስቱ ዕፀው ወነበሩ ስቁላኒሆሙ እስከ ሠርክ ።
፳፯ ወእምዝ ሶበ ዐርበ ፀሐይ አዘዘ ኢያሱ ያውርድዎሙ ወአውረድዎሙ እምዕፀው ወገደፍዎሙ ውስተ ይእቲ በዐት እንተ ውስቴታ ተኀብኡ ወአንከባልሉ እብነ ዓቢየ ዲቤሃ ለይእቲ በዐት ።
፳፰ ወለመቄዳሂ ነሥእዋ በይእቲ ዕለት ወለንጉሣሂ ቀተልዎ በአፈ ሐጺን ወአጥፍእዎሙ ለኵሉ ዘመንፈስ ዘውስቴታ ወኢያትረፉ በውስቴታ ነፋሴ ወኢመነሂ ወአልቦ ዘድኅነ ወገብርዎ ለንጉሠ መቄዳ በከመ ገብርዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ።
፳፱ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ እመቄዳ ውስተ ልብና ወተቃተላ ለልብና ።
፴ ወአግብኣ እግዚአብሔር ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወነሥእዋ ወለንጉሣ ቀተልዎ በአፈ ሐጺን ወኢያትረፈ ውስቴታ እምኵሉ ዘመንፈስ ወኢያድኅኑ ወኢአሐደሂ ነፋሴ

እግዚአብሔር ለእስራኤል ጠላቶቻቸውን አጠፋላቸው ።
ዳግመኛ እስራኤል ሁሉና ኢያሱ ወደ ሰፈራቸው ወደ ገልገላ ተመለሱ ። ኢያ፡ ፲፯ ፹፫ ።
እሊህም አምስቱ ነገሥታት ሸሽተው በመቄዳ ዋሻ ተሠወሩ ። ኢያ፡ ፲ ፲ ።
እሊህ አምስቱ ነገሥታት በተሰበሰቡበት በመቄዳ ዋሻ ተገኙ ብለው ለኢያሱ ነገሩት ።
ኢያሱም ታላቁን ደንጊያ በዚያች ዋሻ አፍ ገጠሟት የሚጠብቋቸውንም ጕልማሶች በዚ ላይ አስቀምጡ ። ነህ፡ ፬ ፳ ፡ መዝ፡ ፴፫ ፳ ፡ ፲፪ ፳ ።
እናንተ ግን ትቆሙ ፡ ጠላቶቻችሁን ሁሉ እስከ ዳር ቻቸው ድረስ ተከተሉ ፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በእ ጃችን ጥሏቸዋልና ወደገራቸው ይገቡ ዘንድ አታሰናብቷቸው አላቸው ። ዘዳ፡ ፳፭ ፲፰ ።
ከዚህ በኋላ ፍጻሜ የሌለው እጅግ ጽኑ ሰልፍ አድርገው ኢያሱና እስራኤል ሁሉ በጠፏቸው ጊዜ ከነዚህም የዳኑት ወደ ጽኑ አገሮች ገቡ ። ኢያ፡ ፰ ፳፱ ።
ሕዝቡም ሁሉ ኢያሱ ወዳለበት ወደ መቄዳ በደኅና ተመለሱ ፡ የእስራኤልንም ልጆች ማንም ማን ጥቂት መከራ ያመጣባቸው የለም ። ዘፀ፡ ፲፩ ፯ ።
ኢያሱም ያችን ዋሻ ከፍታችሁ እነዚያን አምስቱ ነገሥታት ከዚያች ዋሻ ወደኔ አምጧቸው አላቸው ፡ እን ዳላቸውም አደረጉ ።
የኬብሮንን ንጉሥና የኢየሩሳሌምን ንጉሥ የለኪስን ንጉሥና የኢያሪሙትን ንጉሥ ፡ የአዶላምም ንጉሥ እሊ ያን አምስቱ ንጉሦች ከዚያች ዋሻ አውጥተው ወደ ኢያሱ ወሰዷቸው ።
ኢያሱም ከሱ ጋር ወደ ጦርነት የሄዱትንና የተዋጉ እስራኤልን ሁሉ ጠርቶ እግር ከንገት አድርጋችሁ እሰሩ ዋቸው አላቸው ፡ እግር ከንገት አድርገው አሰሯቸው ።
ኢያሱ አትፍሩዋቸው ፡ ከነዚህም የተነሣ አትደንግጡ እናንተ የምትወጉዋቸው ጠላቶቻችሁን እግዚአብሔር እንደዚህ ያደርጋቸዋልና በርቱ ፡ ጽኑ አላቸው ።
ከዚህ በኋላ ወግተው ገድለው በአምስት ዕንጨቶች ላይ ሰቀሏቸው ፡ እስከ ማታም ድረስ ተሰቅለው ዋሉ ።
ከዚህ በኋላ ፀሐይ በገባ ጊዜ ያወርዷቸው ዘንድ ኢያሱ አዘዘ ፡ ከዕንጨቶቹም ላይ አውርደው በተሸሸጉበት በዚያች ዋሻ ጣሏቸው ያችንም ዋሻ ታላቅ ደንጊያ ገጠሟት ። ዘዳ፡ ፳፯ ፳፫ ። ኢያ፡ ፰ ፳፱ ።
በዚያችም ቀን መቄዳን እጅ አደረጓት ፡ ንጉሧንም በጦር ገደሉት ፡ በውስጧም የወንድ አካል ያላቸውን ሁሉ አጠፏቸው ፡ በውስጧ የተሸሸጉትንም ሳላስቀሩም ማንም የዳነ የለም ፡ በኢያሪኮ ንጉሥ እንዳደረጉ በመቄዳም ንጉሥ አደረጉ ። ዘኍ፡ ፳፭ ፴፭ ። ኢያ፡ ፰ ፳፱ ፡ ፲፩ ፳ ።
ኢያሱ ሄደ እስራኤልም ሁሉ ከሱ ጋራ ከመቄዳ ወደ ልብና ሄደው ፡ ልብናን ወጉዋት ። ኢያ፡ ፲፪ ፲፭ ።
እግዚአብሔርም በእስራኤል እጅ ጣላት ፡ እጅም አደረ ጉዋት ፡ ንጉሷንም በጦር ገደለው ፡ በውስጧም የወንድ አካል ካለው ሁሉ አላስቀሩም ፡ ከነሱም አንድ ሰንኳ ሸሽቶ

እምኔሆሙ ፤ ወገብርዎ ለንጉሣ በከመ ገብርዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ።

ያመለጠ የለም ፤ በኢያሪኮም ንጉሥ እንዳደረጉ በንጉሧም አደረጉ (አጠፉት) ። ኢ.ሱ፡ ፴፯ ፳ ።

፴፩ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ እምልብና ውስተ ለኪስ ወነበሩ ላዕሌሃ ወተቃተልዋ ።

ኢያሱም ሄደ ከሱ ጋር ያሉ እስራኤልም ሁሉ ከልብና ወደ ለኪስ ሄዱ በላዩዋም ላይ ተቀምጠው ወጉዋት ።

፴፪ ወአግብኣ እግዚአብሔር ለለኪስ ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወነሥእዋ በሳኒታ ዕለት ወቀተልዎሙ በአፈ ሐፂን ወአጥፍእዋ በከመ ገብርዋ ለልብና ።

እግዚአብሔር ለኪስን በእስራኤል እጅ ጣላት በማግሥቱም እጅ አደረጓት ፤ በጦርም አጠፉዋቸው ፤ ልብናን እንዳጠፉዋት እሷንም አጠፉዋት ።

፴፫ ወዐርገ ይእተ አሚረ ኤላም ንጉሠ ጋዜስ ከመ ይርአያ ለለኪስ ወቀተሎ ኢያሱ በአፈ ሐፂን ወለሕዝቡሂ እስከ ኢያትረፈ እምኔሆሙ ነፋጺተ ወአልቦ ዘድኅነ ።

ያን ጊዜ የጋዜስ ንጉሥ ኤላም ለኪስን ለማየት ወጣ ፤ ኢያሱም በጦር ወግቶ ገደለው ፤ ከነዚያ ሸሽቶ ያመለጠ አንድ ስንኳ ሳይቀር ወገኖቹን ሁሉ ገደላቸው የዳነም የለም ።

፴፬ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ እምለኪስ ውስተ አዶላም ወነበሩ ላዕሌሃ ወተቃተልዋ ።

ኢያሱ ሄደ ፤ እስራኤልም ሁሉ ከሱ ጋር ከለኪስ ወደ አዶላም ሄዱ ፤ በሷም ላይ ሰፍረው ተዋጓት (ወጓት) ።

፴፭ ወአግብኣ እግዚአብሔር ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወነሥእዋ በይእቲ ዕለት ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ወቀተሉ ኵሎ ዘመንፈስ ዘውስቴታ በከመ ገብርዋ ለለኪስ ።

እግዚአብሔርም በእስራኤል እጅ ጣላት ፤ በዚያችም ቀን በጦር ወግተው እጅ አደረጓት ፤ ለኪስንም እንዳደረጓት በውስጧ ያለ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ ገደሉ ።

፴፮ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ እምአዶላም ውስተ ኬብሮን ወነበሩ ላዕሌሃ ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ወለኵሉ ዘመንፈስ ዘውስቴታ ወአልቦ ዘድኅነ እምኵሉ ዘውስቴታ ወአጥፍእዋ በከመ ገብርዋ ለአዶላም ።

ኢያሱም ሄደ ፤ እስራኤልም ሁሉ ከሱ ጋር ከአዶላም ወደ ኬብሮን ሄደው ፤ በሷ ላይ ተቀምጠው በጦር ወግተው አጠፉዋት ፤ በውስጧ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ አጠፉት ፤ የዳነም የለም ፤ አዶላምን እንዳጠፉዋት እሷንም አጠፉዋት ።

፴፯ ወገብአ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ውስተ ዳቤር ወነበሩ ላዕሌሃ ።

ኢያሱም ተመለሰ ፤ እስራኤልም ሁሉ ከሱ ጋር ወደ ዳቤር ተመለሱ ፤ በሷም ላይ ተቀመጡ ።

፴፰ ወነሥእዋ ወቀተልዋ ለንጉሣ በአፈ ሐፂን ወለአህጉሪሃ ወለኵሉ ዘመንፈስ ዘውስቴታ ወአልቦ ዘአትረፉ ውስቴታ ዘድኅነ ወአጥፍእዋ በከመ ገብርዋ ለኬብሮን ወለንጉሣ ከማሁ ገብርዋ ለዳቤር ወለንጉሣ ።

እጅ አደረጓት ፤ ንጉሧንም በጦር ወግተው ገደሉት ፤ አገሮቿንም አጠፉዋቸው በውስጧ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ አጠፉት ፤ በውስጧ ያስቀሩት የዳነም የለም ፤ ኬብሮንን ከንጉሧ ጋር እንዳጠፍዋት ዳቤርንም ከንጉሧ ጋር አጠፏት ።

፵ ወቀተለ ኢያሱ ኵሎ ምድሮሙ ለደወለ አድባር ወናቤ ወለአሕቃላቲሃ ወለአሴዶት ወነገሥቶሙ ወአልቦ ዘተርፈ እምኔሆሙ ወዘድኅነ ወኵሎ ዘመንፈስ ሕይወት አጥፍአ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ።

ኢያሱ የናቤዎንና የደጋዎችን አውራጃ አሴዶትንና አውራጃዎቿን ንጉሦቻቸውንም አጠፋ ፤ ከነዚያ የቀረ የዳነ የለም ፤ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዳዘዘ በነፍስ ሕያው የሆነውን ሰው ሁሉ አጠፋ ። ዘዳ፡ ፳ ፲፮ - ፲፯ ።

፵፩ ወቀተሎሙ ኢያሱ እምቃዴስ በርኔ እስከ ጋዛስ ወኵሎ ጎሶም እስከ ገባኦን ።

ኢያሱ ከቃዴስ በርኔ ጀምሮ እስከ ጋዛስ ድረስ ከጎሶም ጀምሮም እስከ ገባኦን ድረስ አጠፋቸው ።

፵፪ ወቀተለ ኢያሱ ኵሎ ነገሥቶሙ ወምድሮሙሂ አኀዘ በምዕር እስመ እግዚአብሔር ይፀብእ ሎሙ ለእስራኤል ።

ኢያሱ ንጉሦቻቸውን ሁሉ አጠፋ ፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ጠላቶቻቸውን ስላጠፋላቸው አገራቸውን በአንድ ጊዜ ያዘ ። ኢያ፡ ፲ ፲፬ ።

፵፫ ወገብአ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ ኀበ ትዕይንት ውስተ ገልገላ ።

ከዚህ በኋላ ኢያሱ ተመለሰ ፤ ከሱ ጋር ያሉ እስራኤልም ሁሉ ገልገላ ወዳለው ሰፈራቸው ተመለሱ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ወሰበ ሰምዐ ኢያቢስ ንጉሠ አሶር ለአከ ኀበ ኢዮባብ ንጉሠ አምሮን ወኀበ ንጉሠ ሲሞኦን ወኀበ ንጉሠ አዜፍ ።

የአሶር ንጉሥ ኢያቢስ የኢያሱን መምጣት በሰማ ጊዜ ፤ ወደ ሲሞኦን ንጉሥና ወደ አምሮን ንጉሥ ወደ ኢዮባብ ወደ አዜፍም ንጉሥ ላከ ። ኢያ፡ ፲፪ ፲፱ ።

፪ ወኀበ ነገሥት እለ መንገለ መስዕ እንተ ውስተ አድባር ወውስተ ዐረባ ዘአዜብ በቅድመ ኬኔሬት ወውስተ አሕቃላት ዘፌናዶር ።

በአዜብ ኬኔሬት ግራና በደጋ ቀኝ አገር ወደ ሚኖሩ ነገሥታት ወደ ፌናዶር አውራጃዎች ላከ ።

፫ ወውስተ ባሕር ዘአሞሬዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ወፌርዜዎን እለ ውስተ አድባር ወኬጤዎን እለ ውስተ አሕቃላት ወውስተ መሴውማን ።

ወደ ኤዌዎንና ወደ አሞሬዎን ፤ በደጋ ወዳሉ ወደ ፌርዜዎንና ወደ ኢያቡሴዎን በሴውማንና በአውራጃዎ ወዳሉ ኬጤዎንም ምዕራብና ወደ ምሥራቅ ወዳሉ ወደ

ከነናን ምዕራብ ወዳሉ ነገሥታት ላከ። ሙሴ ፫ ፫ ።

፬ ወወፅኡ እሙንቱ ወተዕይንቶሙኒ ምስሌሆሙ ከመ ኆፃ ባሕር ብዝኆሙ ወአፍራስ ወሠረገላት ብዙኃን ጥቀ ።

እነሱም (ነገሥታቱ) ወጡ ሠራዊቶቻቸውም ከነሱ ጋር ብዛታቸው እንደ ባሕር አሸዋ ሁነው ወጡ፤ ሠረገላዎቻቸውና ፈረሶቻቸውም እጅግ ብዙ ነበሩ ።

፭ ወተጋብኡ ኵሎሙ ነገሥት ወመጽኡ ኅቡረ ወተአኅዝዎሙ ይትቃተልዎሙ ለእስራኤል በኀበ ማየ ማሮን ።

እነዚህም ነገሥታት ሁሉ ተሰብስበው እስራኤልን ለመውጋት መጥተው በማሮን ውኃ አጠገብ ተያያዟቸው ።

፮ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ኢትፍራህ እምቅድሜሆሙ እስመ ጌሠመ በዛቲ ጊዜ አነ አገብኦሙ ከመ ይትቃተሉ በቅድመ እስራኤል ወለአፍራሲሆሙኒ ምትር ሥረዊሆሙ ወሠረገላቲሆሙኒ አውዒ በእሳት ።

እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤል ፊት ይሞቱ ዘንድ ነገ ይህን ጊዜ እኔ በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና ከፊታቸው የተነሣ አትፍራ፤ የፈረሶቻቸውንም ቋንጃ ቊረጥ፤ ሠረገላዎቻቸውንም በእሳት አቃጥል አለው ። ዘፍ፡ ፵፱ ፮ ።

፯ ወሖረ ኢያሱ ወኵሎሙ ሕዝብ መስተቃትላን ላዕሌሆሙ ኀበ ማየ ማሮን ወወረዱ ላዕሌሆሙ እምአድባር ወአውገብዎሙ ።

አርበኞች የሚሆኑ ሠራዊቱ ሁሉና ኢያሱም ወደ ማሮን ውኃ ሄዱባቸው (መጡባቸው) ከተራራውም ወደሳቸው ወርደው አስፈሯቸው ።

፰ ወአግብኦሙ እግዚአብሔር ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወዴገንዎሙ እንዘ ይቀትልዎሙ እስከ ሲዶና ዐባይ ወእስከ ማሴሮን ወእስከ አሕቃላተ ሞሳሕ ዘመንገለ ጽባሒሁ ወቀተልዎሙ ወኢያትረፉ እምኔሆሙ ነፍሰ ።

እግዚአብሔርም በእስራኤል እጅ ጣላቸው፤ እስከ ታላቂቱ ሲዶና እስከ ማሴሮንም ድረስ በስተ ምሥራቅ በኩል እስከለ እስከ ሞሳሕ አውራጃ ድረስ እየወጉ ተከትለው አጠፉዋቸው ከነሱም የሸሸውን ሰው አላስቀሩም ።

፱ ወገብሮሙ ኢያሱ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ወመተረ ሥረዊሆሙ ለአፍራሲሆሙ ወሠረገላቲሆሙኒ አውዐየ በእሳት ።

ኢያሱም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረጋቸው፤ የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ቈረጠ፤ ሠረገላዎቻቸውንም በእሳት አቃጠለ ።

፲ ወተመይጠ ኢያሱ በእማንቱ መዋዕል ወነሥኣ ለአሶር ወለንጉሣ ቀተሎ በሰይፍ እስመ አሶር ቀዲሙ ርእሰሙ ይእቲ ለእሉ ኵሎሙ ነገሥት ።

ኢያሱ በዚያ ወራት ተመልሶ አሶርን እጅ አደረጋት ንጉሧንም በሰይፍ ገደለው፤ አሶር ቀድሞ የነዚህ ነገሥታት ሁሉ ዋና ከተማ ነበረች ።

፲፩ ወቀተሉ ኵሎ ዘነፍስ ዘውስቴታ በሐፂን ወአጥፍእዎሙ ለኵሎሙ እስከ ኢያትረፉ ውስቴታ ዘመንፈስ ወአውዐያ ለአሶር በእሳት ወለኵሉ አህጉረ እሉ ነገሥት ።

በውስጧ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ በጦር አጠፉ፤ በውስጧ የወንድ አካል ካለው ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ አሶርን በእሳት አቃጠሏት፤ የእነዚህንም የንጉሦች አገር ሁሉ በእሳት አቃጠላቸው ።

፲፪ ወነሥኦሙ ኢያሱ ለነገሥቶሙ ወቀተሎሙ በሐፂን ወሠረዎሙ በከመ አዘዞ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ።

ኢያሱም ንጉሦቻቸውን ይዞ በጦር ገደላቸው የእግዚአብሔርም ብላቴና ሙሴ እንዳዘዘው አጠፋቸው ።

፲፫ ወባዕደሰ አህጉረ ኵሎ ዘአድያም ኢያውዐዩ እስራኤል እንበለ አሶር በሕቲታ ዘአውዐዩ ።

ከቃጠሏት ከአሶር ብቻ በቀር እስራኤል በአውራጃቸው ያለ ሌላውን አገር ሁሉ ግን አላቃጠሉም ።

፲፬ ወበርበሩ ደቂቀ እስራኤል ለርእሶሙ ኵሎ በርበረ ወሎሙሰ ሠረዎሙ እስከ አጥፍእዎሙ ለኵሎሙ በአፈ ሐፂን ወኢያትረፉ እምኔሆሙ ወኢ አሐደ ዘመንፈስ ።

የእስራኤል ልጆች ምርኮውን ሁሉ ለራሳቸው ዘረፉ፤ ሁሉንም በጦር እስኪያጠፉዋቸው ድረስ ደርሰው ሰዎችን ግን በጦር አጠፉዋቸው ከነሱ አንድ ሰው ስንኳን አላስቀሩም ።

፲፭ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ቍልዔሁ ወሙሴ አዘዞ ለኢያሱ ወከማሁ ገብረ ኢያሱ ወኢኀደገ ምንተኒ እምኵሉ ዘአዘዞ ሙሴ ።

እግዚአብሔር ለወዳጁ ለሙሴ እንዳዘዘው፤ ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው፤ ኢያሱ እንዳዘዘው አደረገ፤ ሙሴ ካዘዘው ሁሉ ምንም አላስቀረም ። ዘፀ፡ ፴፬ ፲፩ - ፲፪ ።

፲፮ ወነሥአ ኢያሱ ኵሎ ደወሊ ምድሮሙ ዘመንገለ አድባር ወኵሎ ምድረ አዴብ ወኵሎ ምድረ ጎሶም ወአሕቃላቲሆሙ ወዘመንገለ ዐረቢሃ ወለኵሉ ደብረ እስራኤል ወታሕታየኒ ደወሎሙ ዘመንገለ ደብር እምደብረ ኤኬል ።

ኢያሱ አዴብ የሚባል አገር ሁሉና በደጋው ያለ የአገራቸውን አውራጃ ሁሉ አውራጃቸውን ሁሉና ጎሶም የሚባል አገርን ሁሉ እጅ አደረገ፤ በምዕራብ በኩል ያለው የእስራኤል አገር ሁሉ ከኤኬል ተራራ በደጋው ያለ ታችኛውን አገር ሁሉም እጅ አደረገ ። ኢያ፡ ፲፪ ፰፤ ፲ ፵፩ ።

፲፯ ወየዐርግ እስከ ሴይር ወእስከ በለገድ ወአሕቃላተ ሊባኖስ ዘመንገለ ደብረ አኤርሞን ወአኀዞሙ ለኵሎሙ ነገሥቶሙ ወቀተሎሙ ወአጥፍኦሙ ።

እስከ በለገድና እስከ ሴይር ድረስ በአኤርሞን ተራራ በኩል ባለ እስከ ሊባኖስ አውራጃ ድረስ ወጥቶ ንጉሦቻቸውን ሁሉ ይዞ በጦር ወግቶ ገደላቸው ።

፲፰ ወጕንዱየ መዋዕለ ነበረ ኢያሱ ኀበ እሉ ነገሥት እንዘ ይትቃተሎሙ ።

ኢያሱ ከእነዚህ ነገሥታት ጋር ሲዋጋ ብዙ ዘመን ኖረ።

፲፱ ወአልቦ ሀገር እንተ ኢነሥኡ እስራኤል እንበለ ኤዋ
ውያን ዘይነብሩ በገባኦን ወለኵሎሙ ነሥእዎሙ በቀትል ።
እስራኤል በገባኦን የሚኖሩ ሰዎች ከያዙት በቀር እጅ
ያላደረጉት አገር የለም ። ኢያ፣ ፱ ፫ ፯ ።

፳ እስመ እግዚአብሔር አጽንዐ ልበሙ ውስተ ቀትል
ለእስራኤል ከመ ይሥርውዎሙ ወከመ ኢይምሐርዎሙ
አላ ከመ ያጥፍእዎሙ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ።
እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ያጠፏቸው ዘንድ
ነው እንጂ እንዳይራሩላቸው በሰልፍ ያጠፉዋቸው ዘንድ
የእስራኤልን ልቡናቸውን አጽንቷልና በሰይፍ አገሮቻቸ
ውን ሁሉ እጅ አደረጉዋቸው ።

፳፩ ወሐረ ኢያሱ በእማንቱ መዋዕል ወአጥፍኦሙ ለእ
ቂም እለ ውስተ አድባር እምኬብሮን ወእምዳቤር ወእምአ
ናብት ወእምውስተ ኵሉ ደወሎሙ ለእስራኤል ወእምአ
ድባረ ይሁዳ ምስለ አህጉሪሆሙ ።
ኢያሱም በዚያ ወራት ሂዶ በደጋዎች ያሉ ኃያላኑን
ከዳቤርና ከኬብሮን ከእስራኤል አውራጃ ሁሉና ከአናብት
ከይሁዳም አገር ከአገሮቻቸው ጋር አጠፋቸው ።

፳፪ ወአጥፍኦሙ ኢያሱ ወኢያትረፈ እምኔሆሙ ለአቂም
በማእከለ እስራኤል ዘእንበለ ውስተ ጋዛ ወውስተ ጌት
ወአዛጦን ዘተርፉ ።
ኢያሱ በጌትና በጋዛ በአዛጦንም ከቀሩት በቀር ኃያ
ላኑ (አቂም) በእስራኤል መካከል ሳያስቀር አጠፋቸው ።

፳፫ ወነሥአ ኢያሱ ኵሎ ምድሮሙ በከመ አዘዘ እግዚአ
ብሔር ለሙሴ ወወሀቦሙ ኢያሱ ርስቶሙ ለእስራኤል ዘከ
መ ክፍሎሙ በበነገዶሙ፣ ወአዕረፈት እንከ ምድር እም
ቀትል ።
እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው ኢያሱ አገራቸውን
ሁሉ እጅ አደረገ፣ ኢያሱም ለእስራኤል በየወገናቸው እን
ደየዕጣቸው ርስታቸውን ሰጣቸው፣ ከዚህ በኋላ ምድር
ከሰልፍ (ከጦርነት) አረፈች ። ዘኍ፣ ፴፬ ፪ ። ኢያ፣ ፲፬ ፩ ።

## ምዕራፍ ፲፪ ።

፩ ወእሉ እሙንቱ ነገሥት ዘቀተልዎሙ ደቂቀ እስራኤል
ወወረስዎሙ ምድሮሙ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ሠ
ርቀ ፀሐይ እምቈላተ አርኖን እስከ ደብረ አኤርሞን ወኵ
ሉ ምድረ ዐረባ ዘመንገለ ጽባሒሁ ።
ከአርኖን ቈላ ጀምሮ በምሥራቅ በኩል እስከለው ዓ
ረባ ምድር ሁሉና እስከ አኤርሞን ተራራ ድረስ በፀሐይ
መውጫ በዮርዳኖስ ማዶ የእስራኤል ልጆች ወግተው አገ
ራቸውን የወረሱዋቸው ነገሥታት እነዚህ ናቸው ።

፪ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ወይ
ኴንን እምአርኖን እንተ ሀለወት ውስተ ቈላት ዘእሐዱ ኅ
ብር ወመንፈቀ ገለአድ እስከ ኢያቦቅ ደወሎሙ ለደቂቀ
አሞን ።
በሐሴቦን የሚኖር አንድ ወገኑ ቈላ በሚሆን ካለች
ከአርኖን፣ ከገለዓድም እኩሌታ ጀምሮ የዓሬብና የዓሞን
ልጆች ድንበር እስከ ሚሆን እስከ ያቦቅ ድረስ የሚገዛ
ሴዎን ነው ። ዘፍ፣ ፴፪ ፳፪ ። ዘኍ፣ ፳፩ ፳፬ ።

፫ ወዐረበ እስከ ባሕረ ኬኔሬብ ዘመንገለ ጽባሕ እስከ
ባሕረ ዐረባ ባሕረ ኤሎን እምነ ጽባሒሁ እምፍናዊ ዘመ
ንገለ አሴሞት ወእምቴማን እንተ መትሕተ አሴዶት ፋ
ስጋ ወደወላ ።
በምሥራቅ በኩል እስከለ እስከ ኬኔሬብ ምዕራብም
ድረስ በአሴሞት ካለ በምሥራቁ መንገድ ጀምሮ ከፋስጋና
ከአሴዶት በአውራጃዋ በታች ካለች ከቴማን ጀምሮ ይኸ
ውም የጨው ባሕር ነው አውራጃዋንም እስከዚህ ድረስ
የሚገዛ ሴዎን ነው ። ዘኍ፣ ፴፬ ፲፩ ። ኢያ፣ ፲፫ ፳ ።

፬ ዓግ ንጉሠ ባሳን ዘተርፈ እምኔሆሙ ለእለ ያርብሕ እለ
ይነብሩ ውስተ አስጣሮት ወኤንድራይን ።
በኤንድራይንና በአስጣሮት ከሚኖሩ አርበኞች የቀረ
የባሳን ንጉሥ ዓግ ነው ። ዘፍ፣ ፲፬ ፭ ። ዘኍ፣ ፳፩ ፴፫ ።

፭ ወመስፍን ውእቱ ላዕለ አድባረ አኤርሞን ወከሴኪ
ወለኵሉ ባሳን እስከ አድዋለ ጌርጌሲ ወመከት ወመንፈቀ
ገለአድ ደወሉ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ።
በካሴኪና በአኤርሞን አውራጃ ገዥ ነው፣ እስከ መከ
ትና እስከ ጌርጌሲ የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎን አውራጃ እስከ
ገለዓድ እኩሌታ አውራጃም ድረስ ለባሳን ሁሉ ገዥ ነው።

፮ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ወደቂቀ እስራኤል
ቀተልዎሙ፣ ወወሀቦሙ ርስቶሙ ሙሴ ኪያሃ ምድረ
ለሮቤል ወለጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ።
የእስራኤል ልጆችና የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ
እነዚህን ገድለው ለጋድና ለሮቤል ለምናሴም ነገድ እኩ
ሌታ ያችን አገር ሙሴ ርስት አድርጎ ሰጣቸው ።

፯ ወእሉ እሙንቱ ነገሥተ ምድረ ከነዓን ዘቀተልዎሙ
ኢያሱ ወደቂቀ እስራኤል በማዕዶተ ዮርዳኖስ በመንገለ
ባሕረ በለገድ ውስተ ገዳመ ሊባኖስ ወእስከ ደብረ ኤሌኬ
ዘየዐርግ ውስተ ሴይር ወወሀቦሙ ኢያሱ ይእተ ምድረ
ለሕዝበ እስራኤል ።
የእስራኤል ልጆችና ኢያሱ በሊባኖስ ቈላ በበነለድ
ባሕር በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ሴይር በሚደርስ በኤሌኬ
ተራራ የገደሏቸው የከነዓን ነገሥታት እኒህ ናቸው፣ ኢያ
ሱም ያችን ምድር ለእስራኤል ወገኖች ሰጣቸው ።

፰ ወአውረሶሙ ርስተ በውስተ ደብርኒ ወበውስተ ገዳ
ምኒ ወበዐረባ ወበአሴዶት ወበአሕቃላትኒ ወናጌብ ወበኬ
ጤዎን ወበአሞሬዎን ወበከናኔዎን ወበፌርዜዎን ወበኢያ
ቡሴዎን ወበኤዌዎን ።
በቈላና በደጋ በአሴዶትና በዓረባ በናጌብና በአውራ
ጃዎቿ፣ በአሞሬዎንና በኬጤዎን፣ በፌርዜዎንንና በከናኔ
ዎን፣ በኤዌዎንና በኢያቡሴዎን ያለ ርስታቸውን አወረሳ
ቸው ። ኢያ፣ ፲ ፵፣ ፱ ፩ ።

፱ ንጉሠ ኢያሪኮ፡ ወንጉሠ ጋይ እንተ መአንዘ ቤቴል።

አንደኛው የኢያሪኮ ንጉሥ ነው፡ ሁለተኛው የቤቴል መያያዣ የጋይ ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፮ ፪፡ ፰ ፳፱።

፲ ንጉሠ ኢየሩሳሌም፡ ንጉሠ ኬብሮን።

ሦስተኛው የኢየሩሳሌም ንጉሥ ነው፡ አራተኛው የኬብሮን ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲፫ ፳፫።

፲፩ ንጉሠ ኢያሪሞት፡ ንጉሠ ለኪስ።

አምስተኛው የኢያሪሞት ንጉሥ ነው፡ ስድስተኛው የለኪስ ንጉሥ ነው።

፲፪ ንጉሠ ኤሎም፡ ንጉሠ ጋዜር።

ሰባተኛው የኤሎም ንጉሥ ነው፡ ስምንተኛው የጋዜር ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲ ፳፫።

፲፫ ንጉሠ ዳቤር፡ ንጉሠ ጋሌ።

ዘጠነኛው የዳቤር ንጉሥ ነው፡ አሥረኛው የጋሌ ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲ ፴፰።

፲፬ ንጉሠ ኤርሞት፡ ንጉሠ አራድ።

ዓሥራ አንደኛው የኤርሞት ንጉሥ ነው፡ ዓሥራ ሁለተኛው የአራድ ንጉሥ ነው። ዘኍ፡ ፳፩ ፫።

፲፭ ንጉሠ ሎምና፡ ንጉሠ አዶላም።

ዓሥራ ሦስተኛው የሎምና ንጉሥ ነው፡ ዓሥራ አራተኛው የአዶላም ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲ ፳፱፡ ፲፭ ፴፭።

፲፮ ንጉሠ ኤዳ፡ ንጉሠ ኤጣፋድ።

ዓሥራ አምስተኛው የኤዳ ንጉሥ ነው፡ ዓሥራ ስድስተኛው የኤጣፋድ ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲ ፳፰፡ ፲፰ ፲፯።

፲፯ ንጉሠ አፌር፡ ንጉሠ አፌቀጠሰሩት።

ዓሥራ ሰባተኛው የአፌር ንጉሥ ነው፡ ዓሥራ ስምንተኛው የአፌቀጠሰሩት ንጉሥ ነው።

፲፰ ንጉሠ አሶር፡ ንጉሠ ስሞዓን።

ዓሥራ ዘጠነኛው የአሶር ንጉሥ ነው፡ ሃያኛው የስሞዓን ንጉሥ ነው። ፩ ሳሙ፡ ፬ ፲፰-፳፫።

፲፱ ንጉሠ መምሮት፡ ንጉሠ አዜፍ።

ሃያ አንደኛው የመምሮት ንጉሥ ነው፡ ሃያ ሁለተኛው የአዜፍ ንጉሥ ነው። ኢያ፡ ፲፩ ፩።

፳ ንጉሠ ቃሌስ፡ ንጉሠ ዘቃቅ።

ሃያ ሦስተኛው የቃሌስ ንጉሥ ነው፡ ሃያ አራተኛው የዘቃቅ ንጉሥ ነው።

፳፩ ንጉሠ ማርዶት፡ ንጉሠ የዶቆም ዘኬርሜል።

ሃያ አምስተኛው የማርዶት ንጉሥ ነው፡ ሃያ ስድስተኛው የኬርሜል ዕፃ የምትሆን የዶቆም ንጉሥ ነው።

፳፪ ንጉሠ ኤዶር፡ ዘፌናእድር ንጉሠ ሐጌ ዘጋልያ፡ ንጉሠ ተርሳ።

ሃያ ሰባተኛው የፌናአድር ክፍል የምትሆን የኤዶር ንጉሥ ነው፡ ሃያ ስምንተኛው የጋልያ ዕፃ የምትሆን የሐጌ ንጉሥ ነው፡ ሃያ ዘጠነኛው የተርሳ ንጉሥ ነው።

፳፫ እሉ ኵሎሙ ነገሥት፡ ዕሥራ ወተስዐቱ።

እነዚህ ሁሉ ሃያ ዘጠኝ ነገሥታት ናቸው።

## ምዕራፍ ፲፫።

፩ ወልህቀ ኢያሱ ወኀለፈ መዋዒሁ፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ ኀለፈ መዋዕሊከ ለከ ወተርፈት ምድር ብዝኀት ዘኢተዋረሱ።

ኢያሱ አረጀ የወጣትነቱም ወራት አለፈ፡ እግዚአብሔርም ኢያሱን እነሆ የሕፃንነትህ ወራት አለፈ፡ ያልወረሱዋት ብዙ አገር ቀረች አለው። ኢያ፡ ፳፫ ፩፡ ፲፬ ፲።

፪ ወዛቲ ይእቲ ምድር እንተ ተርፈት ደወሎሙ ለፍልስጥኤም ወለጌሴሪ ወለከናኔዎን።

ሳይወርሷት የቀረችውም አገር ይህች ናት፡ የጌሴሪና የፍልስጥኤም የከናኔዎንም አውራጃ ናት።

፫ እምበድው ዘመንገለ ገጸ ግብጽ እስከ ደወሎሙ ለአቃሮን ዘመንገለ ፀጋሞሙ ለአሞሬዎን ዘይትኌለቍ ለኀምስቱ በሐውርተ ፍልስጥኤም ለጋዛ፡ ወለአዛጦን፡ ወለአስቀሎና፡ ወለጌት፡ ወለአቃሮን፡ ወለኤዊ እምቴማን።

በግብጽ ካለ ምድረ በዳ ጀምሮ በፍልስጥኤም ላሉ ለአምስት አገሮች ለአዛጦንና ለጋዛ ለጌትና ለአስቀሎና ከቴማን ጀምሮ ለኤዊና ለአቃሮን የሚቈጠሩ በአሞሬዎን ግራ እስከ አቃሮን አውራጃ ድረስ ነው።

፬ ወኵሉ ምድረ ከነዓን ዘቅድመ ጋዛ ወሲዶናዊ እስከ ጤፌቅ ወእስከ አድዋሊሆሙ ለአሞሬዎን።

ከቴማንም ጀምሮ በሲዶናና በጋዛ አፍዛዥ ያለ የከነዓን አገር ሁሉ እስከ ጤፌቅና እስከ አሞሬዎን አውራጃዎች ድረስ ነው። ኢሳ፡ ፲፱ ፲፰። መሳ፡ ፩ ፴፬።

፭ ወኵሉ ምድረ ገድያድ ዘፍልስጥኤም ወኵሉ ሊባኖስ እምሠርቀ ፀሐይ ወእምገልገላ ዘመትሕተ ደብረ አኤርሞን እስከ ምብዋአ ለኤማት።

የፍልስጥኤም ዕፃ እስከሚሆን እስከ ገድያድ አገር ሁሉ ድረስ እስከ ሊባኖስም ሁሉ ድረስ ከፀሐይ መውጫ ከኤርሞን ተራራ በታች ካለ ከገልገላም ጀምሮ እስከ ኤማት መግቢያ ድረስ ነው። ኢያ፡ ፲፩ ፲፯። ፩ ነገ፡ ፲ ፰።

፮ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር እምሊባኖስ እስከ

ከሊባኖስ ጀምሮ የሮሚም ዕፃ እስከምትሆን እስከ

| | | |
|---|---|---|
| ሙዓለ ሴሬት ዘማይም ዘሮሚም ወኵሉ ሲዶና ኦለ አነ አጠፍኦሙ እምቅድመ ገጾሙ ለእስራኤል በከመ አቤለከ ። | | ማይም ዕፃ እስከ ሴሬት መያያዣ ድረስ በደጋ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው፡ እኔ እንደ ነገርሁህ ከእስራኤል ፊት የማጠፋቸው እስከ ሲዶናም ሁሉ ድረስ ነው ። |
| ወይእዜኒ ክፍሎሙ ዘተ ምድረ ወአስተዋርሶሙ ለተስዐቱ ሕዝብ ወለመንፈቀ ሕዝብ ዘምናሴ እምዮርዳኖስ እስከ ባሕር ዐቢይ ዘመንገለ ዐረበ ፀሐይ ትሁቦሙ ወይከውኖሙ ወሰኖሙ ባሕር ዐቢይ ። | ፯ | አሁንም ይህን ምድር አካፍላቸው ለምናሴ ወገን ለእኩሌታው ነገድና ለዘጠኙ ነገድ አውርሳቸው ከዮርዳኖስ ጀምሮ ከፀሐይ መግቢያ እስከ አለ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ስጣቸው፡ ወሰናቸውም ታላቁ ባሕር ይሁናቸው አለው። |
| ወለእልክቱ ክልኤቱ ነገድ ዘሮቤል ወዘጋድ፡ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወሀቦሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ሠርቀ ፀሐይ፡ እምአሮኤር እንተ ውስተ ማዕዶተ ፈለገ አርኖን፡ ወሀገር እንተ ውስተ ማእከለ ቈላት ። | ፰ | ለእነዚህ ሁለቱ ለጋድ ነገድና ለሮቤል ነገድ፡ ለነገደ ምናሴ እኩሌታም በፀሐይ መውጫ በዮርዳኖስ ማዶ በቈላ መካከል ባለች አገርና በአርኖን ወንዝ ማዶ ካለች ከአሮኤር ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሙሴ ሰጣቸው ። |
| ወኵሉ ሚሶር እምዴቦን ወኵሉ አህጉረ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘነግሠ በሐሴቦን እስከ ደወሎሙ ለደቂቀ ዓሞን፡ ወገለአድ ። | ፱ | ከዴቦንም እስከ ሚሶር ሁሉ ድረስ በሐሴቦን ከነገሠ ከአሞሬዎን ንጉሥ ከሴዎን አገሮች ሁሉ ጀምሮ እስከ ገለዓድና እስከ አሞን ልጆች አውራጃ ድረስ ። |
| ወለደወሎሙ ለጌሴሪ ወለመከጢ ወለኵሉ አድባረ አኤርሞን፡ ወኵሉ ባሳን እስከ አካ ። | ፲ | እስከ መከጢና እስከ ጌሴሪ አውራጃ ድረስ እስከ አኤርሞን ደጋ ሁሉ አውራጃ ድረስ፡ ባሳንንና የባሳን ዕፃ እስከ ምትሆን እስከ አካ ድረስ ። |
| ኵሉ መንግሥቶ ለዓግ ዘባሳን ዘነግሠ በኤንድራይን ወበአስጣሮት ወውእቱ ዘተርፈ እምደምሙ ለእለ ያርብሕ ወቀተሎሙ ሙሴ ወአውረሶሙ ። | ፲፩ | በአስጣሮትና በኤንድራይን የነገሠ የዓግን ግዛት ሁሉ ሙሴ ገድሎ ርስታቸውን ለእስራኤል ካወረሳቸው ከአርበኞች ወገን የቀረም እሱ ነው ። |
| ወኢያጥፍእዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለጌሴሪ ወለመከጢ ወነበሩ ንጉሠ ጌሴሪ ወመከጢ ውስተ ደቂቀ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት ። | ፲፪ | የእስራኤልም ልጆች ጌሴሪንና መከጢን አላጠፉዋቸውም እስከዚህች ቀን ድረስ መከጢና የጌሴሪ ንጉሥ በእስራኤል ውስጥ ተቀመጡ ። ኢያ፡ ፲፫ ፲፩ ። |
| እንበለ ነገደ ሌዊ እለ ኢነሥኡ መክፈልቶሙ እስመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ውእቱ መክፈልቶሙ በከመ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ። | ፲፫ | ዕፃቸውን ካልተቀበሉ ከነገደ ሌዊ በቀር፡ እግዚአብሔር እንደ ነገራቸው ዕፃቸው የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ነውና ። ዘኍ፡ ፲፰ ፳ ። ኢያ፡ ፲፫ ፴፫ ። |
| ወወሀቦሙ ሙሴ ለነገደ ሮቤል በበሕዘቢሆሙ ። | ፲፬ | ሙሴ ለሮቤል ነገድ በየወገናቸው ሰጣቸው ። |
| ወኮነ ደወሎሙ እምአሮኤር እንተ መንገለ ቈላተ አርኖን ወአህጉርኒ ዘውስተ ቈላተ አርኖን ። | ፲፭ | በአርኖን ቈላ ካለ ከአሮኤር ጀምሮ በአርኖን ቈላ ካሉ አገሮችም ጀምሮ ። |
| ወኵሉ ሚሶር እስከ ሐሴቦን ወኵሎን አህጉር ዘሀለዋ ውስተ ሚሶር ወዴቦን ወቤሞን ወበአል ወአብያተ መዔልሞት ። | ፲፮ | ከሚሶርም ሁሉ ጀምሮ እስከ ሐሴቦን ድረስ በሚሶርም እስካሉ አገሮች ሁሉ ድረስ ከዴቦንም ጀምሮ እስከ ቤሞን ድረስ ከበአልም ጀምሮ እስከ አብያተ መዔልሞት ድረስ። |
| ወባሳን፡ ወበቄድሜን፡ ወፌማት፡ ወቀርያትም፡ ወሴባማ፡ ወሴራዳት፡ ወስዮን በደብረ ኤናብ፡ ወቤተ ፌጎር፡ ወኤሴዶት፡ ወፋስጋ፡ ወኤቢታን፡ ወሴሮት ። | ፲፯ | ከባሳን ጀምሮ እስከ በቄድሜን እስከ ፌማት ከቀርያትም እስከ ሴባማ ድረስ ከሴራዳት ጀምሮ በኤናብ ተራራ እስከለ እስከ ስዮን ድረስ፡ (ከብኤል ፌጎር) ከማእቱ ቤት ጀምሮ እስከ ኤሴዶት፡ ከፋስጋ ጀምሮ እስከ ኤቢታንና እስከ ሴሮት ድረስ ። ዘኍ፡ ፴፫ ፳፫ ። ኢያ፡ ፲፪ ፫ ። |
| ወኵሎን አህጉረ ሚሶር ወኵሉ መንግሥተ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘቀተሎሙ ሙሴ ። | ፲፰ | እስከ ሚሶር አገሮች ሁሉ ድረስ ሙሴ እስከ ገደላቸው እስከ አሞሬዎን ንጉሥ እስከ ሴዎን ግዛት ሁሉ ድረስ ድንበራቸው ሆነ ። |
| ወለመሳፍንተ ምድያም፡ ወኤዊን፡ ወሮባቅ፡ ወሱር፡ ወኡር፡ ወሮቤ፡ ወለመሳፍንተ ጸራልያ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ስዮን ። | ፲፱ | የምድያም ገዥዎች ሮባቅና ኤዊን፡ ኡርና ሱር፡ ሮቤንም፡ የጸራልያም ገዥዎች በስዮን የሚኖሩም ሰዎች ። |
| ወለበለዓም ወልደ ቤዖር ዘመቅስም፡ ዘቀተልዎሙ በምዕር ። | ፳ | ሟርተኛ የሚሆን የቤዖር ልጅ በለዓምን አንድነት አጠፉዋቸው ። ዘኍ፡ ፴፩ ፰ ። |
| ወኮነ ደወሎሙ ለሮቤል ዮርዳኖስ ወሰኖሙ ወዝንቱ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ሮቤል በበነገዶሙ ወአህጉሪሆሙኒ። | ፳፩ | የሮቤል ልጆች ድንበራቸው እንዲህ ሆነ፡ ወሰናቸው ዮርዳኖስ ነው፡ በየወገናቸው የሮቤል ልጆች አገራቸውና ዕፃቸው ይህ ነው ። |

፳፬ ወወሀቦሙ ሙሴ ለደቂቀ ጋድ በበነገዶሙ ወከነ ደወሎሙ ኢያዜር ።

፳፭ ወኵሎን አህጉረ ገለዓድ ወመንፈቀ ምድረ ደቂቀ አሞን እስከ ዐራብ እንተ ቅድመ ገጸ አራድ ።

፳፮ ወእምሐሴቦን እስከ አራቦት እንተ መንገለ መሴፋ ወበጣኒ ወማአን እስከ ደወሎሙ ለዴቦን ወአዳማ፣ ወአትርጋ ወአበይን፣ ዘትንብሬ፣ ወሲኮታ፣ ወሳፌን ።

፳፯ ወበሰደኒ ዘተርፈ መንግሥቱ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን፣ ወዮርዳኖስ ወሰኖሙ እስከ አሐዱ ኅብር ዘባሕረ ኬኔሬት በማዕዶተ ዮርዳኖስ ጽባሒዊ ።

፳፰ ወዝንቱ ውእቱ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ጋድ በበነገዶሙ፣ ወሚጡ ዘበኖሙ ቅድመ ፀሮሙ እስመ በበነገዶሙ ከነ አህጉሪሆሙኒ ወደብረ አህጉሪሆሙኒ ።

፳፱ ወወሀቦሙ ሙሴ ለመንፈቀ ነገደ ምናሴ በበሕዘቢሆሙ ።

፴ ወከነ ደወሎሙ እምሐኖ ወኵሉ ባሳን፣ ወኵሉ መንግሥተ ዓግ ንጉሠ ባሳን፣ ወኵሎን አህጉረ ኢያእር እለ ሀለዋ ውስተ ባሳን ስሳ አህጉር ።

፴፩ ወመንፈቀ ምድረ ገለአድ ወአስጣሮት ወኤንድራይን አህጉረ መንግሥቱ ለዓግ እለ ውስተ ባሳን ለደቂቀ ማኪር ትውልደ ምናሴ ወለመንፈቆሙሂ ለደቂቀ ማኪር ዘትውልደ ምናሴ በበሕዘቢሆሙ ።

፴፪ እሉ እሙንቱ ዘአስተዋረሰሙ ሙሴ በአራቦት ዘሞዓብ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ጽባሒሁ ለኢያሪኮ ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

፩ ወእሉ እሙንቱ እለ አስተዋረስዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ከነዓን አልአዛር ካህን፣ ወኢያሱ ወልደ ነዌ፣ ወመላእክተ ቤተ አበወ ነገዶሙ ለእስራኤል ።

፪ በዐመክፈልቶሙ ተዋረሱ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ፣ ተስዐቱ ነገድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ እማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

፫ ወለሌዋውያንሰ ኢወሀብዎሙ መክፈልቶሙ ።

፬ እስመ ደቂቀ ዮሴፍ ክልኤቱ ነገድ እሙንቱ ዘምናሴ ወዘኤፍሬም ወኢወሀብዎሙ መክፈልቶሙ ምድረ ለሌዋውያን ዘእንበለ አህጉር ዘውስቴቶን ይነብሩ ዘፈለጡሎሙ ።

፭ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ወተካፈሉ ምድረ ።

፮ ወመጽኡ ደቂቀ ይሁዳ ኀበ ኢያሱ በገልገላ ወይቤሎ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ቄኔዛዊ ለሊከ ተአምር ቃለ ዘይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር በእንቲአየ ወእንቲኒ ውስተ ቃዴስ በርኔ ።

፯ እስመ አርብዓ ዓም ሊተ አመ ፈነወኒ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር እምቃዴስ በርኔ ከመ እርአያ ለዛቲ ምድር ወዜነውዎሙ ነገረ ዘከመ ሐሊናሆሙ እኅውየ አለ ዐርጉ ምስሌየ ።

ሙሴ ለጋድ ልጆች በየወገናቸው ሰጣቸው ድንበራቸውም ኢያዜር ሆነ ።

የአሞን ልጆች አገር እኩሌታና የገለዓድ አገሮችን በአራድ ፊት ለፊት ካለው እስከ ዓራብ ድረስ ሰጣቸው ።

ከሐሴቦን ጀምሮ በበማኒና በመሴፋ አውራጃ እስከአ እስከ ዓራቦት ድረስ ከማአንም ጀምሮ እስከ አዳማና እስከ ዴቦን፣ ከአትርጋ ጀምሮ የትንብሬ ዕጣ እስከሆነች እስከ አበይን ድረስ ከሲኮታ ጀምሮ እስከ ሳፌን ድረስ ።

እስከ ሐሴቦን ንጉሥ እስከ ሴዎን ግዛት ድረስና እስከ ቀረውም ሌላ አገር ድረስ በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ የባሕረ ኬኔሬት ዕፃ እስከ ምትሆን እስከ አንድ ወገን ድረስ ዮርዳኖስ ወሰናቸው ነው ። ዘፍ፡ ፫ ፲፯ ።

የጋድ ልጆች በየወገናቸው ፈንታቸው ይህ ነው፣ መንደራቸውም በየወገናቸው ሆዷልና በጠላቶቻቸው ፊት ጀርባቸውን መልሰው ፳፰ ።

ሙሴ ለነገደ ምናሴ እኩሌታ በየወገናቸው ሰጣቸው።

ድንበራቸውም ከበሳንና ከሐኖ ጀምሮ እስከ ባሳን ንጉሥ እስከ የዓግ ግዛት ድረስ ሆነ፣ በባሳን ያሉ የኢያእር አገሮች ሁሉ ስሳ ከተሞች ናቸው ። ዘኍ፡ ፴፪ ፵፩ ።

እስከ ገለዓድ ምድር እኩሌታ በባሳን እስከሉ የዓግ ግዛት እስከሚሆኑ አገሮች እስከ ኤንድራይንና እስከ አስጣሮት ድረስ ከምናሴ ለተወለዱ ለማኪር ልጆች ለእኩሌቶች በየወገናቸው አወረሳቸው ። ፩ ዜና መ፡ ፪ ፳፫ ።

በኢያሪኮ ምሥራቅ በዮርዳኖስ ማዶ የሞዓብ ዕጣ በምትሆን በዓራቦት፣ ሙሴ በየወገናቸው ያወረሳቸው እሊህ ናቸው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፩ ። ኢያ፡ ፲፱ ፴ ፡ ፲፯ ፩ ።

ምዕራፍ ፲፬ ።

በከነዓን አገር የእስራኤል ልጆች ያወረስዋቸው እሊህ ናቸው፣ የነዌ ልጅ ኢያሱና ካህኑ አልአዛር የእስራኤል የነገዳቸው አባቶች አለቆችም ናቸው ። ዘኍ፡ ፴፬ ፲፭ ።

የነገደ ምናሴ እኩሌታና ዘጠኝ ነገድ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል እንዳዘዘ በዮርዳኖስ ማዶ የየርስታቸውን ዕጣ ተካፈሉ ። ዘኍ፡ ፳፯ ፶፭ ፡ ፴፫ ፶፬ ።

ለሌዋውያን ግን ዕጣቸውን አልሰጧቸውም ።

የዮሴፍ ልጆች ኤፍሬምና ምናሴ ሁለት ነገድ ቀብለው ተቈጥራዋልና በውስጣቸው ከሚኖሩባቸው ከለዩላቸው አገሮች በቀር ለሌዋውያን ዕጣቸውን አልሰጡዋቸውም ። ዘፍ፡ ፵፰ ፭ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፭ ፪ ።

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የእስራኤል ልጆች እንደዚህ አደረጉ፣ ምድሩን ተካፈሉ ። ዘኍ፡ ፴፭ ፪ ።

የይሁዳም ልጆች በገልገላ ወዳለ ወደ ኢያሱ መጡ፣ የቄኔዝ ወገን የሚሆን የዮፎኒ ልጅ ካሌብ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ሰው ለሚሆን ለሙሴ ስለኔ የተናገረውን ነገር አንተ ታውቃለህ፣ አንተም በቃዴስ በርኔ ነበርክ ።

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ ይህችን አገር እናያት ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ ለኔ አርባ ዘመን ሁኖኝ ነበር፣ ከኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼም እንደ አሳባቸው መጠን ነገሩዋቸው ። ዘኍ፡ ፲፫ ፳፯፣ ፲፬ ፯ ።

፰ ወአክሐድዎ ለልበ ሕዝብ ወአንሰ ገባእኩ እትልዎ ለእግዚአብሔር አምላክየ ።

፱ ወመሐለ ሙሴ በይእቲ ዕለት እንዘ ይብል ምድር እንተ ውስቴታ በረገ እንተ ለከ ትከውን መክፈልተከ ወለውሉድከ ለዓለም እስመ ገባእኩ እትልዎ ለእግዚአብሔር አምላክየ ።

፲ ወይእዜኒ ናሁ አርባዓ ወኃምስቱ ዓም እምአመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዘንተ ቃለ ወሖሩ እስራኤል ውስተ ገዳም ።

፲፩ ወይእዜኒ ናሁ ዮምኒ እንዘ ሰማንያ ወኃምስቱ ዓመትየ ዓዲየ ጽኑዕ አነ ከመ አመ ይፌንወኒ ሙሴ ከማሁ ጽኑዕ አነ ይእዜኒ ለወፂአ ውስተ ፀብእ ወለአትዎኒ ።

፲፪ ወይእዜኒ ኅሠሥከ ዘንተ ደብረ በከመ ይቤ እግዚአብሔር በይእቲ ዕለት እስመ ለሊከ ሰማዕከ ይእተ አሚረ ዘንተ ቃለ ።

፲፫ ወይእዜሰ ሰብአ ኤቄም ህየ ሀለዉ ወአህጉሪሆሙኒ ዐበይት ወጽኑዓት ወእመሰ ሀለወ እግዚአብሔር ምስሌየ እጠፍኦሙ በከመ ይቤለኒ እግዚአብሔር ።

፲፬ ወባረኮ ኢያሱ ለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ወልደ ቄኔዝ ወወሀቦ ኬብሮንሃ መክፈልቶ ።

፲፭ ወበበይነ ዝንቱ ኮነት ኬብሮን ለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ቄኔዛዊ መክፈልቶ እስከ ዛቲ ዕለት እስመ ተለዎ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ።

፲፮ ወስማ ቀዲሙ ለኬብሮን ሀገረ አርጎብ ወደብረ አህጉር ይእቲ ለእለ ውስተ ኤቄም ወአዕረፈት ምድር እምቀትል ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

፩ ወኮነ ደወሎሙ ለነገደ ይሁዳ በበሕዘቢሆሙ ዘመንገለ አዜብ ኀበ ደወለ ኤዶም እምገዳም ዘጺን እምጽንፈ ቴማን እስከ አሐዱ ኅብር ዘበሕረ ኤሌቄ ።

፪ ወእምፍናት እንተ ትወስድ ላዕለ ሊብ፡ ወትሐውር እንተ ቅድመ አቅራቢን ።

፫ ወትወፅእ ላዕለ ኤናቅ ወተዐርግ እምሊባኖስ ላዕለ ቃዴስ በርኔ ወትወፅእ ላዕለ አስሮን ወተዐርግ ላዕለ ሰራዳ ።

፬ ወትወፅእ ላዕለ ዐረበ ቃዴስ ወተሐውር ላዕለ ኤልሞናን ወትወፅእ ላዕለ ቈላተ ግብጽ ወይከውን ሞጻእቱ ለደወሎሙ ላዕለ ባሕር ወዝንቱ ውእቱ ደወሎሙ ዘመንገለ አዜብ ።

፭ ወደወሎሙ ዘመንገለ ጽባሕ ኵሉ ባሕረ ኤሌቄ እስከ ዮርዳኖስ ወደወሎሙኒ ዘመንገለ መስዕ እምፍናት እንተ ኀበ ባሕር ወእምአሐዱ ኅብር ዘዮርዳኖስ፡ ወየዐርግ ደወሎሙ ዲበ ቤተ ገልአም ።

፮ ወየኀልፍ ዲበ በራ ወየዐርግ ላዕለ ሊቶንቤዎን ዘደወለ ሮጋቤል ።

ነግረውም የሕዝቡን ልቡና አስከዱት፣ እኔ ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን (በሃይማኖት) አክተለው ዘንድ ተመለስኩ ። ዘዳ፡ ፩ ፳፰፡ ፲፱ ፳፱ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን (በሃይማኖት) አክተለው ዘንድ ወደ መከተል ተመልሻለሁና ሙሴ በዚያች ቀን ያች የወጣህባት አገር ለዘለዓለሙ ላንተና ለልጆችህ ፈንታ ትሁን ብሎ ማለ ። ዘኁ፡ ፲፬ ፳፫ ። ኢ.ያ፡ ፳ ፱ ።

አሁንም እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከነገረው እስራኤልም በምድረ በዳ ከኖሩ ወዲህ ያለው ዘመን እነሆ አርባ አምስት ዘመን ነው ።

እነሆ ዛሬም ለኔ ሰማንያ አምስት ዘመን ሲሆነኝ ገና ክጉልበት ነኝ ሙሴ በላከኝ ጊዜ ክጉልበት እንደ ነበርሁ አሁንም ወደ ዘመቻ ለመውጣትና ለመግባት እንደዚያው ክጉልበት ነኝ ። ዘኁ፡ ፲፫ ፴፡ ፲፬ ፯ ። ዘዳ፡ ፴፬ ፯ ።

በዚያች ቀን እግዚአብሔር እንደተናገረ የዚያን ጊዜ ይህንን ነገር አንተም ሰምተሃልና አሁን ይህንን አስምንኻለሁ ይህንን አገር ስጠኝ ።

አሁን የኤቄም ሰዎች በዚያ አሉ፣ አምባዎቻቸውም ረጃጅሞችና የጸኑ ናቸው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ከኔ ጋር ካለ እግዚአብሔር እንዳለኝ አጠፋቸዋለሁ አለው ።

ኢያሱም የቄኔዝ ልጅ የሚሆን የዮፎኒ ልጅ ካሌብን መርቆ ኬብሮንን ፈንታ (ድርሻ) አድርጎ ሰጠው ።

የእስራኤል ፈጣሬ እግዚአብሔርን (በሃይማኖት) ተከትሎታልና ስለዚህ ኬብሮን እስከዚች ቀን ድረስ የቄኔዝ ልጅ ለሚሆን ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ፈንታው ሆነች ።

ቀድሞ ግን የኬብሮን ስሟ አርጎብ ይባል ነበር፣ በኤቄም ላሉ ሰዎችም የአገራቸው መዲና ትባል ነበር፣ ከዚህ በኋላ አገሪቱ ከጦርነት አረፈች ። ኢ.ያ፡ ፳፩ ፲፩፡ ፲፩ ፳፫ ።

## ምዕራፍ ፲፭ ።

በየወገናቸው የነገደ ይሁዳ ድንበራቸው በኤዶምያስ አውራጃ ባለ በአዜብ በኩል ጺን የሚባል ዛፍ ካለበት ምድረ በዳ ጀምሮ ከቴማንም ዳርቻ ጀምሮ እስከ ባሕረ ጨው እስከ አንድ ወገን ድረስ ነው ። ዘኁ፡ ፴፬ ፫ ።

ወደ ሊብ ከምትወስድ መንገድ ጀምሮ ከአቅራቢን አፋዛገር ትደርሳለች ።

ከኤናቅም ወጥታ ከሊባኖስ እስከ ቃዴስ በርኔ ትደርሳለች ከአስሮንም ወጥታ ወደ ሰራዳም ትደርሳለች ።

ከቃዴስም ምዕራብ ወጥታ ወደ ኤልሞናን ትደርሳለች እስከ ግብጽ ቈላም ትደርሳለች፣ የአገራቸው ፍጻሜም ባሕረ ጨው ነው፣ በአዜብ በኩል ያለው ድንበራቸው ይህ ነው ።

በምሥራቅም በኩል ድንበራቸው ከባሕረ ጨው ሁሉ ጀምሮ እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ነው፤ በመስዕም በኩል ድንበራቸው ከባሕረ ጨው መንገድ ጀምሮ ከዮርዳኖስም አንድ ወገን ጀምሮ፣ ወደ ቤተ ገለዓም ይደርሳል ።

ወደ በራም ይደርሳል፣ የሮጋቤል አውራጃ ወደሚሆን ሊቶንቤዎንም ይደርሳል ። ኢ.ያ፡ ፲፰ ፲፱ ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
## The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



| | | |
|---|---|---|
| ወየዐርግ ላዕለ ራብዕቱ ለቈላተ አኮር ወይወርድ ላዕለ ገልገላ እንተ ቅድመ ማዕዶተ አዳሚን እንተ መንገለ አዜቡ ለቈላ ፡ ወትወፅእ ላእለ ነቅዐ ማየሄልዩ ወይከውን ሞጻእቱ ነቅዐ ሮጌል ። | ፯ | ወደ አኮር ሸለቆ ፍጻሜም ይደርሳል ፡ በቈላው ግራ በለች በአዳሚን አፋዛዥ ጌልጌላም ይደርሳል ፡ ወደ ማየሄልዩ ወንዝም ትደርሳለች ፡ መጨረሻውም የሮጌል ምንጭ ነው ። |
| ወየዐርግ እንተ ቈላተ ወልደ ኤኖም እንተ መንገለ አዜብ ለኢያቡስ እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ወይወፅእ ዳወራ ውስተ ርእሰ ደብር ዘሀለወ ቅድመ ቈላተ ኤኖም ዘኀበ ባሕር እንተ ውስተ አሐዱ ኀብር ዘምድረ ራፋይን ዘመንገለ መስዕ ። | ፰ | ይህችውም ኢየሩሳሌም ናት ፡ በኢያቡስ ግራ ወዳለ ወደ ኤኖም ልጅ ቈላ ትደርሳለች ፡ በመስዕ በኩል ኃያላኑ በያዟት አገር በአንድ ወገኑ በባሕረ ጌው አጠገብ ባለ በኤኖም ቈላ አፋዛዥ ወዳለ ወደ ተራራው ራስ ወደ ዳወራ ይደርሳል ። |
| ወይወስድ እምውእቱ ርእሰ ደብር ላዕለ ነቅዐ ማይ ዘነፍቶ ፡ ወይበጽሕ ውስተ ኤፍሮን ወይወስድ ላዕለ ኢያቡኤል እንተ ይእቲ ሀገረ ኢያሪን ። | ፱ | ከዚህ ከተራራውም ራስ ጀምሮ ወደ ነፍቶ ውኃ ምንጭ ይደርሳል ፡ ወደ ኤፍሮንም ይደርሳል ፡ ወደ ኢያቡኤልም ይደርሳል ፡ ይህችውም ኢያሪን የምትባል አገር ናት ። |
| ወየኀልፍ እምኢያቡኤል ላዕለ ባሕር ፡ ወየኀልፍ እንተ ደወለ አስራቱስ እንተ መንገለ አዜብ ለሀገረ ኢያሪም ወመስዕ ለከስሎን ወይወስድ ላዕለ ሀገረ ሄልዩ ወየኀልፍ ላዕለ ሊብ ። | ፲ | ከኢያቡኤልም ጀምሮ ወደ ባሕር ይደርሳል ፡ በኢያሪም አገር ግራ ወዳለች ወደ አስራቱስ አውራጃም ይደርሳል ፡ ወደ ከስሎን ቀኝም ይደርሳል ፡ ወደ ሄልዩ አገርም ይደርሳል ፡ ወደ ሊብም ይደርሳል ። ፩ ሳሙ ፡ ፯ ፱ ። |
| ወይወፅእ ላዕለ አዜብ ለአቃሮን ወይኀብእ ላዕለ መስዕ ወይወፅእ ዲበ ሰቆት ወየኀልፍ ላዕለ አዜብ ወይወፅእ ላዕለ ሌብና ወይከውን ሞፃእቱ ለደወሎሙ ዲበ ባሕር ወደወሎሙኒ ዘመንገለ ባሕር ፡ ባሕር ዐቢይ ወሰኖሙ ። | ፲፩ | ወደ አቃሮን ግራም ይደርሳል ፡ ወደ መስዕ ይደርሳል ወደ ሰቆትም ወደ አዜብም ይደርሳል ፡ ወደ ሌብናም ይደርሳል ፡ የአገራቸው ፍጻሜ ባሕር ነው ፡ በምዕራብም በኩል ወሰናቸው ድንበራቸው ታላቁ ባሕር ነው ። |
| ወዝንቱ ውእቱ ወሰኖሙ ወደወሎሙ ለደቂቀ ይሁዳ ዘዐውዶሙ በበሕዘቢሆሙ ። | ፲፪ | የይሁዳ ልጆች በየወገናቸው በዙርያቸው ዳርቻቸው ይህ ነው ። ዘኍ ፴፬ ፯ ። ዘዳ ፲፩ ፳፬ ። |
| ወለከሌብ ወልደ ዮፎኒ ወሀበ መክፈልቶ በማእከሎሙ ለደቂቀ ይሁዳ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወወሀበ ኢያሱ ሀገረ አስበቅ ደብረ አህጉረ ኤናቅ እንተ ይእቲ ኬብሮን ። | ፲፫ | ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብም በእግዚአብሔር ትእዛዝ በይሁዳ ልጆች መካከል ፈንታውን ሰጠው ፡ ይህችውም ኬብሮን ናት ፡ የኃያላኑ አገሮች መዲና የምትሆን አስበቅ የምትባል አገር ኢያሱ ሰጠው ። ኢያ ፡ ፲፬ ፲፫ - ፲፭ ። |
| ወሠረዎሙ እምህየ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ለሠለስቲሆሙ ደቂቀ ኤናቅ ለጡሲ ፡ ወለጠሐሚ ፡ ወለአካሚ ። | ፲፬ | የዮፎኒ ልጅ ካሌብም ጠሐሚንና ጡሲን ፡ አካሚንም ሦስቱን ሁሉ የኃያላኑን ልጆች ከዚያ አጠፋቸው ። |
| ወዐርገ እምህየ ካሌብ ላዕለ እለ ይነብሩ ውስተ ዳቤር ወስማ ለዳቤር ቀዲሙ ሀገረ መጽሐፍ ። | ፲፭ | ካሌብ በዚያ በዳቤር ወደ ሚኖሩ ሰዎች ወጣ ፡ ቀድሞ የዳቤር ስሟ የወግ የታሪክ አገር ይባል ነበር ። |
| ወይቤ ካሌብ ዘነሥአ ወቀተላ ለሀገረ መጽሐፍ ወእስተጋብአ እሁቦ አስካሃ ወለትየ ትኩኖ ብእሲተ ። | ፲፮ | ካሌብ የወግ የታሪክ አገርን ወግቶ እጅ ላደረጋት ሰው ሚስት ልትሆነው ልጄን አስካን እሰጠዋለሁ አለ ። |
| ወነሥአ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ ወወሀቦ አስካሃ ወለቶ ትኩኖ ብእሲተ ። | ፲፯ | የካሌብም ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ወግቶ እጅ አደረጋት ፡ ልጁ አስካን ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው ። |
| ወእምዝ ሶበ ለሐዊር ተማከረቶ እንዘ ትብል እስእሎ ለአቡየ ገራህተ ወጸርሐት በዲበ አድግ ወይቤላ ካሌብ ምንት ኮንኪ ። | ፲፰ | ከዚህ በኋላ ለመሄድ በተነሣች ጊዜ አባቴን ጕልት እለምነዋለሁ ብላ ተማከረችው በአህያም ላይ ሁና እንጕራጕረች ፡ ካሌብም ምን ሆንሺ ፤ አላት ። ዘፍ ፡ ፳፬ ፷ ። |
| ወትቤሎ ሀበኒ በረከተ እስመ ውስተ ምድረ አዜብ ፈነውከኒ ወመጠውከኒ ሀበኒ በታኔስሃ ፡ ወወሀባ ጎኒታላን እንተ ላዕሉ ወጎኒታላን እንተ ታሕቱ እምርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ይሁዳ ። | ፲፱ | ወደ አዜብ በረኻ ስደኸኛልና በታኔስን ጕልት ስጠኝ አለችው ፡ ከነገደ ይሁዳ ልጆች ርስት ላይኛይቱ ጎኒታላንና ታችኛይቱ ጎኒታላን ሰጣት ። ዘፍ ፡ ፴፫ ፲፩ ፡ ፳፩ ፳፭ ። |
| ወኮነ አህጉሪሆሙ ለነገደ ደቂቀ ይሁዳ ኀበ ደወለ ኤዶም ወአዜብ በሴልኤል ፡ ወአራ ፡ ወአሶር ። | ፳ | የይሁዳ ልጆች ወገኖች አገሮቻቸው ከኤዶም አውራጃ በአዜብ አራና ፡ በሴልኤል ፡ አሶርም ነው ። |
| ወኢቃም ፡ ወሬግማ ፡ ወአሩሄል ፡ ወቃዴስ ፡ ወአሶርዮስም ፡ ወመናን ፡ ወበልማን ፡ ወአዕፃዳቲሆን ። | ፳፩ | ሬግማና ኢቃም ፡ ቃዴስና አሩሄል አሶርዮስምና መናን ፡ በልማንም ከመንደሮቻቸው ጋር እነዚህ ናቸው ። |
| ወሀገረ አሴሮም እንተ ይእቲ አሶር ፡ ወሰማዕ ፡ ወሞላዳ ፡ ወሴር ፡ ወቤፋላድ ፡ ወከላሲአዳ ፡ ወቤርሳሕ ፡ ወአዕፃዳቲሆን ። | ፳፪ | ይችውም አሶር ናት ፡ አሴሮም የምትባል አገር ሰማዕና ሞላዳ ፡ ቤፋላድና ሴር ፡ ቤርሳሕና ከላሲአዳ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ እሊህ ናቸው ። ፩ ዜና መዋ ፡ ፲፩ ፱ ። |
| ባላ ፡ ወበቆብ ፡ ወደብራቲሆን ። | ፳፫ | በቆብና ባላ ከመሠማሪያቸው ጋራ እሊህ ናቸው ። |

፴፬ ወኤለበሐዳድ፡ ወቤቴል፡ ወኤርማ፡ ወሲቅላቅ፡ ወመክሮን፡ ወሰቱና።

፴፭ ወላበስ፡ ወሳሌ፡ ወኤሞት፡ ዕሥራ ወተስዓቱ አህጉር፡ ወአዕፃዳቲሆሙ በውስተ ሐቅል።

፴፮ ወአስጥሐል፡ ወአራ፡ ወአሣ፡ ወራሚና፡ እንተ ሳዕሉ፡ ወኢዳዳት፡ ወመሐስን፡ ወኤርሞት፡ ወኤዶላም፡ ወአምራ፡ ወሰዓከ፡ ወሐዚቃ።

፴፯ ወሴቃርም፡ ወጋዴር፡ ወዳቤር፡ ዓሥሩ ወአርባዕ አህጉር፡ ወአዕፃዳቲሆን።

፴፰ ሲና፡ ወአዶሳን፡ ወመገድገድ፡ ወአዶላል፡ ወመሴፋ፡ ወይቃሩል፡ ወመኬሳ።

፴፱ ወበሴዶት፡ ወይዴሃ፡ ወዳልያ፡ ወከብራ፡ ወመሐክስ፡ ወጋዶራ፡ ወበጋዲያል።

፵ ወኖማን፡ ወመቄዶም፡ ዓሥሩ ወስሱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን።

፵፩ ሌምና፡ ወኢተቅ፡ ወአኖክ፡ ወአድና፡ ወናሴብ።

፵፪ ወኤላም፡ ወአቄዛም፡ ወራሴር፡ ወኤሎም፡ ተስዓቱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን።

፵፫ አቃሮን፡ ወአዕፃዳቲሃ፡ ወደብራቲሃ።

፵፬ እምአቃሮን ወጌማ፡ ወኵሉ ዘሀለወ ቅሩበ አሴዶት፡ ወአዕፃዳቲሆን።

፵፭ አስያዶት፡ ወአዕፃዳቲሃ፡ ወደብራቲሃ።

፵፮ ወጋዛ፡ ወአዕፃዳቲሃ፡ ወደብራቲሃ እስከ ፈለገ ግብጽ፡ ወባሕር ዓቢይ ወሰኑ።

፵፯ ወአድባረ ሣምርሂ፡ ኤዬቴር፡ ወስከ፡ ወፌና፡ ወሀገረ መጽሐፍ ይእቲ ዳቤር።

፵፰ ወአኖን፡ ወሴቄማ፡ ወኤሱም፡ ዓሥሩ ወአሐቲ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን።

፵፱ ኤሬም፡ ወራምና፡ ወሰማ፡ ወኢያማይን፡ ወቤቴቁ፡ ወፋቁሐ፡ ወኤውማ።

፶ ወሀገረ አርጎብ እንተ ይእቲ ኬብሮን፡ ወሰሬት፡ ተሱዑ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን።

፶፩ ማሐር፡ ወኬርሚል፡ ወአዜብ፡ ወኢጦን፡ ወኢያሬዩል።

፶፪ ወኢያሪቀም፡ ወዘቃይን፡ ወጋበ፡ ወተምና፡ ተሱዑ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን።

፶፫ አብዋ፡ ወተሱር፡ ወጌዳር፡ ወሚጌዶት፡ ወቤታንዎ፡ ወኤቱም፡ ስሱ አህጉር፡ ወአዕፃዳቲሆን።

፶፬ ቶቂ፡ ወኤፍራታ፡ እንተ ይእቲ ቤተ ልሔም፡ ወፋጎር ወኤጣን፡ ወቱላን።

፶፭ ወጠጠን፡ ወሰብሂ፡ ወቃሬ፡ ወጌሴም፡ ወኤቴር፡ ወመኖክ፡ ዓሡሩ ወአሐቲ አህጉር፡ ወአዕፃዳቲሆን።

፶፮ ቀርያት በዓል፡ እንተ ይእቲ ሀገረ ኢያርም፡ ወሶቤታ ክልኤቲ አህጉር ወደብራቲሆን።

፶፯ በልዳንስ፡ ወተራብዓም፡ ወኤምን፡ ወሲኬወዛን፡ ወናፍላዛን፡ ወሰሎም፡ ወአቃዱስ፡ ሰብዓቱ አህጉር፡ ወአዕፃዳቲሆን።

፶፰ ወለኢያቡሴዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ስእንዎሙ ደቂቀ ይሁዳ አጥፍኦቶሙ፡ ወነበሩ ኢያቡሴዎን፡ ውስተ ኢየሩሳሌም፡ እስከ ዛቲ ዕለት።

ቤቴልና ኤለበሐዳድ ሴቂላቅና ኤርማ ሰቱናና መክሮን።

ሳሌና ላበስ፡ ኤሞትም በምድረ በዳ ካሉት ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ እኒህ ሃያ ዘጠኙ አገሮች ናቸው።

አራና አስጥሐል፡ በላይ ያሉት ራሚናና አሣ፡ መሐስንና ኢዳዳት፡ ኤዶላምና ኤርሞት፡ ሰዓክና አምራ ሐዚቃም። ኢያ፡ ፲፱ ፲፯።

ጋዴርና ሴቃርም፡ ዳቤርም ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ እነዚህ አሥራ አራቱ አገሮች ናቸው።

አዶሳንና ሲና፡ አዶላልና መገድገድ፡ ይቃሩልና መሴፋ መኬሳም። ፩ ሳሙ፡ ፲፯ ፶፪።

ይዴሃና በሴዶት፡ ከብራና ዳልያ፡ ጋዶራና መሐክስ፡ በጋዲያልም። ኢያ፡ ፳ ፫። ፩ ነገ፡ ፴፱ ፩።

መቄዶምና ኖማን፡ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ ስድስት አገሮች እነዚህ ናቸው።

ኢተቅና ሌምና፡ አድናና አኖክ፡ ናሴብም።

አቄዛምና ኤላም፡ ኤሎምና ራሴር፡ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋር እነዚህ ዘጠኝ አገሮች ናቸው።

አቃሮን ከአውራጃዋና ከመሠማሪያዎቿ ጋር።

ከጌማና ከአቃሮን ጀምሮ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋር በአሴዶት አቅራቢያ ያለው ሁሉ። ዘኍ፡ ፴፩ ፴፭።

አስያዶት ከአውራጃዎቿና ከመሠማሪያዎቿ ጋራ።

ጋዛ ከመሠማሪያዎቿ ጋራ እስከ ግብጽ ወንዝ ድረስ ነው፡ ወሰኑም እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ነው።

የኢዬቴር የሣምርና የወስከ ተራራዎች፡ ይህችም የወሚ የታሪክ አገር የምትሆን ዳቤር ናት ፌናም ናት።

ሴቄማ አኖንና ኤሱም ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ አንድ አገሮች ናቸው። ፩ ዜና መዋ፡ ፮ ፶፯።

ኤሬም ራምና ሰማ፡ ኢያማይን ቤቴቁ ፋቁሔ ኤውማ።

ይህችውም ኬብሮን ናት፡ ሰሬትና፡ አርጎብ የምትባል አገር ከመሠማሪያዎቻቸው ጋር ዘጠኝ አገሮች ናቸው።

ማሐርና ኬርሚል፡ አዜብ፡ ኢጦንና ኢያሬዩል።

ኢያሪቀም፡ ዘቃይን፡ ጋበና ተምና ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዘጠኝ አገሮች ናቸው።

አብዋ፡ ተሱር፡ ጌዳር፡ ሚጌዶት ቤታንዎና ኤቱም ከመሠማሪያቸው ጋራ ስድስት አገሮች ናቸው።

ቶቂ፡ ኤፍራታ ይችውም ቤተ ልሔም ናት፡ ፋጎር፡ ኤጣንና ቱላን።

ጠጠን፡ ሰብሂ፡ ቃሬ፡ ጌሴም፡ ኤቴር፡ መኖክ፡ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ አንድ አገሮች ናቸው።

ሶቤታና ይህችውም ኢያርም የምትባል አገር ናት፡ ቀርያት በዓል ከመሠማሪያዎቻቸው ጋር ሁለት አገሮች ናቸው።

በልዳንስና ተራብዓም ኤምንና ሲኬወዛን ናፍላዛንና ሰሎምና አቃዱስ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ሰባት አገሮች ናቸው።

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢያቡሴዎንም የይሁዳ ልጆች ማጥፋት ተሳናቸው፡ ኢያቡሴዎንም እስከዚች ቀን ድረስ በኢየሩሳሌም ኖሩ። ፩ ሳሙ፡ ፴፱ ፲፩።

## ምዕራፍ ፲፮ ።

፩ ወኮነ ደወሎሙ ለደቂቀ ዮሴፍ እምዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ እምጽባሒሁ ወየዐርግ እምኢያሪኮ ላዕለ አድባር ዘውስተ ገዳም ውስተ ቤቴል ሎዛ ።

፪ ወይወፅእ እምቤቴል ሎዛ ወየኀልፍ ላዕለ ደወለ ኬሮንቴ ።

፫ ወየኀልፍ ኀበ ሰብአቱ አፍላግ ውስተ ደወሎሙ ለቤቶሮን ዘታሕታይ ወይከውን ሞጻኢቱ ላዕለ ባሕር ።

፬ ወተዋረሱ ደቂቀ ዮሴፍ ኤፍሬም ወምናሴ ።

፭ ወኮነ ደወሎሙ ለኤፍሬምኒ በበሕዝቢሆሙ እምጽባሒሁ ለአጣሮት ወኤሮን ወቤቶሮን እንተ ላዕሉ ወጋዜራ ።

፮ ወየኀልፍ ላዕለ ባሕር እመስዕ ለቶርማ ወየኀልፍ ላዕለ ጽባሕ ኀበ ቴርናቶ ወውስተ ኤላስ ።

፯ ወየኀልፍ እምጽባሒሁ ውስተ ኢያኖክ ወውስተ መራክ ወአጣሮት ወአሰየዳቲሆን ።

፰ ወይበውእ ኀበ ኢያሪኮ ወይወፅእ ኀበ ዮርዳኖስ ።

፱ ወእምጣፉ የሐውር ላዕለ ባሕር ኀበ ኬልቃና ወይከውን ሞጻኢቱ ኀበ ባሕር ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለሕዝበ ኤፍሬም በበሕዝቢሆሙ ።

፲ ወአህጉሪሁ ኀበ ፈለጡ ለደቂቀ ኤፍሬም በውስተ ማእከለ ርስቶሙ ለደቂቀ ምናሴ ኵሉ አህጉሪሆሙ ወመፋራቲሆሙ ።

፲፩ ወኢያጥፍኦሙ ኤፍሬም ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ጋዜር ወነበሩ ከናኔዎን ውስተ ኤፍሬም እስከ ዮም ወኮኑ መጸብሐ ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

፩ ወኮነ ደወሎሙ ለነገደ ደቂቀ ምናሴ እስመ ውእቱ በኵሩ ለዮሴፍ ወማኪር በኵሩ ለምናሴ አቡሁ ለገለአድ እስመ ብእሲ መስተቃትል ውእቱ ወኮነ ሎቱ ገለአድ ወበሳን ።

፪ ወኮነ ለደቂቀ ምናሴ እለ ተርፉ በበሕዝቢሆሙ ለደቂቀ ኢያዜ ፡ ወለደቂቀ ቄሎዜ ፡ ወለደቂቀ ኢየርያል ፡ ወለደቂቀ ኢሐኬም ፡ ወለደቂቀ አፌር ፡ እሉ ተባዕቶሙ በበሕዝቢሆሙ ።

፫ ወለሰልጰአድ ወልደ ኦፌር አልቦ ደቂቀ ዘእንበለ አዋልድ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆን መሐላ ፡ ወኑኃ ፡ ወሔግላ ፡ ወሚልካ ፡ ወቴርሳ ።

፬ ወቆማ ቅድመ አልአዛር ካህን ወቅድመ ኢያሱ ወቅድመ መላእክት ወይቤላ እግዚአብሔር አዘዘ በእደ ሙሴ ከመ ይሀቡነ ርስተነ በማእከለ አኀዊነ ወወሀብዎን በትእዛዘ እግዚአብሔር ምስለ አኀዊሆን ለአቡሆን ።

፭ ወወድቀ ሐብለ ምናሴ ዐሠርቱ እንበለ ገለአድ ወበሳን ዘማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

፮ እስመ አዋልደ ደቂቀ ምናሴ ተዋረሳ በማእከለ አኀዊሆን ፡ ወምድረ ገለአድሰ ኮነት ለደቂቀ ምናሴ እለ ተርፉ ።

## ምዕራፍ ፲፮ ።

የዮሴፍ ልጆች ድንበራቸው በኢያሪኮ አንጻር ካለ ከዮርዳኖስ ከምሥራቁ ጀምሮ ነው ፡ ከኢያሪኮም ሎዛ ቤተ በሉች ቤቴል ወዳለ ምድረ በዳ ይደርሳል ።

ሎዛ ትባል ከነበረች ከቤቴል ወጥቶም ወደ ኬሮንቴ አጦሮጅ ይደርሳል ። ዘፍ፡ ፳፰ ፲፱ ።

በታች ባሉ በቤቶሮን አጦሮጅ ሰባት ወንዞች ወዳሉ በት ወደ ኬሮንቴ አጦሮጅ ይደርሳል ፡ ፍጻሜውም ባሕር ነው ። ኢያ፡ ፲ ፲፡ ፩ ፴፫ ።

የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍሬምም ወረሱ ።

በየወገኖቻቸው የኤፍሬም ልጆች አውራጃቸው ከኤሮንና ከአጣሮት ምሥራቅም ከጋዛራና ከታችኛይቱ ቤቶሮን ጀምሮ ነው ፡ ኢያ፡ ፲፮ ፯ ። ፩ ዜና መዋ፡ ፯ ፳፱ ።

ከቶርማ ቀኝ ጀምሮ ወደ ባሕር ይደርሳል ፡ በኤላስና በቴርናታም ወደ ምሥራቅ ይደርሳል ። ኢያ፡ ፲፮ ፯ ።

ከምሥራቁም ወደ መራክና ወደ ኢያኖክ ወደ አጣሮትም ከመንደሮቻቸው ጋራ ይደርሳል ።

ወደ ኢያሪኮም ይገባል ወደ ዮርዳኖስም ይወጣል ።

ከእምጣፉ በኬልቃና ላይ ወደ ባሕር ይደርሳል ፡ ፍጻሜውም ባሕር ነው ፡ በየወገኖቻቸው የኤፍሬም ወገኖች ርስታቸው ይህ ነው ። ኢያ፡ ፲፱ ፲፫ ።

በምናሴ ልጆች ርስት መካከል ለኤፍሬም ልጆች የለዩላቸው አገሮችም ከመንደሮቻቸው ጋር አገሮቻቸው ሁሉ እነዚህ ናቸው ። ኢያ፡ ፲፯ ፱ ።

ኤፍሬም በጋዜር የሚኖሩ ከናኔዎንን አላጠፋቸውም ከናኔዎንም እስከ ዛሬ ድረስ በኤፍሬም ውስጥ ኖሩ ፡ ገባርም ሆኑ ። መሳ፡ ፩ ፳፱ ። ፩ ነገ፡ ፱ ፲፮ ።

## ምዕራፍ ፲፯ ።

የዮሴፍ የበኩር ልጅ ይህ ነውና የምናሴ ልጆች ድንበራቸው ይህ ነው ፡ ለምናሴ ለበኩር ልጁ ለገለዓድ አባት ለማኪር አርበኛ ሰው ነውና ገለዓድ ከበሳን ጋር ለሱ ሆኑ ።

በየወገናቸው ለቀሩ ለምናሴ ልጆች ለቄሎዜ ልጆችና ለኢያዜ ልጆች ፡ ለኢሐኬም ልጆችና ፡ ለኢየርያል ልጆች ፡ ለኦፌርም ልጆች ሆነ ፡ በየወገኖቻቸው ወንዶች እነዚህ ናቸው ። ዘኍ፡ ፳፮ ፳፱ - ፴፪ ።

ለኦፌር ልጅ ለሰለጰአድም ከሴቶች ልጆች በቀር ወንድ ልጅ አልነበረውም ስማቸውም ይህ ነው ፡ መሐላ ፡ ኑኃ ፡ ሔግላ ፡ ሚልካ ፡ ቴርሳ ፡ ይባላል ።

በኢያሱና በሊቀ ካህናቱ በአልአዛር ፊት በአለቆችም ፊት ቆመው በወንድሞቻችን መካከል ርስታችንን ይሰጡን ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አዘዞን ነበር ፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ከአባታቸው ወንድሞች ጋራ ሰጧቸው ።

በዮርዳኖስ ማዶ ካለው ከበሳንና ከገለዓድ በቀር የምናሴ ዕጣ ዓሥር ሆኖ ወደቀ ። ኢያ፡ ፲፱ ፭ ።

የምናሴ ልጅ የሰለጰአድ ልጆች በወንድሞቻቸው መካከል ርስት ወርሰዋልና ፡ ገለዓድ ግን ለቀሩት ለምናሴ ልጆች ሆነች ።

፯ ወከነ ደወሎሙ ለደቂቀ ምናሴ እምአሴሩ ዴላናታ እንተ ቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ ሴኬም ፤ ወየሐውር ላዕለ ደወሎሙ ለኢያሚን በውስተ ኢያቢስ ዲብ ነቅዐ ተፍቶት ።
፰ ወከነ ለምናሴ ጣፌት ፤ ወጣፌትሰ ኀበ ደወሎሙ ለደቂቀ ምናሴ ወለደቂቀ ኤፍሬም ።
፱ ወይወርድ ደወሎሙ ላዕለ ቈላተ ቃሬና ዘኀበ አዜብ ወዲበ ቈላተ ኢያርያል ወጤሬምንቶን ዘኤፍሬም ማእከለ አህጉረ ምናሴ ፤ ወደወሉሂ ለምናሴ ላዕለ መስዕ እንተ ኀበ ፈለግ ።
፲ ወከነ ሞጻእቱ ባሕር እንተ መንገለ አዜቡ ለኤፍሬም ወዘኀበ መስዑ ለምናሴ ወይከውን ባሕር ወሰኖሙ ፤ ወበአሴር ይትራከቡ በመስዕ ወበይሳኮር እምጽባሕ ።
፲፩ ወይከውን ለምናሴ በይሳኮር ወበአሴር ቤተ ሳን ወሙፋሬቲሆን ወእለ ይነብሩ ውስተ ዶር ወሙፋሬቲሃ ወእለ ይነብሩ ውስተ ጌዳ ወሙፋሬቲሃ ፤ ወሣልስተ እጁሃ ለመፌታ ወሙፋሬቲሃ ።
፲፪ ወስእኑ ደቂቀ ምናሴ አጥፍኦቶን ለአላንቱ አህጉር ፤ ወመጽኡ ከናኔዎን ይንበሩ ውስተ ይእቲ ምድር ።
፲፫ ወጸንዕዎሙ እስራኤል ወቀነይዎሙ ወኢያጥፍኦ በሕቁ ኢያጥፍእዎሙ ።
፲፬ ወተዋቀስዎ ደቂቀ ዮሴፍ ለኢያሱ ወይቤልዎ በበይነ ምንት አውረስከነ አሐደ ርስተ ወአሐደ ሐብለ እንዘ ብዙኃ ሕዝብ ንሕነ ወእግዚአብሔር ባረከነ ።
፲፭ ወይቤሎሙ ዕርጉ ኀበ ኢያርምር ወአንጽሕዎ ለክሙ እመ ይጸብበክሙ ደብረ ኤፍሬም ።
፲፮ ወይቤሉ ኢየአክለነ ደብረ ኤፍሬም ወከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስቴቱ በሙ አፍራስ ኀሩያን ወሐፂን በቤቴል ወበሙፋሬቲሃ በቈላተ ኢይዝራኤል ።

፲፯ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ ዮሴፍ እስመ ብዙኃ ሕዝብ አንተ ወብከ ዐቢይ ኀይል ወኢይከውንከ አሐዱ ርስት ።
፲፰ እስመ ደብር እከ ውእቱ እስመ ገዳም ውእቱ ወታነጽሖ እከ ወይከውንከ እስከ ታጠፍኦሙ ለከናኔዎን እስመ ሠረገላ ሐፂን ቦሙ ወጽኑዕ ውእቱ ወአፍራስ ኀሩያን ቦሙ ወለሊከ ጸናዕከሆሙ ።

የምናሴ ልጆች ድንበር በሴኬም ልጆች አፍዝዣ ከለች ከአሴሩ ዴላታ ጀምሮ በተፍቶት ምንጭ በለች በኢያቢስ በኩል ወደ ኢያሚን አውራጃ ይደርሳል ።
ጣፌት ለምናሴ ሆነ ፤ ጣፌት ግን በኤፍሬም ልጆችና በምናሴ ልጆች አውራጃ ያለ ነው ። ፩ ነገ፡ ፲፪ ፳፭ ።
በአዜብ ወዳለች ወደ ቃሬና ቈላ የኤፍሬም ዕጣ ወደ ምትሆን ወደ ጤሬምንቶንና ወደ ኢያርያል ቈላም ይደርሳል ፤ ይህም በምናሴ አገሮች መከከል ያለ ነው ፤ የምናሴም ድንበር ወንዝ ባለበት በመስዕ በኩል ነው ።
ፍጻሜውም በምናሴ ዕጣ ቀኝና በኤፍሬም ዕጣ ግራ ያለ ባሕር ነው ፤ ወሰናቸው ባሕር ነው ፤ ከአሴርም ጋር በቀኝ ይገናኛሉ ፤ ከይሳኮርም ጋራ በመስዕ በኩል ይገናኛሉ ።
የምናሴ ዕጣ በአሴርና በይሳኮር ዕጣ ነው ፤ ቤተሳን ከመሠማሪያዋ ጋር በዶር የሚኖሩ ሰዎች ከመሠማሪያዋ ጋራ በጌዳ የሚኖሩ ሰዎች ከመሠማሪያዋ ጋር የመፌቷም ሢሶ ከመሠማሪያዋ ጋራ ለምናሴ ሆኑ ። ፩ ዜና መ፡ ፯ ፳፱ ።
የምናሴም ልጆች እነዚያን አገሮች ማጥፋት ተሳናቸው ከናኔዎንም በዚያች አገር ይኖሩ ዘንድ ወደዱ ።
እስራኤልም በርትተው ገዟቸው ፤ ነገር ግን ፈጽመው አላጠፉዋቸውም ። ኢያ፡ ፲፮ ፱ ፤ መሳ፡ ፲፫ ፳ ።
የዮሴፍ ልጆች ኢያሱን እኛ ብዙ ወገን ስንሆን እግዚአብሔር ሲያበዛረን ስለምን አንድ ዕጣ አንድ ርስት አወረስከን ብለው ወቀሱት ። ዘፍ፡ ፴፫ ፳-፳፪ ።
(እሱም) የኤፍሬም ዕጣ ከጠበበችሁ ወደ ኢያርምር ወጥታችሁ አቅኗት አላቸው ። ኢያ፡ ፲፮ ፲፯-፲፰ ።
(እነሱም) የኤፍሬም ዕጣ አይበቃንም ፤ ነገር ግን በእነርሱ የሚኖሩ ከናኔዎን የተመረጡ ፈረሶች አሏቸው ፤ በኢይዝራኤል ቈላም በመሠማሪያዋና በቤቴል ጦር አላቸው አሉ ።
ኢያሱም የዮሴፍን ልጆች አንተ ብዙ ወገን ነህና ብዙ ሠራዊትም አለህና አንድ ርስት አይበቃህም አላቸው ።
ምድረ በዳ ስለሆነ አውራጃው ላንተ ይሁን ፤ ላንተ ምሏት አድርገው የብረት ሠረገላ አላቸውና እሱም (ሠረገላው) ጽኑ ነውና የተመረጡ ፈረሶችም አሏቸውና አንተም አጽንተህ ገዝተሃቸዋልና ከናኔዎንን እስክታጠፋቸው ድረስ ላንተ ይሁን አለው ። ኢያ፡ ፲፩ ፯ ።

ምዕራፍ ፲፰ ።

፩ ወተጋብኡ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ሴሎ ወተክልዋ ለህየ ለደብተራ መርጡል ወአጽንዕዋ ለምድር እሙንቱ ።
፪ ወተርፉ ደቂቀ እስራኤል እለ ኢተዋረሱ ሰብዓቱ ነገድ ፤
፫ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል እስከ ማእዜኑ ታቴንሑ ለምድር ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክ ከመ ኢትትዋረስዋ ።
፬ አውስኡ እምውስቴትክሙ ሠለስተ አደወ እምነገድ ነገድ ፤ ወይትንሥኡ ያዑድዋ ለምድር ወይጽሐፍዋ ከመ ያድልዋ ፤ ወይርአይዋ ፤ ወይፈልጽዋ ሰብዓተ መክፈልተ ወይምጽኡ ኀቤየ ።

የእስራኤል ልጆች በሴሎ ተሰብስበው ደብተራ ኦሪትን በዚያ ተከሉት ፤ አገሪቱም ምድርን አጸኗት ።

ያልወረሱ የእስራኤል ልጆች ሰባት ነገድ ቀሩ ።
ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሰጣችሁ ምድርን ለመውረስ እስከ መቼ ድረስ ታቈያላችሁ ፤ አላቸው ። መሳ፡ ፲፰ ፱ ። ኢያ፡ ፲፩ ።
ከየነገዱም ሦስት ሦስት ሰዎች አውጡ ተነሥተው ምድሪቱን ይዞሩዋት ፤ እንደ ርስታቸውም ይጻፏት ወደ እኔም ይመለሱ ፤ ... ተከፈለች አላቸው ። ኢያ፡ ፲፰ ፩ ።

፭ ወኢቀመ ሎቱ ይሁዳ ደወሎ መንገለ አዜብ ወደቂቀ ዮሴፍ አቀሙ ደወሎሙ መንገለ መስዕ።

፮ ወአንትሙሰ ክፍልዋ ለምድር ሰብዐተ ክፍለ ወአምጽኡ ኀቤየ ዝየ ወአበውእ ለክሙ ርስተ።

፯ ወአወፅእ ለክሙ ዝየ ዕፃ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ፤ እስመ አልቦሙ ክፍል ለደቂቀ ሌዊ ምስሌክሙ እስመ ክህነቱ ለእግዚአብሔር ክፍሎሙ።

፰ ወጋድሰ ወሮቤል ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ነሥኡ ርስቶሙ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ጽባሐዊ ዘወሀቦሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር።

፱ ወተንሥኡ እሙንቱ እደው ወሖሩ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለእለ የሐውሩ ይዑድዋ ለምድር ወይቤሎሙ ሑሩ ዑድዋ ለምድር ወጸሐፍዋ ወግብኡ ኀቤየ ዝየ ከመ አውፅእ ለክሙ ዕፃ ቅድመ እግዚአብሔር በሴሎ።

፲ ወሖሩ ወዖድዋ ለምድር ወርእይዋ ወጸሐፍዋ ውስተ መጽሐፍ በበአህጉሪሃ ወአምጽኡ ኀበ ኢያሱ።

፲፩ ወአብአ ኢያሱ መክፈልቶሙ ቅድመ እግዚአብሔር በሴሎ።

፲፪ ወበጽሐ ክፍሉ ለብንያም ቅድመ በበሕዘቢሆሙ ወረከቦሙ ደወለ መክፈልቶሙ ማእከለ ደቂቀ ይሁዳ ወማእከለ ደቂቀ ዮሴፍ።

፲፫ ወኮነ ደወሎሙ ዘመንገለ ሰሜን እምዮርዳኖስ ወየዐርግ ላዕለ አዜብ ለኢያሪኮ እምሰሜን ወየዐርግ ላዕለ ደብር ዘኀበ ባሕር ወይከውን ሞጻእቱ ምድብራይጣስ ዘቤቶን።

፲፬ ወየኀልፍ እምህየ ላዕለ አድበረ ሎዛ እንተ ዘበነ ሎዛ እንተ ዲበ አዜብ እንተ ይእቲ ቤቴል ወይወርድ ላዕለ ደወለ አጣሮት ዘሆሬህ እንተ ላዕለ አድባር ዘመንገለ አዜብ ለቤቶሮን ታሕታይ።

፲፭ ወየኀልፍ ላዕለ አሐዱ ኅብር ዘይኔጽር መንገለ ባሕር ዘመንገለ አዜቡ ለደብር ዘቅድመ ቤቶሮን ዘቅድመ አዜብ ወይከውን ሞጻእቱ ላዕለ ቀርያትበዓል እንተ ይእቲ ቀርያታርም ሀገረ ደቂቀ ይሁዳ፤ ወዝንቱ ውእቱ ደወሎሙ ዘመንገለ ባሕር።

፲፮ ወደወሎሙኒ ዘመንገለ አዜብ እምቀርያትበዓል ወየኀልፍ ላዕለ ጋይን ዲበ ነቅዐ ማይ ዘነፍቶ።

፲፯ ወይወርድ ላዕለ አሐዱ ኅብር ዘቅድመ ናጺስናም ዘመንገለ ገበሃ ለኤምቅራፋይን ዘኀበ መስዕ ወይወርድ እምናጺን ዲበ ዘበነ ኢያቡሴ ዘኀበ አዜብ ወይወርድ ዲበ ነቅዐ ሮጌል።

፲፰ ወየኀልፍ ዲበ ነቅዐ ቤተሳሚስ ወይበውእ ዲበ ከልዮት እንተ ቅድመ ዐቀበ ኤታሚን።

፲፱ ወይወርድ ዲበ እብነ ቤዜዎን ዘደቂቀ ሮቤል፤ ወየኀልፍ ዲበ ዘበነ ቤተ ራባ ዘኀበ መስዕ ወይወርድ ላዕለ ፍናተ ባሕር ዘመንገለ መስዕ።

፳ ወይከውን ሞጻእቱ ለደወሎሙ ላዕለ ፍኖተ ባሕር ዘአሎን ዘመንገለ መስዕ ወገበሁ ለዮርዳኖስ ዘኀበ አዜብ ዝንቱ

ይሁዳም ድንበሩን በአዜብ አጸና፤ የዮሴፍም ልጆች ድንበራቸውን በመስዕ አጸኑ። ኢያ፣ ፲፯ ፱።

እናንተ ግን ምድሪቱን ሰባት ዕጣ አድርጋችሁ ክፈሏት፤ ከዚያም ወደኔ አምጡ፤ ርስት አድርጌ አገባላችኋለሁ።

የእግዚአብሔር ክህነቱ ዕጣቸው ስለሆነ የሌዊ ልጆች ከናንተ ጋራ ዕጣ የላቸውምና በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አወጣላችኋለሁ።

ሮቤልና ጋድ የነገደ ምናሴ እኩሌታ ግን በምሥራቅ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ የእግዚአብሔር በለሟል ሙሴ የሰጣቸውን ርስት ተቀበሉ አላቸው። ዘኍ፣ ፲፰ ፴፫።

እነዚያም ሰዎች ተነሥተው ሄዱ፤ ኢያሱም ምድርን ይዞሩዋት ዘንድ የሚሄዱትን ሰዎች ሂዱ ምድሪቱን ዞራችሁ ጽፋችኋት በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አወጣላችሁ ዘንድ እዚህ ወደኔ ተመለሱ ብሎ አዘዛቸው።

(እነሱም) ሄደው ምድሪቱን ዞሯት በየአገሩም አይተዋትና በመጽሐፍ ጽፈዋት ወደ ኢያሱ አመጡ።

ኢያሱም በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣቸውን አገባ።

የብንያም ዕጣ በየወገኑ አስቀድሞ ወጣ፡ በዮሴፍ ልጆች መካከልና በይሁዳ ልጆች መካከል ዕጣቸው የወደቀበትን አገር አገኙ።

ድንበራቸውም ከዮርዳኖስ ጀምሮ በሰሜን ሆነ፤ ከሰሜንም ጀምሮ ወደ ኢያሪኮ ግራ ይደርሳል፤ በባሕር ወዲያ ተራራም ይደርሳል፤ ፍጻሜውም የቤቶሮን ዕጣ የሚሆን ምድብራይጣስ ነው። ኢያ፣ ፲፮ ፩፣ ፯ ፪።

ከዚያም ይህችውም ቤቴል ናት፤ በአዜብ ወዳለች ወደ ሎዛ ተራራ ይደርሳል፤ በታችኛው ቤቶሮን ግራ (አዜብ) ባለ በተራራው ላይ የሆሬህ ዕጣ ወደ ምትሆን ወደ አጣሮት ይወርዳል። ኢያ፣ ፲፮ ፭፣ ፲ ፲።

በአዜብ አፍዛዣ ባለ በቤቶሮን አፍዛዣ ባለ በተራራው ግራ (አዜቡ) ወዳለ ወደ ባሕር ወደሚወስድ ወደ አንድ ወገን ይደርሳል፤ ይህችውም የይሁዳ ልጆች አገር ቀርያታርም ናት፤ ፍጻሜውም ቀርያትበዓል ነው፤ በባሕር በኩል ድንበራቸው ይህ ነው።

ከቀርያትበዓልም በአዜብ በኩል ድንበራቸው ይህ ነው፤ በነፍቶ ውኃ ምንጭ ወዳለ ወደ ጋይን ይደርሳል።

በመስዕ በኩል ወዳለች በኤምቅራፋይን ጐን ወዳለ በናጺስናም ፊት ለፊት ወዳለ ወዳንዱ ወገን ይወርዳል፤ ከናጺንም በአዜብ አጠገብ ወዳለ ወደ ኢያቡሴ ይወርዳል፤ ወደ ሮጌል ምንጭም ይወርዳል። ፪ ነገ፣ ፳፫ ፲።

ወደ ቤተ ሳሚስም ምንጭ ይደርሳል፤ በኢታምን ዐቀበት ፊት ለፊት ወዳለ ወደ ከልዮትም ይገባል።

የሮጌል ልጆች ዕጣ ወደ ሚሆን ወደ ቤዜዎን ድንጊያ ይደርሳል፤ በመስዕ በኩል ወዳለ ወደ ቤተ ራባ ዠርባም ይደርሳል፤ በመስዕም በኩል ወደ ባሕር ወደ ሚወስደው መንገድ ይደርሳል። ኢያ፣ ፲፭ ፯። ፪ ሳሙ፣ ፲፭ ፳፫።

የድንበራቸውም ፍጻሜ በመስዕ በኩል ካለ ከአሎን ባሕር መንገድ ይደርሳል፤ በአዜብም በኩል ድንበራቸው

ደወለ አዜብ ።
፳፩ ወዮርዳኖስ ወሰኖሙ እመንገለ ጽባሕ ወዝንቱ ውእቱ ደወሎሙ ዘዐውዶሙ ለደቂቀ ብንያሚ በበሕዝቢሆሙ ዘተዋረሱ ።
፳፪ ወከና አህጉሪሆሙ ለደቂቀ ብንያሚ በበሕዝቢሆሙ ዘተዋረሱ፡ ኢያሪኮ፡ ወቤተግዎ፡ ወአመቀሰስ፡ ወቤተባራ ወሰዓርታቤፋና ።
፳፫ ወአኢን፡ ወፋራ፡ ወኤፍራታ፡ ወቃሬፋ፡ ወቂፋራ፡ ሞኢ፡ ወንባሕ፡ ዐሥሩ ወክልኤቲ አህጉር ወመፋሬቲሆን ።
፳፬ ገባዖን፡ ወራማ፡ ወማሴማ፡ ወቤሮን፡ ወምቄ፡ ወቤራ፡ ወቃፋን፡ ወቃና ።
፳፭ ወሴሌቃን፡ ወቴርስላ፡ ወኢያቡሴዎን፡ እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም፡ ወገበአን፡ ወሀገረ ኢያሪን፡ ዓሥሩ ወሠላስ አህጉር፡ ወመፋሬቲሆን ።
፳፮ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለደቂቀ ብንያሚን በበሕዝቢሆሙ ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ወበጽሐሙ ለደቂቀ ስምዖን ክልእ ክፍል ወኮነ ርስቶሙ ውስተ ማእከሎሙ ለደቂቀ ይሁዳ ።
፪ ወረከበሙ መክፈልቶሙ ቤርሳቤሕ፡ ወሰማሕ፡ ወቆሎዶን ወአርሳበ፡ ወበላ፡ ወኢያሰን ።
፫ ወልዑላ፡ ወቡል፡ ወኤርማ፡ ወሴቅላቅ፡ ወቤተ ማከሬብ፡ ወሰርሰኤን፡ ወአበታሩት፡ ዐሠሩ ወሠላስ አህጉር፡ ወመፋሬቲሆን ።
፬ ሬሞን፡ ወቴልክ፡ ወኢያቴር፡ ወአሣ፡ አርባዕ አህጉር ወመፋሬቲሆን፡ ዘዐውዶን ለእላንቱ አህጉር እስከ ባሌቅ ።
፭ ወየኀልፍ ላዕለ ባሚት ዘመንገለ አዜብ፡ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ስምዖን ።
፮ እስመ ኮነ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ይሁዳ ዓቢየ እምኢአሆሙ፡ ወወረሱ ደቂቀ ስምዖን ማእከለ መክፈልቶሙ ።
፯ ወረከበሙ ማልስ መክፈልት ለደቂቀ ዛብሎን በበሕዝቢሆሙ፡ ወኮነ ደወለ ርስቶሙ ኤሴዴቅ ወኀላ እምባሕር ወመግሬላ ።
፰ ወይትአኀዝ ምስለ ቤተ ራበ ዘውስተ ቄላት እንተ ቅድመ ገጹ ለኢያቃምን ።
፱ ወተመይጠ እምሰዴቅ ላዕለ ቅድመ ጽባሒሁ ለቤተ ሳሚስ ዲበ ደወለ አካሲሎቴት ።
፲ ወየኀልፍ እንተ ዳቤሮት፡ ወየዓርግ ላዕለ ፈጢ፡ ወየኀልፍ ዘቅድመ ጽባሒሁ ለሀገረ ጌቤር፡ እንተ ኀበሴም ወየኀልፍ ዲበ ሬሞን ዘአምተርዮዘ ።
፲፩ ወየኀልፍ ላዕለ መስዓሞት፡ ወይከውን ሞፃእቶሙ ላዕለ ጌፋሄል፡ እንተ ኀበ ናቲ ።
፲፪ ወናበሕል፡ ወሲሞዖን፡ ወዳኤል፡ ወሜቴሚን ዐሥሩ ወክልኤቲ አህጉር፡ ወመፋሬቲሆን ።
፲፫ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ዛብሎን በበሕዝቢሆሙ፡ እላ አህጉር ወመፋሬቲሆን ።
፲፬ ወረከበሙ ለደቂቀ ይሳኮር ራብዕ መክፈልት ።

ዮርዳኖስ ነው፡ በአዜብም በኩል ድንበራቸው ይህ ነው።
፳፩ በምሥራቅም በኩል ድንበራቸው ዮርዳኖስ ነው፡ በየወገናቸው የወረሱት የብንያም ልጆች ድንበራቸው ይህ ነው ።
፳፪ በየወገናቸው የብንያም ልጆች የወረሷቸው አገሮቻቸው ቤተግዎና ኢያሪኮ፡ ቤተ ራባና አመቀሰስ ሰዓርታቤፋና ።
፳፫ አኢን፡ ፋራ፡ ኤፍራታ፡ ቃሬፋ፡ ቂፋራ፡ ሞኢ፡ ንበሕ፡ ከመሠማሪያቸው ጋራ ዓሥራ ሁለት አገሮች ናቸው ።
፳፬ ገባዖን፡ ራማ፡ ማሴማ፡ ቤሮን፡ ምቄ፡ ቤራ፡ ቃፋን፡ ቃና ። ኢያ፡ ፱ ፫ ። መሳ፡ ፬ ፭ ።
፳፭ ሴሌቃን፡ ቴርስላ፡ ኢያቡሴዎን ይህችም ኢየሩሳሌም ናት፡ ገባዖን የኢያሪን አገር ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ ሦስት አገሮች ናቸው ። ኢያ፡ ፲፭ ፲፮ ።
፳፮ በየወገናቸው የብንያም ልጆች ርስታቸው ይህ ነው ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩ ለስምዖን ልጆች ሁለተኛ ዕጣ ደረሳቸው ርስታቸውም በይሁዳ ልጆች መካከል ነው ። ኢያ፡ ፲፱ ፱ ።
፪ ዕጣቸውም ቤርሳቤሕ፡ ሰማሕ፡ ቆሎዶን፡ አርሳበ፡ በላ፡ ኢያሰን ። ኢያ፡ ፲፱ ፰ ። ፩ ዜና መ፡ ፬ ፳፰ - ፴፫ ።
፫ ቡል፡ ልዑላ፡ ኤርማ፡ ሴቅላቅ፡ ቤተማከሬብ፡ ሰርሰኤን፡ አበታሩት፡ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ ሦስት አገሮች ናቸው ። ዘኍ፡ ፳፩ ፫ ።
፬ ሬሞን፡ ቴልክ፡ ኢያቴር፡ አሣ፡ እስከ ባሌቅ ድረስ በነዚህ አገሮች ዙርያ ካሉ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ አራት አገሮች ናቸው ። ኢያ፡ ፲፭ ፵፪ ።
፭ በአዜብ በኩል ወደ ባሚት ያልፋል (ይደርሳል) የነገደ ስምዖን ርስታቸው ይህ ነው ። ኢያ፡ ፲፭ ፳፬፡ ፳፱ ፩ ።
፮ የይሁዳ ልጆች ዕጣ ከነሱ ዕጣ የበዛ ሆኗልና፡ የስምዖን ልጆች በነሳቸው ዕጣ መካከል ወረሱ ።
፯ ለዛብሎንም ልጆች በየወገናቸው ሦስተኛ ዕጣ ደረሳቸው የርስታቸውም ዳርቻ በምዕራብ በኩል ከመግሬላና ከባሕር ጀምሮ ኀላና ኤሴዴቅ ናቸው ።
፰ በኢያቃምን አንጻር ቈላ ካለች ከቤተ ራብ ጋራ የተያያዘ ነው ። ዘፍ፡ ፵፱ ፲፫ ። ኢያ፡ ፲፱ ፲፫፡ ፲፪ ፳፪ ።
፱ ከሰዴቅ በከሲሎቴት ዳርቻ ላይ በቤተ ሳሚስ ምሥራቅ ፊት ለፊት ላይ ይመለሳል ። ኢያ፡ ፲፱ ፳ ።
፲ ወደ ዳቤሮት ይደርሳል፡ ወደ ፈጢም ይወጣል፡ በኀበሴም ወዳለ ወደ ጌቤር አገር ምሥራቅ አንጻር ይደርሳል የዘአምተርዮዘ ዕጣ ወደ ምትሆን ወደ ሬሞንም ያልፋል ።
፲፩ ወደ መስዓሞት ይደርሳል፡ ፍጻሜውም በኀበናት ወዳለ ወደ ጌፋሄል ነው ።
፲፪ ናበሕል፡ ሲሞዖን፡ ዳኤል፡ ሜቴሚን፡ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ዓሥራ ሁለት አገሮች ናቸው ።
፲፫ በየወገናቸው የነገደ ዛብሎን ልጆች ርስት ይህ ነው፡ እነዚህም አገሮች ከመሠማሪያቸው ጋራ እሊህ ናቸው ።
፲፬ ለይሳኮርም ልጆች አራተኛ ዕጣ ደረሳቸው ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org



፲፭ ወከነ ደወሎሙ ኢይዝራኤል ወከለስሎት ወሱሳን፣
ወአጊን፣ ወሲዎናን፣ ወርኄቱ ።
፲፮ ወአንክሬት፣ ወዳቤራት፣ ወቂሶን፣ ወሮቤስ ።
፲፯ ወሬማን፣ ወኤማሬቅ፣ ወቤርሳቤሕ ።
፲፰ ወይትአኃዝ ደወሎሙ በታቦር ወላዕለ ሰሌም እንተ
መንገለ ባሕር፣ ወቤተ ሳሚስ ።
፲፱ ወይከውን ሞፃእተ ደወሎሙ ዮርዳኖስ፣ ዐሠርቱ ወስ
ድስቱ አህጉር ወሙፋሬቲሆን ።
፳ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ይሳኮር፣ በበ
ሕዘቢሆሙ፣ ወአህጉሪሆሙኒ ወአዕፃዳቲሆሙኒ ።
፳፩ ወረከበሙ ሐምስ መክፈልት ለደቂቀ አሴር ።
፳፪ ወከነ ደወሎሙ፣ እምኤልኬት፣ ወኤሌፍ፣ ወቤቶቅ፣
ወአቂያፉ፣ ወአሊሚሊ፣ ወአሚኄል፣ ወማሕሳ ።
፳፫ ወይትአኀዝ በቀርሜሎስ፣ ዘመንገለ ባሕር፣ ወበሴዎን፣
ወለበንት፣ እምጽበሒሁ ወይገብእ በቴኄኔት ።
፳፬ ወይትአኃዝ በዛብሎን ወእምጌጊ፣ ወፍትሔል ዘመን
ገለ መስዕ ።
፳፭ ወይበውእ ደወሎሙ ውስተ ሰፍቱ፣ ቤታሚህ፣ ወኢ
ንሂል፣ ወየኃልፍ ውስተ ክበም ወአሴሜል ።
፳፮ ወኤብሮን፣ ወራዓብ፣ ወአሜማህን፣ ወቀንታሌዎን፣
እስከ ሲዶና ዓቢይ ።
፳፯ ወይገብእ ደወሎሙ ውስተ አራማ፣ ወእስከ ሀገረ ቅ
ጽረ ጢሮስ ወይገብእ ደወሎሙ ውስተ ኢያሰፍ ።

፳፰ ወይከውን ደወለ ሞፃእቱ፣ ባሕር እምነ ሌብ፣ ወከዛብ ።

፳፱ ወአርከብ፣ ወአፌቅ፣ ወረዓው፣ ዕሥራ ወክልኤቱ አህ
ጉር፣ ወሙፋሬቲሆን ።
፴ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ አሴር፣ በበሕ
ዘቢሆሙ፣ ወአህጉሪሆሙኒ ወሙፍሬቲሆሙ ።
፴፩ ወረከበሙ ለደቂቀ ንፍታሌም ሳድስ ክፍል ።
፴፪ ወከነ ደወሎሙ መሐላም፣ ወሞላ፣ ወቤሴሜይን፣ ወአ
ርሜ፣ ወኖብ፣ ወኢያፍታሜን፣ እስከ አዕዳላን፣ ወከነ ሞፃ
እቱ ዮርዳኖስ ።
፴፫ ወይገብእ ደወሎሙ ላዕለ እናብትሮን፣ ወየኃልፍ እም
ህየ ላዕለ አቃናቃ፣ ወይትአኃዝ በዛብሎን እመንገለ አዜብ ።

፴፬ ወአሴርኒ ይትአኃዝ መንገለ ባሕር ወበይሁዳ ወዮርዳ
ኖስ እመንገለ ጽባሕ ።
፴፭ ወአህጉረ ሲዶና እለ ቅጽር በን ወጢሮስ ወእምዱቀቅ
ወቂሬት ወአርሜት፣ ወአራሂን ።
፴፮ ወአስር፣ ወቃዴስ ወአስራይስ፣ ወነቅዐ አሶር ወቆሬ፣
ወሚጋላህርም፣ ወቤታሚ፣ ወታስሚስ፣ ዐሠርቱ ወተስ
ዐቱ አህጉር፣ ወሙፋሬቲሆን ።
፴፯ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ንፍታሌም ።
፴፰ ወረከበሙ ለደቂቀ ዳን ሳብዕ ክፍል፣ ወከነ ደወሎሙ
ሰራሕት፣ ወአሣ፣ ሀገረሰማውስ፣ ወሰላቢን፣ ወዓሞን፣
ወሴላታ ።

አውራጃዎቻቸውም ኢይዝራኤል ከለስሎት፣ ሱሳን፣
አጊን፣ ሲዎናን ርኄቱ ። ኢያ፣ ፲፯ ፲፯ ። ፩ ሳሙ፣ ፳፰ ፬ ።
አንክሬት፣ ዳቤራት፣ ቂሶን፣ ሮቤስ ።
ሬማን፣ ኤማሬቅ፣ ቤርሳቤሕ ናቸው ።
ድንበራቸውም በባሕር አንጻር ባለች በሰሌም ላይና
በታቦር በቤተ ሳሚስም ይያያዛል ።
የድንበራቸውም ፍጻሜ ዮርዳኖስ ነው፣ እነዚህም
ከመሠማሪያቸው ጋራ ዓሥራ ስድስት አገሮች ናቸው ።
በየወገኖቻቸው በየአገሮቻቸው በየአውራጃዎቻቸው
የነገደ ይሳኮር ልጆች ርስታቸው ይህ ነው ።
ለአሴርም ልጆች አምስተኛ ዕጣ ደረሳቸው ።
አውራጃዎቻቸውም ከኤልኬት፣ ኤሌፍ፣ ቤቶቅ፣ አቂ
ያፉ፣ አሊሚሊ፣ አሚኄል፣ ማሕሳ ጀምሮ ነው ።
በሴዎንና በባሕር አንጻር ከምሥራቁም ከለበንት ከቀ
ርሜሎስ ጀምሮ ወደ ቴኄኔት ይመለሳል ።
ከጌጊና ከዛብሎን በመስዕ አንጻር ካለ ከፍትሔልም
ይያያዛል ።
ወሰናቸውም ወደ ሰፍቱ፣ ወደ ቤታሚህና ወደ ኢን
ሄል ይገባል፣ ወደ አሴሜልና ወደ ክበም ይደርሳል ።
ወደ ራዓብና ወደ ኤብሮን፣ ወደ ቀንታሌዎንና ወደ
አሜማህን ሰፈ ወደሆነ እስከ ሲዶና ይደርሳል ።
አውራጃቸውም ወደ አራማ ይመለሳል፣ እስከ ጢሮስ
ቅጽር አምባ ድረስ ይደርሳል፣ ድንበራቸውም ወደ ኢያ
ሰፍ ይመለሳል ።
የፍጻሜያቸውም ድንበር ከከዛብና ከሌብ ያለ ባሕር
ነው ። ኢያ፣ ፲፰ ፵፪ ። ፪ ሳሙ፣ ፳ ፲፩ ።
አፌቅና አርከብ፣ ረዓው ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ሃያ
ሁለት አገሮች ናቸው ። ኢያ፣ ፲፩ ፲፰፣ ፲፱ ፲፰ ።
በየወገኖቻቸው በየአገሮቻቸው በየመሠማሪያዎቻቸው
የነገደ አሴር ልጆች ርስት ይህ ነው ።
ለንፍታሌም ልጆች ስድስተኛ ዕጣ ደረሳቸው ።
አውራጃዎቻቸው መሐላም ሞላ፣ ቤሴሜይን፣ አርሜ
ኖቢ፣ ኢያፍታሜን፣ እስከ አዕዳላን ድረስ እነዚህ ናቸው
ፍጻሜውም ዮርዳኖስ ነው ። መሳ፣ ፬ ፲፩ ።
ወሰናቸውም በአናብትሮን ባሕር ላይ ይመለሳል፣ ከዚ
ያም በአቃናቃ ላይ ያልፋል፣ በአዜብም በኩል ከዛብሎን
ይያያዛል ።
አሴርም በምዕራብ በኩል በስተምሥራቅ በኩል ባለ
በዮርዳኖስና በይሁዳ ይገናኛል ። ዘዳ፣ ፴፫ ፳፫ ።
ቅጽር ያላቸው የሲዶና አገሮችም እምዱቀቅና ጢሮስ
አርሜትና ቂሬት፣ አራሂን ። ኢያ፣ ፲፩ ፪ ።
አስር፣ ቃዴስ፣ አስራይስ፣ ነቅዐ አሶር፣ ቆሬ፣ ሚጋላ
ህርም፣ ቤታሚ፣ ታስሚስ፣ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ
ዓሥራ ዘጠኝ አገሮች እነዚህ ናቸው ።
የነገደ ንፍታሌም ልጆች ርስት ይህ ነው ።
ለዳን ልጆችም ሰባተኛ ዕጣ ደረሳቸው፣ አውራጃዎ
ቻቸውም ሰራሕት፣ አሣ፣ ሀገረሰማውስ፣ ሰላቢን፣ ዓሞን፣
ሴላታ ። መሳ፣ ፩ ፴፭ ።

፵፱ ወኤሎን ፡ ወቲምናታ ፡ ወአቃሮን ወለተቃታ ፡ ወጌቤቶን ፡ ወጌቤሌን ።

፶ ወአዘዘር ፡ ወቤኔቤዋቅ ፡ ወጌቴሬም ወእምባሕረ ኢያላቅን ደወል ዘቅሩበ ኢዮጴ ።

፶፩ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ዳን በበሕዘቢሆሙ ፡ ወአህጉሪሆሙ ወመንደሪሆን ።

፶፪ ወኢያጠቅዎሙ ደቂቀ ዳን ለአሞሬዎን ፡ እለ ያጠውቅዎሙ በውስተ ደብር ፡ ወኢያበውሕዎሙ አሞሬዎን ይረዱ ውስተ ቈላት ወነሥኡ እምኔሆሙ አሐደ ጎብረ እምደወለ መክፈልቶሙ ።

፶፫ ወሖሩ ደቂቀ ዳን ፡ ወቀተልዎሙ ለለኪስ ፡ ወነሥኡ ሀገሮሙ ፡ ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ፡ ወነበሩ ውስቴታ ወሰመዩ ስማ ዳን ፡ በስመ ዳን አቡሆሙ ።

፶፬ ወቆሙ አሞሬዎን ከመ ይንበሩ ውስተ ኤዶም ፡ ወውስተ ላሚን ፡ ወጸንዓት እዴሁ ለኤፍሬም ላዕሌሆሙ ፡ ወኮንዎሙ መጸብሐ ።

፶፭ ወሖሩ ይዑድዋ ለምድር በውስተ ደወሎሙ ፡ ወወሀብዎ ደቂቀ እስራኤል ክፍሎ ለኢያሱ በውስቴቶሙ በትእዛዘ እግዚአብሔር ።

፶፮ ወወሀብዎ ሀገረ ዘሰአለ ተምናማራህ ፡ ዘውስተ ደብረ ኤፍሬም ፡ ወነደቃ ለይእቲ ሀገር ወነበረ ውስቴታ ።

፶፯ ወዝንቱ ውእቱ አክፋሊሆሙ ፡ ዘከመ አስተዋረስዎሙ አልአዛር ካህን ወኢያሱ ወልደ ነዌ ፡ ወመላእክተ አበዊሆሙ ለነገደ እስራኤል በበመክፈልቶሙ ፡ በሴሎ በቅድመ እግዚአብሔር በኆበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል ወፈጸሙ ክፊለ ምድር ።

## ምዕራፍ ፳ ።

፩ ወነበበ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወይቤሎ ፡ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል ወበሎሙ ሀቡ አህጉረ ምስካይ ዘእቤለክሙ በእደ ሙሴ ።

፪ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ዘቀተለ ነፍሰ በኢያእምሮ እንዘ ኢይፈቅድ ፡ ወግበሩ ለክሙ አህጉረ ምስካይ ወይስኪ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ።

፫ ወይቁም ውስተ ኆኅተ አንቀጸ ሀገር ወይንግሮሙ ቃሎ ለሊቃናተ ይእቲ ሀገር ወያብእዎ ሰብአ ለይእቲ ሀገር ኀቤሆሙ ወየሀብዎ መከነ ወይንበር ምስሌሆሙ ።

፬ ወሶበ ዴገኖ አበ ደም ኢየግብእዎ ሎቱ ውስተ እዴሁ እስመ በኢያእምሮ ቀተሎ ለካልኡ ፡ ወእንዘ ኢይጸልኦ ቀዲሙ ።

፭ ወይንበር ውስተ ይእቲ ሀገር እስከ ይበጽሕ ቅድመ በውድ ይትሐተት ወእስከ አመ ይመውት ካህን ዐቢይ ዘህለወ በእማንቱ መዋዕል ።

፮ ወይእተ አሚረ ይገብእ ቀታሊ ወየአቱ ሀገር ውስተ ቤቱ ወውስተ ሀገር እንተ እምህየ ሰከየ ወኢይቀትሎ አበ ደም ለቀታሊ እስከ ይቀውም ቅድመ ዓውድ ወይትሐተት ።

፯ ወፈለጥዎ ለቃዴስ በውስተ ገሊላ በውስተ ደብረ ንፍታሌም ፡ ወሰሰኬም በውስተ ደብረ ኤፍሬም ፡ ወለሀገረ

ኤቤን ፡ ቴምናታ ፡ አቃሮን ፡ ለተቃታ ፡ ጌቤቶን ፡ ጌቤሉን ። ኢያ፡ ፳፩ ፳፫ ።

አዘዘር ፡ ቤኔቤዋቅ ፡ ጌቴሬም ፡ የኢዮጴ ፡ አቅራቢያ ከሚሆን ከኢያላቅን ባሕር ጀምሮ ይህ ነው ።

በየወገኖቻቸው በየአገሮቻቸው በየመሠማሪያዎቻቸውም የነገደ ዳን ርስታቸው ይህ ነው ።

በደጋ የሚያስጨንቋቸው አሞሬዎንን የዳን ልጆች በቈላ አላስጨነቋቸውም ወደ ቈላ ይወርዱ ዘንድ አሞሬዎን እየሰናብቷቸውም ነበር ፡ ከፈንታቸውም አውራጃ ከነሳቸው አንድ ወገኑን ያዙ ። ዘኁ፡ ፳፯ ፵፫ ። መሳ፡ ፩ ፴፬ ።

የዳን ልጆች ሄደው ለኪስን ወጉዋቸው ፡ አገራቸውንም አጅ አደረጉ ፡ በጦርም ወግተው በውስጧ ተቀመጡ ስሟንም በአባታቸው በዳን ስም "ዳን„ አሏት ።

አሞሬዎንም በላሚንና በኤዶም ይኖሩ ዘንድ ጸኑ ፤ የኤፍሬም ሥልጣን በነሳቸው ላይ ጸናች ገባሮችም ሆኑዋቸው ።

በአውራጃው ያለች አገርንም ይዞሯት ዘንድ ሄዱ ፤ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለኢያሱ በውስጣቸው ፈንታውን ሰጡት ። ኢያ፡ ፳፬ ፴ ።

በደብረ ኤፍሬም ያለ የለመነውን አገር ተምናማራሕን፡ ሰጡት ፡ ያችንም አገር ቀጽሮ በውስጧ ኖረ ።

የነዌ ልጅ ኢያሱና ካህኑ አልአዛር ከእስራኤል ነገድ አባቶች አለቆች ጋራ ልዩ በሆነች ድንኳን ደጃፍ ዘንድ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሴሎም በየፈንታቸው እንዳወረሱዋቸው አከፋፈላቸው ይህ ነው ፡ ምድርንም ከፍለው ጨረሱ ።

## ምዕራፍ ፳ ።

በሙሴ ቃል የነገርኋችሁን መማጠኛ አገሮችን ስጡ ፡ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ብሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ነገረው ።

ባለማወቅ ነፍስ የገደለ ሰው በዚያ ይማጠን ዘንድ ለናንተ መማጠኛ አገሮችን ሥሩ ፡ ነፍስን የገደለ ሰው ከነዚያ አገሮች በአንዲቱ አገር ይማጠን ።

በከተማውም በር ደጃፍ ቆሞ ለዚያች አገር ሽማግሎች ይንገራቸው የዚያችም አገር ሰዎች ወደነሱ አግብተው ቦታ ይስጡት ፡ ከነሳቸውም ጋራ ይኑር ።

ባለደም ቢከተለውም ቀድሞ ጠብ ሳይኖረው ባለማወቅ ባልንጀራውን ገድሎታልና አሳልፈው ለሱ በእጁ አይስጡት ። ዘዳ፡ ፴ ፪ ፡ ኢያ፡ ፳ ፫ ።

ሊመረመር ወደ አደባባይ እስኪደርስ ድረስ በዚያ ወራት ያለ ታላቁ ካህንም (ሊቀ ካህናት) እስኪሞት ድረስ በዚያች አገር ይኑር ።

ነፍስ የገደለ ሰው በዚያች ጊዜ ከተማጠነበት ከዚያ ቦታ ወዳገሩ ወደ ቤቱ ይመለስ ይመረመርም ዘንድ በአደባባይ እስኪቆም ድረስ ያገን ነፍስ ገዳይ ባለደሙ አይግደለው ፡ አለው ። ዘኊ፡ ፴፭ ፲፪ ፡ ፳፬ ፳፭ ።

በንፍታሌም አገር ዕጣ በገሊላ ያለ ቃዴስን ለዩት ፡ በኤፍሬም አገር ዕጣ ያለች ሴኬምን አርበቅ የምትባል

አርበቅ እንተ ይእቲ ኬብሮን በደብረ ይሁዳ ።

፰ ወበማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ እመንገለ ጽባሕ ወሀቡ ቦሶርሃ በሐቅለ ገዳም እምነገደ ሮቤል ወአርሞት በገለአድ እምነገደ ጋድ ፡ ወጋውሎን በባሳን እምነገደ ምናሴ ።

፱ አላንቱ ዘኀረዩ እምነገደ እስራኤል ወለግዩራኒ ዘሀለው ውስቴቶሙ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ኵሉ ዘቀተለ ነፍሰ ሰብእ በኢያእምሮ ከመ ኢይቅትሎ አበ ደም እስከ ይቀውም ቅድመ ዓውድ ወይትሐተት ።

ምዕራፍ ፳፩ ።

፩ ወመጽኡ መላእክቲሆሙ ለደቂቀ ሌዊ ኀበ አልአዛር ካህን ወኀበ ኢያሱ ወልደ ነዌ ወኀበ መላእክተ ነገደ አብያተ አበዊሆሙ ለሕዝበ እስራኤል በሴሎ በምድረ ከናአን ።

፪ ወይቤልዎሙ አዘዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ ከመ የሀቡነ አህጉረ ዘውስቴቶን ንነብር ወመጠፈራቲሆን ለእንስሳነ ።

፫ ወወሀብዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለሌዋውያን በትእዛዘ እግዚአብሔር እላንቱ አህጉረ ወመጠፈራቲሆን ።

፬ ወበጽሐሙ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ሕዝበ ቃዓት ፡ ወኮኑ ለደቂቀ አሮን ካህናት እምሕዝበ ይሁዳ ፡ ወእምሕዝበ ስምዖን ፡ ወእምሕዝበ ብንያም መክፈልቶሙ ዐሡሩ ወሠላስ አህጉር ።

፭ ወለደቂቀ ቀዓት እለ ተርፉ እምሕዝበ ኤፍሬም ፡ ወእምሕዝበ ዳን ፡ ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ መክፈልቶሙ ዐሠርቱ አህጉር ።

፮ ወለደቂቀ ጌድሶን እምነገደ ሕዝበ ይሳኮር ፡ ወእምሕዝበ አሴር ፡ ወእምሕዝበ ንፍታሌም ፡ ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ በባሳን መክፈልቶሙ ዐሡሩ ወሠላስ አህጉር ።

፯ ወለደቂቀ ሜራሪ በበሕዘቢሆሙ እምነገደ ሮቤል ፡ ወእምነገደ ጋድ ፡ ወእምነገደ ዛብሎን መክፈልቶሙ ዐሥሩ ወክልኤ አህጉር ።

፰ ወወሀብዎሙ ደቂቀ እስራኤል አህጉረ ለሌዋውያን ወመጠፈራቲሆን በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ለሙሴ መክፈልቶሙ ።

፱ ወወሀቡ ነገደ ደቂቀ ይሁዳ ወነገደ ደቂቀ ስምዖን እላንተ አህጉረ ።

፲ ወተሰምያ ለደቂቀ አሮን እምሕዝበ ቀዓት ወእምደቂቀ ሌዊ እስመ ሎሙ ኮነ መክፈልቶሙ ።

፲፩ ወወሀብዎሙ ምድረ ቀርያርበቅ ደብረ አህጉረ ኤናቅ እንተ ይእቲ ኬብሮን ዘደብረ ይሁዳ ወመጠፈራቲሃ ዘዐውዳ ።

፲፪ ወአሕቃላተ ሀገር ወአዕፃዳቲሃ ወሀብዎሙ ኢያሱ ለደቂቀ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ደወሎሙ ።

፲፫ ወለደቂቀ አሮን ካህን ወሀብዎሙ ሀገረ ምስካይ ለቀታሊ ኬብሮን ወመጠፈራቲሃ ፡ ወሎቤና ወመጠፈራቲሃ ።

አገርንም ለዩዋት ፡ ይህችውም በይሁዳ ተራራ ያለች ኬብሮን ናት ። ኢያ፡ ፲፱ ፴፯ ፡ ፲፱ ፯ ።

በስተምሥራቅም በኩል በኢያሪኮ አንጻር በለ በዮርዳኖስ ማዶ ከነገደ ሮቤል ዕጣ በምድረ በዳ ያለች ቦሶርን ሰጡ ፡ ከጋድም ነገደ በገለዓድ ያለች ሬሞትን ፡ ከነገደ ምናሴም በባሳን ያለች ጋውሎንን ሰጡ ።

ከነገደ እስራኤል የመረጧቸው እነዚህ ናቸው ፡ በእደ በባይ ቁሞ እስኪመረመር ድረስ ባለ ደም እንዳይገድለው ባለማወቅ ነፍስ የገደለ ሰው ሁሉ በዚያ ይማጠን ዘንድ በውስጣቸው ለሚኖር መጻተኛ መማጠኛን ሠሩ ።

ምዕራፍ ፳፩ ።

የሌዊ ልጆች አለቆች ከነዌ ልጅ ከኢያሱና ከካህኑ አልአዛር ከእስራኤል ወገኖች አበቶች ነገድ አለቆችም ዘንድ ከነዓን ከምትባል አገር ወዳለች ወደ ሴሎም መጡ ።

ከብቶቻችን የሚሠማሩባቸው መሠማሪያዎችንና የምንኖርባቸው አገሮችን ይሰጡን ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አዝዞን ነበር አሏቸው ። ዘኍ፡ ፴፭ ፪ ።

የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከመሠማሪያቸው ጋራ እነዚያን አገሮች ለሌዋውያን ሰጡዋቸው ።

ለቀዓት ልጆች ወገኖችም ፈንታቸው ደርሳቸው የአሮን ልጆች ካህናት ፈንታም ከስምዖን ወገኖችና ከይሁዳ ወገኖች ከብንያምም ወገኖች ሆኑ ፡ ፈንታቸውም ዓሥራ ሦስት አገሮች ናቸው ። ዘፀ፡ ፮ ፲፰ ። ኢያ፡ ፳፩ ፱ ።

ለቀሩት ለቀዓት ልጆችም ዕጣቸው ከዳን ወገኖችና ከኤፍሬም ወገኖች ሆነ ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ፈንታቸውም ዓሥር አገሮች ናቸው ።

የጌድሶንም ልጆች ዕጣ ከአሴር ወገኖችና ከይሳኮር ወገኖች ነገድ ፡ ከነገደ ምናሴም እኩሌታና ከንፍታሌም ወገኖች ሆነ ፡ በባሳን ያሉ ፈንታቸውም ዓሥራ ሦስት አገሮች ናቸው ። ኢያ፡ ፳፩ ፳፯ ።

በየወገኖቻቸው የሜራሪ ልጆች ዕጣም ከነገደ ጋድና ከነገደ ሮቤል ፡ ከነገደ ዛብሎንም ሆነ ፡ ፈንታቸውም ዓሥራ ሁለት አገሮች ናቸው ። ኢያ፡ ፳፩ ፴፪ ።

የእስራኤል ልጆች ፈንታቸውን ይሰጡዋቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ ለሌዋውያን ፈንታቸውን ሰጧቸው ።

የስምዖን ልጆች ነገድና የይሁዳ ልጆች ነገድ እነዚህን አገሮች ሰጡ ። ኢያ፡ ፳፩ ፬ ።

ፈንታቸው ሆነዋልና ከሌዊ ልጆችና ከቀዓት ልጆች ወገን ተለይተው የአሮን ልጆች ዕጣ ተባሉ ።

የኤናቅ አገሮች ተራራ የምትሆን ቀርያርበቅ የምትባለውን አገር ሰጧቸው ፡ ይህችውም በዙርያዋ ካለ ከእውራጃዋ ጋራ ፡ በይሁዳ ዕጣ ያለች ኬብሮን ናት ።

የአገሪቱንም አውራጃዎች ከመሠማሪያዎቿ ጋራ ኢያሱ ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ልጆች ሰጣቸው ።

ለካህኑ ለአሮን ልጆችም ነፍስ ለገደለ ሰው መማጠኛ ሊሆን መማጠኛ አገርን ሰጣቸው ፡ እነዚህም ኬብሮን ከአውራጃዋ ጋራ ሎቤና ከመሠማሪያዋ ጋራ ።

፲፬ ወአቴር ወመፋራታሃ፡ ወኤታም ወመፋራቲሃ።

አቴር ከመሠማሪያዋ ጋራ ኤታም ከመሠማሪያዋ ጋራ።

፲፭ ወሄሎን ወመፋራቲሃ፡ ወዳቤር ወመፋራቲሃ።

ሄሎን ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ዳቤር ከመሠማሪያዎቿ ጋራ። ኢያ፡ ፲ ፴፰፡ ፲፭ ፲፭። ፩ ዜና መ፡ ፮ ፶፰።

፲፮ ወናሰን ወመፋራቲሃ፥ ወዩጣ ወመፋራቲሃ፥ ወቤተ ሳሚስ ወመፋራቲሃ፡ ተስዑ አህጉር እምክልኤቱ ሕዝብ።

ናሰን ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ዩጣ ከመሠማሪያዎቿ ጋራ ቤተ ሳሚስ ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ከነዚህ ከሁለቱ ነገድ የተሰጡ እነዚህ ዘጠኙ አገሮች ናቸው። ኢያ፡ ፲፭ ፶፪።

፲፯ ወእምነገደ ብንያም ገበኦን ወመፋራቲሃ፥ ወጋማላቁ ወመፋራቲሃ።

ከነገደ ብንያም የተሰጡ አገሮች ገባዖን ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ጋማላቁ ከመሠማሪያዎቿ ጋራ።

፲፰ ወአናቶት ወመፋራቲሃ፥ ወአሌሞን ወመፋራቲሃ አርባዕቱ አህጉር።

አናቶት ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ አሌሞን ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ እነዚህ አራቱ አገሮች ናቸው።

፲፱ ወኵሎሙ አህጉሪሆሙ ለደቂቀ አሮን ካህናት ዐሥሩ ወሠለስ አህጉር፥ ወመፋራቲሃ ከማሁ።

አገልጋዮች የሆኑ የአሮን ልጆች አገሮች ሁሉ ዓሥራ ሦስት ናቸው፥ ከመሠማሪያዎቻቸው እንደዚያው ናቸው።

፳ ወለደቂቀ ቀዓት ሌዋውያን፥ እለ ተርፉ ኮና አህጉሪሆሙ እምሕዝበ ኤፍሬም፥ ወወሀብሙ ሀገረ ምስክይ ለቀታሊ።

ለቀሩት ለቀዓት ልጆች ለሌዋውያንም አገሮቻቸው ከኤፍሬም ወገን ዕጣ ሆኑ፥ ነፍስ ለገደለ ሰው መማጠኛ ሊሆን መማጠኛ አገር ሰጣቸው።

፳፩ ሴኬም ወመፋራቲሃ፥ ወቤቶሮን ወመፋራቲሃ፥ ጌዜር ወመፋራቲሃ፥ ወቄቤጼይ ወመፋራቲሃ፡ አርባዕ አህጉር።

ሴኬም ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ቤቶሮን ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ጌዜር ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ቄቤጼይ ከመሠማሪያዎቿ ጋራ እነዚህ አራት አገሮች ናቸው።

፳፪ ወእምሕዝበ ዳን ኢሊቄቁም ወመፋራቲሃ፥ ወገባቶን ወመፋራቲሃ።

ከነገደ ዳን ዕጣም ኢሊቄቁም ከመሠማሪያዎቿ ጋራ፥ ገባቶን ከመሠማሪያዋ ጋራ። ኢያ፡ ፲፱ ፵፬።

፳፫ ወኤሎን ወመፋራቲሃ፡ ወጌቴርምን ወመፋራቲሃ፡ አርባዕ አህጉር።

ኤሎን ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ጌቴርምን ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ (ከነገደ ዳን) የተሰጡ እሊህ ዓራት አገሮች ናቸው።

፳፬ ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ ጠናሕ ወመፋራቲሃ፡ ወዮብት ወመፋራቲሃ፡ ክልኤቲ አህጉር።

ከነገደ ምናሴ እኩሌታ ዕጣ የተለዩ (የተሰጡ) አገሮች ጠናሕ ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ዮብታም ከመሠማሪያዋ ጋራ እነዚህ ሁለቱ አገሮች ናቸው። መሳ፡ ፩ ፲፱።

፳፭ ወኵሎን አህጉር ዐሥሩ ወመፋራቲሆን ዘቀሩቦን ለነገደ ደቂቀ ቀዓት እለ ተርፉ።

ለቀሩት ለቀዓት ልጆች ነገድ አቅራቢያዎች የሚሆኑ ከመሠማሪያዎች ጋራ የተሰጡ አገሮች ሁሉ ዓሥር ናቸው።

፳፮ ወለደቂቀ ጌድሶን ሌዋውያን እመንፈቀ ነገደ ምናሴ አህጉር እለ ፈለጡ ምስክየ ለቀታሊ፥ ጋውሎን በባሳን፥ ወመፋራቲሃ፥ ወአስጣሮት በባሶር ወመፋራቲሃ፡ ክልኤቲ አህጉር።

ለካህናት ለሆኑ ለጌድሶን ልጆችም ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከምናሴ ነገድ እኩሌታ የተለዩ አገሮች ከመሠማሪያዋ ጋራ በባሳን ያለች ጋውሎን፥ በባሶር ያለች አስጣሮት ከመሠማሪያዋ ጋራ እነዚህ ሁለቱ አገሮች ናቸው። ኢያ፡ ፳፩ ፮-፳፰። ፩ ዜና መ፡ ፮ ፸፩።

፳፯ ወእምነገደ እሴር መሴላ ወመፋራቲሃ፥ ወአቤጾን ወመፋራቲሃ፥ ወያቃቅ ወመፋራቲሃ፥ ወሮዓብ ወመፋራቲሃ፥ አርባዕ አህጉር።

ከነገደ አሴር ዕጣ የተለዩም አገሮች መሴላ ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ አቤጾን ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ያቃቅ ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ሮዓብ ከመሠማሪያዋ ጋራ እነዚህ አራቱ አገሮች ናቸው።

፳፰ ወእምነገደ ይሳኮር ቂስዮን ወዳቤራት ወመፋራቲሆን ያሬማት ወኤንጋን ወመፋራቲሆን፡ አርባዕ አህጉር።

ከነገደ ይሳኮር ዕጣ የተለዩም አገሮች ዳቤራታና ቂስዮን ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ፥ ያሬማትና ኤንጋን ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ እነዚህ አራቱ አገሮች ናቸው።

፳፱ ወእምሕዝበ ንፍታሌም ሀገር ዘፈለጡ ለቀታሊ ቃዴስ በገሊላ ወመፋራቲሃ፥ ወኤማት ወመፋራቲሃ፥ ወቀርያቴአም ወመፋራቲሃ፡ ሠለስ አህጉር።

ለነፍስ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከንፍታሌም ወገን ዕጣ የለዩዋቸውም አገሮች በገሊላ ያለች ቃዴስ ከመሠማሪያዋ ጋራ ኤማት ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ቀርያቴአም ከመሠማሪያዋ ጋራ እነዚህ ሦስቱ አገሮች ናቸው።

፴ ወኵሎን አህጉር ዘጌድሶን በበሕዘቢሆሙ ዓሥሩ ወሠላስ አህጉር።

በየወገኖቻቸው የጌድሶን ልጆች የተቀበሉዋቸው አገሮች ሁሉ ዓሥራ ሦስት አገሮች ናቸው።

፴፩ ወለነገደ ሕዝበ ሜራሪ እለ ተርፉ እምሌዋውያን እምሕዝበ ዛቡሎን፡ ኢያቅማን ወመፋራቲሃ፡ ወቃዴስ ወመፋራቲሃ።

ከሌዋውያን ለቀሩ ለሜራሪ ወገኖች ከዛብሎን ወገኖች ዕጣ የተሰጡ አገሮች ኢያቅማን ከመሠማሪያዋ ጋራ ቃዴስ ከመሠማሪያዋ ጋራ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org



፴፪ ወሲላ ወሙፋራቲሃ፤ ሚጊታኒ ወሙፋራቲሃ፥ አርባዕ አህጉር ።

፴፫ ወበማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ እምሕዝበ ሮቤል ሀገረ ምስክይ ለቃታሊ፥ ባሶር በገዳም ወሙፋራቲሃ ።

፴፬ ወያዜር ወሙፋራቲሃ፥ ወቄዴሞት ወሙፋራቲሃ፥ ወሚፌአት ወሙፋራቲሃ፥ አርባዕ አህጉር ።

፴፭ ወእምሕዝበ ጋድ ሀገር ለምስክዩ ቀታሊ ሬሞት በገለዓድ ወሙፋራቲሃ፥ ወምናኤም ወሙፋራቲሃ ።

፴፮ ወሐሴቦን ወሙፋራቲሃ፥ ወኢያኔዜር ወሙፋራቲሃ አርባዕ አህጉር ።

፴፯ ወኵሉ አህጉሪሆሙ ለእለ ተርፉ እምነገደ ሌዊ ለደቂቀ ሜራሪ በበነገዶሙ፥ ወኮነ ደወሎሙ እሥሩ ወክልኤቱ አህጉር ።

፴፰ ወኵሉ አህጉሪሆሙ ለሌዋውያን በማእከለ ደወሎሙ ለደቂቀ እስራኤል አርብዓ ወሰማኒ አህጉር ወሙፋራቲሆን፥ ዘዓውዶን ለእማንቱ አህጉር ።

፴፱ ለለሀገር ወሙፋራቲሃ፥ ዓውዳ ለሀገር ከማሁ ለኵሎን እላንቱ አህጉር ።

፵ ወፈጸመ ኢያሱ ከፊለ ምድር በበደወሎሙ፤ ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ምድረ ዘመሐለ ለአበዊሆሙ፥ ወተዋረስዋ ወነበሩ ውስቴታ ።

፵፩ ወአዕረፎሙ እግዚአብሔር እምእለ ዓውዶሙ በከመ መሐለ ለአበዊሆሙ፤ ወአልቦ እንከ መኑሂ ዘተቃወሞሙ ቅድመ ገጾሙ እምኵሉ ፀሮሙ፤ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ለኵሎሙ ፀሮሙ ውስተ እደዊሆሙ ።

፵፪ ወኢተርፈት አሐቲ ቃል እምኵሉ ሠናያት ዘይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ኵሉ በጽሖሙ ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

፩ ወእምዝ ጸውዖሙ ኢያሱ ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ።

፪ ወይቤሎሙ ለሊክሙ ሰማዕክሙ ኵሎ ዘአዘዘክሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ወሰማዕክሙ ቃልየ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ ።

፫ ወኢኀደግሙ አኀዊክሙ በእማንቱ መዋዕል ብዙኃት እስከ ዛቲ ዕለት ወሀቀብክሙ ትእዛዘ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ።

፬ ወይእዜሰ አዕረፎሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ ለአኀዊክሙ በከመ ይቤሎሙ ።

፭ ወይእዜኒ ተመየጡ ወእትዉ ውስተ አብያቲክሙ ወውስተ ደወልክሙ ውስተ ብሔር ዘወሀበክሙ ሙሴ ገብረ እግዚአብሔር በማዕዶተ ዮርዳኖስ ።

፮ ወባሕቱ ተዓቀቡ ከመ ትግበሩ ጥቀ ትእዛዘ ወሕገ ዘአዘዘክሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ከመ ታፍቅርዎ ለእግዚአብሔር አምላክነ ወትሑሩ በኵሉ ፍናዊሁ ወት

ሲላ ከመሠማሪያዋ ጋራ፤ ሚጊታኒ ከመሠማሪያዋ ጋራ እነዚህ አራት አገሮች ናቸው ። ኢያ፥ ፲፱ ፴፯ ።

በኢያሪኮ አንጻር ባለች ከዮርዳኖስ ማዶ ለነፍስ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ለሮቤል ወገኖች ዕጣ የተለዩ አገሮች በምድረ በዳ ያለች ባሶር ከመሠማሪያዋ ጋራ ።

ያዜር ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ቄዴሞት ከመሠማሪያዋ ጋራ ሚፌአት ከመሠማሪያዋ ጋር እነዚህ አራት አገሮች ናቸው ። ኢያ፥ ፳፰፥ ፲፫-፲፰ ።

ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ለጋድ ወገኖች የተለዩ አገሮችም በገለዓድ ያለች ሬሞት ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ምናኤም ከመሠማሪያዋ ጋራ ። ፩ ነገ፥ ፳፪ ፫ ።

ሐሴቦን ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ ኢያኔዜር ከመሠማሪያዋ ጋራ፥ እነዚህ አራት አገሮች ናቸው ።

ከነገደ ሌዊ ለቀሩ ለሜራሪ ልጆች በየነገዳቸው የደረሷቸው አገሮች ሁሉ እነዚህ ናቸው፤ አውራጃዎቻቸውም ዓሥራ ሁለት አገሮች ሆኑ ። ዘኍ፥ ፴፬ ፴፭ ።

በእስራኤል ልጆች አውራጃ መካከል ያሉ የሌዋውያን አገሮች ሁሉ በነዚያ አገሮች ዙርያ ካሉ ከመሠማሪያዎቻቸው ጋራ አርባ ስምንት አገሮች ናቸው ።

በአገር ያሉ ያንዳቱም ያንዳቱም አገር መሠማሪያዋ እንደነዚያ አገሮች መሠማሪያ ነው ። ዘኍ፥ ፴፭ ፯ ።

ኢያሱም በየአውራጃቸው ምድርን ከፍሎ ጨረሰ፤ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ልጆች ላባቶቻቸው የማለላቸውን አገር ሰጥቶአቸው ወርሰዋት በውስጧ ኖሩ ።

እግዚአብሔር ላባቶቻቸው እንደ ማለላቸው በዙርያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው አሳረፋቸው እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን በእጃቸው ጥሏቸዋልና ከዚያ በኋላ ከጠላቶቻቸው ሁሉ በፊታቸው ማንም ማን የተጣላቸው የለም ።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች ከተናገራቸው በጎ ነገር ሁሉ ሁሉም ደረሳቸው እንጂ አንድም የቀረች ቃል የለችም ።

ምዕራፍ ፳፪ ።

ከዚህ በኋላ ኢያሱ የጋድ ልጆችንና የሮቤል ልጆችን የምናሴ ነገድ እኩሌታን ጠራቸው ።

የእግዚአብሔር ወዳጁ ሙሴ ያዘዛችሁን ሁሉ እናንተ ሰምታችኋል፤ እኔ ያዘዝኋችሁንም ቃሌን ሰማችሁ ።

ብዙ በሆኑ በነዚያ ወራቶች እስከዚች ቀን ድረስ ወንድሞቻችሁን አልተዋቻሁም የፈጣሪያችን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ጠበቃችሁ ።

አሁን ግን ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንደነገራቸው ወንድሞቻችሁን አሳረፋቸው ።

አሁንም ተመልሳችሁ ወደ ቤታችሁ ግቡ፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ሰጣችሁ አገር አውራጃችሁ ተመለሱ ። ኢያ፥ ፲፫ ፰፥ ፳፫ ፩ ።

ነገር ግን ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን ልትወዱት በሥርዓቱም ሁሉ ጸንታችሁ ልትኖሩ ትእዛዙንም ልትጠብቁ በፍጹም ሰውነታችሁና በፍጹም ልቡናችሁ ልትከተሉትና

ዕቀቡ ትእዛዞ ወትትልውዎ ወታምልክዎ በኵሉ ልብክሙ ወበኵሉ ነፍስክሙ ።

፯ ወባረኮሙ ኢያሱ ወፈነዎሙ፣ ወአተዉ ውስተ አብያቲሆሙ ።

፰ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወሀቦሙ ሙሴ በባሳን፤ ወለመንፈቆሙሰ ወሀቦሙ ኢያሱ ምስለ አኀዊሆሙ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘኀበ ባሕር ።

፱ ወሶበ ፈነዎሙ ኢያሱ ውስተ አብያቲሆሙ፣ አተዉ ምስለ ብዙኅ ንዋይ፣ ወምስለ ብዙኅ እንስሳ፣ ወምስለ ወርቅ ወብሩር ወብርት ወሐፂን ወአልባስ ብዙኅ ጥቀ ዘተካፈሉ በርበረ ፀሮሙ ምስለ አኀዊሆሙ ።

፲ ወተመይጡ ወአተዉ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ እምደቂቀ ሸል እምነ ሴሎ ዘምድረ ከነአን ከመ ይሑሩ ውስተ ገለአድ ውስተ ደወሎሙ ወውስተ ርስቶሙ ዘተዋረስዋ በትእዛዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ ።

፲፩ ወበጽሑ ውስተ ገለአድ ዘዮርዳኖስ ዘምድረ ከነአን ወነደቁ ደቂቀ ጋድ ወደቂቀ ሮቤል ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ በህየ ምሥዋዐ ዐቢየ ዘያስተርኢ ።

፲፪ ወሰምዑ ደቂቀ እስራኤል ከመ ነደቁ ምሥዋዐ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ በውስተ ደወለ ምድረ ከነአን በኀበ ገለአድ ዘዮርዳኖስ በማዕዶቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ።

፲፫ ወሰምዑ ደቂቀ እስራኤል ኵሎሙ ወተጋብኡ ውስተ ሴሎ ከመ ይዕርጉ ወይትቃተልዎሙ ።

፲፬ ወለአኩ ደቂቀ እስራኤል ኀበ ደቂቀ ሮቤል ወኀበ ደቂቀ ጋድ ወኀበ መንፈቀ ነገደ ምናሴ ውስተ ምድረ ገለአድ ፊንሐስሃ ወልደ አልአዛር ወልደ አሮን ካህን ።

፲፭ ወዐሠርተ መላእክተ ምስሌሁ መልአክ አሐዱ አሐዱ እምአብያተ አበዊሆሙ እምኵሉ ነገደ እስራኤል እደወ መላእክተ አብያተ አበዊሆሙ ወመሳፍንተ እሙንቱ ለእስራኤል ።

፲፮ ወበጽሑ ኀበ ደቂቀ ጋድ ወኀበ ደቂቀ ሮቤል ወኀበ መንፈቀ ነገደ ምናሴ ውስተ ገለአድ ።

፲፯ ወነገርዎሙ ወይቤልዎሙ ከመዝ ይቤሉ ኵሉ ተዓይነ እግዚአብሔር ምንትኑ ዛቲ አበሳ ዘአበስክሙ ቅድመ አምላከ እራኤል ከመ ትኅድጉ ዮም ተሊዎቶ ለእግዚአብሔር ወትንድቁ ለክሙ ምሥዋዐ ወከመ ትክሐድዎ ዮም ለእግዚአብሔር ።

፲፰ አስተንአስክሙኑ ኀጢአቶ ለፌጎር ዘኢነጻሕነ እምኔሃ እስከ ዮም፣ ወኮነ መቅሠፍት ላዕለ ትዕይንቱ ለእግዚአብሔር ።

፲፱ ዮምኒ አንትሙ ኀደግሙ ተሊዎቶ ለእግዚአብሔር ወእምከመ አንትሙ ዮም ክሕድክምዎ ለእግዚአብሔር ጌሠመ ላዕለ ኵሉ እስራኤል ይከውን መቅሠፍት ።

፳ ወይእዜኒ እመ ትንእስክሙ ደወለ ምድርክሙ ዕድዉ ውስተ ኢየሩሳም ደወለ ምድረ እግዚአብሔር ኀበ ትነብር ህየ ደብተራሁ ለእግዚአብሔር ወተዋረሱ ምስሌነ ወኢትክሐድዎ ለእግዚአብሔር እስመ ነደቅሙ ምሥዋዐ አፍአ እምሥዋዒሁ ለእግዚአብሔር አምላክነ ።

ልታመልኩት የእግዚአብሔር ወዳጁ ሙሴ ያዘዛችሁን ሕጉንና ትእዛዙን ታደርጉ ዘንድ ፈጽማችሁ ተጠበቁ አላቸው።

ኢያሱም መርቆ አሰናበታቸው፤ ወደ ቤቶቻቸውም ገቡ ። ዘፀ፡ ፴፱ ፵፫ ። ኢያ፡ ፳፬ ፯ ።

ለምናሴ ነገድ እኩሌታም ሙሴ በባሳን ሰጣቸው ለእኩሌቶቹ ግን ኢያሱ ከወንድሞቻቸው ጋር በባሕር በኩል ባለች በዮርዳኖስ መካከል ሰጣቸው ። ኢያ፡ ፲፯ ፭ ።

ኢያሱ ወደየ ቤታቸው ባሰናበታቸው ጊዜ እጅግ ብዙ ከሆነ ከብትና ከብዙ ገንዘብ ጋራ ከወርቅና ከብር ከብረትና ከናስ ጋራ ተመለሱ፣ ከጠላቶቻቸውም ምርኮ ከወንድሞቻቸውም ጋር የተካፈሉት ልብስ እጅግ ብዙ ነው ።

የጋድና የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም እኩሌታ ከእስራኤል ልጆች ተለይተው በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሙሴ ቃል ወደ ወረሷት ርስታቸውና ወደ አውራጃቸው ወደ ገለዓድ ለመሄድ በከነዓን ካለች ከሴሎም ተመለሱ ።

የከነዓን ዕጣ በምትሆን በዮርዳኖስ ማዶ ወዳለች ወደ ገለዓድ ደርሰው የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች፣ የነገደ ምናሴም እኩሌታ በዚያ የሚታይ ታላቅ መሠውያን ሠሩ።

የእስራኤልም ልጆች የጋድ ልጆች የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም እኩሌቶች በከነዓን አውራጃ ባለች በእስራኤል ልጆች ማዶ የዮርዳኖስ ዕጣ በምትሆን በገለዓድ መሠውያን እንደ ሠሩ ሰሙ ። ዘዳ፡ ፲፫ ፲፪፣ ፲፬ ፲፭ ።

የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሰምተው ወጥተው ይዋጉዋቸው ዘንድ በሴሎ ተሰበሰቡ ። መሳ፡ ፳ ፩ ።

የእስራኤል ልጆች ከጋድ ልጆችና ከሮቤል ልጆች ከነገደ ምናሴም እኩሌታ ዘንድ አገልጋይ የሚሆን የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስን ገለአድ ወደሚባል አገር ላኩ ።

ዓሥር አለቆችም ከሱ ጋራ ሄዱ፣ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ የተቈጠሩ ያባቶቻቸው ወገኖች አለቆች አንዱም አንዱም አለቃ ከአባቶቻቸው ወገን የተቈጠሩ ናቸው፤ እነዚህም የእስራኤል ሹማምንት ናቸው ። ዘኍ፡ ፩ ፬ ።

በገለዓድ ወዳሉ ወደ ሮቤል ልጆች ወደ ጋድ ልጆች ወደ ነገደ ምናሴም እኩሌቶች ደርሰው ።

የእግዚአብሔር ሠራዊት ሁሉ እንዲህ አሉ ገዥ የሚሆን እግዚአብሔርን ማምለክ ትታችሁ መሠውያን ትሠሩ ዘንድ እግዚአብሔርንም አሁን ትክዱት ዘንድ በእስራኤል ፈጣሪ ፊት የሠራችኋት ይህች ኃጢአት ምንድር ናት፤ አሉ ብለው ነገሯቸው ። ዘሌ፡ ፲፯ ፱ ። ዘኍ፡ ፲፱ ፱ ።

እስከሁን ድረስ ከሷ ያልነጻን ጣኦቱን በማምለክ ያገኘችን ኃጢአትን በእግዚአብሔር ሠራዊት ላይ የተደረገ ያነን መቅሠፍት ታቃልሉታላችሁን፤ ።

አሁንም እናንተ እግዚአብሔርን ማምለክ ተዋችሁ፤ አሁን እናንተ እግዚአብሔርን ከካዳችሁት ነገ በእስራኤል ሁሉ መቅሠፍት ይደረጋል ። ዘኍ፡ ፲፯ ፳፪ ።

አሁንም ያገራችሁ አውራጃ ከነሳችሁ የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳን ወዳለችበት ወደ እግዚአብሔር አገር አውራጃ ወደ ኢየሩሳሌም ተሻገራችሁ ከኛ ጋራ ውረሱ፤ ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔር መሠውያ ውጭ መሠውያን ሠርታችኋልና እግዚአብሔርን አትክዱት ።

፳፩ አኮኑ አካን ወልደ ዛራ አመ አበሰ ወጌገየ ወነሥአ እም
ዘኃሩም ላዕለ ኵሉ ትዕይንተ እስራኤል ኮነ መቅሠፍት
ሰበ ባሕቲቱ አበሰ፣ በኑ ባሕቲቱ ሞተ በኃጢአቱ ።

፳፪ ወአውሥኡ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ
ነገደ ምናሴ ወይቤልዎሙ ለመላእክተ እስራኤል እንዘ ይ
ብሉ፣ እግዚአብሔር ውእቱ አምላክ ወእግዚእ ወአምላክ
አማልክት ውእቱ ።

፳፫ እግዚአብሔርሰ ውእቱ የአምር ወለእስራኤልኒ ውእቱ
የአምሮ ከመ አኮ ለክሒድ ወለአብሶ ዘገበርነ ቅድሜሁ
ለእግዚአብሔር ወእመ አኮሰ ኢያድኅነነ ዮም ።

፳፬ ወእመኒ ምሥዋዐ ነደቅነ ለነ ከመ ንክሕዶ ለእግዚአ
ብሔር አምላክነ ወከመ ናዕርግ ላዕሌሁ መሥዋዕተ ወቍር
ባነ ወእመኒ ከመ ንግበር ላዕሌሁ መሥዋዕተ መድኃኒት
ውእቱ ለሊሁ እግዚአብሔር ለይትኃሠሠ ።

፳፭ ወእመአኮሰ በበይነ ፍርሀተ ነገር ዘገበርናሁ ለዝንቱ
ግብር እንዘ ንብል ከመ ኢይበልዎሙ ጌሠመ ውሉድክሙ
ለውሉድነ ምንት ብክሙ ምስለ እግዚአብሔር አምላክ
እስራኤል ።

፳፮ እስመ አቀመ እግዚአብሔር ወሰነ ማእከሌክሙ ወማ
እከሌነ ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ም
ናሴ ለዮርዳኖስ አቀሞ ወአልብክሙ ክፍል ምስለ እግዚ
አብሔር ወይሬስይዎሙ ነኪራነ ውሉድክሙ ለውሉድነ
ከመ ኢያውዕእዎሙ እምአምልኮ እግዚአብሔር ።

፳፯ ወንቤ ከመ ንግበር ከመዝ ወንንድቅ ዘንተ ምሥዋዐ
አኮ በበይነ ቍርባን ወአኮ በበይነ መሥዋዕት ።

፳፰ አላ ከመ ይኩን ዝንቱ ስምዐ ማእከሌነ ወማእከሌክሙ
ማእከለ ውሉድነ ወማእከለ ውሉድክሙ እምድኅሬነ ከመ
ያምልክዎ አምልኮ ለእግዚአብሔር በቅድሜሁ በቍርባን
ክሙ ወበመሥዋዕተ መድኃኒትክሙ፣ ወኢይበልዎሙ
ውሉድክሙ ለውሉድነ ጌሠመ አልብክሙ ክፍል ምስለ
እግዚአብሔር ።

፳፱ ወንቤ እመ ኮነ ድኅረ ወይቤሉነ ጌሠመ አው ለውሉ
ድነ ከመ ይበልዎሙ ናሁ ርእዩ አምሳለ ምሥዋዑ ለእግ
ዚአብሔር ዘገብሩ አበዊነ አኮ በበይነ ቍርባን ወአኮ በበ
ይነ መሥዋዕት አላ ከመ ይኩን ስምዐ ማእከሌነ ወማ
እከሌክሙ ።

፴ ሐሰ ለነ እስከ ነኀድግ ተሊዎቶ ለእግዚአብሔር ዮም
ከመ ንክሐዶ ለእግዚአብሔር ወከመ ንንድቅ ለነ ምሥዋዐ
ለቍርባን ወለመሥዋዕተ ሰላም ወለመሥዋዕተ መድኃ
ኒት ዘእንበለ ውስተ ምሥዋዒሁ ለእግዚአብሔር አምላ
ክነ ዘቅድመ ደብተራሁ ።

፴፩ ወሰበ ሰምዐ ፊንሐስ ካህን ወኵሎሙ መላእክተ ተዓ
ይን ወመሳፍንተ እስራኤል እለ ምስሌሁ ቃለ ዘይቤል

የዛራ ልጅ አካን ፈጽሞ ስለ በደለ እርም ነገርንም ስለ
ወሰደ በእስራኤል ሠራዊት ላይ መቅሠፍት የተደረገ አይ
ደለምን፤ ብቻውን ቢበድል በኃጢአቱ ብቻውን ሞተን፤
አላቸው ። ኢያ፣ ፯ ፳፭ ።

የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም እኩ
ሌቶች እግዚአብሔር ገዥም ፈጣሪም ነው፣ የአማልክ
ትም አምላክ ነው ብለው ለእስራኤል መልእክተኞች
መለሱላቸው ።

እግዚአብሔር ግን ሁሉን ያውቃል ይህን ሥራ የሠራ
ነው እግዚአብሔርን ለመካድና ለመበደል እንዳይደለ እስ
ራኤልን እሱ ያውቀዋል ፤ ይህስ ካልሆነ አሁን አያድነን ።

እኛ መሠውያንውም ብንሠራ ፈጣሪያችን እግዚአብ
ሔርን እንክደው ዘንድ ቍርባኑንና መሥዋዕቱን በመሠ
ውያው ላይ ለመሠዋት አይደለም የድኅነት መሥዋዕትን
በሱ እናደርግ ዘንድ የሠራነውስ ቢሆን እሱ እግዚአብ
ሔር ይመራመረን ። ዘዳ፣ ፲፱ ፲፰ ። ፪ ሳሙ፣ ፰ ፲፯ ።

ነገ ልጆቻችሁ ልጆቻችንን ከእስራኤል ፈጣሪ ከእግዚ
አብሔር ጋራ ምን አላችሁ፤ እንዳይሉዋቸው ብለን ነገር
ስለ መፍራት ይህን ሥራ የሠራነውስ ካልሆነ እግዚአብ
ሔር ይመራመረን ። ዘፍ፣ ፴ ፴፫ ። ዘፀ፣ ፲፪ ፲፫ ።

እግዚአብሔር በኛና በናንተ መካከል ለጋድ ልጆችና
ለሮቤል ልጆች ለነገደ ምናሴም እኩሌቶች ዮርዳኖስን
ድንበር አድርጎ አጽንቶታልና ከእግዚአብሔር ጋር ዕድል
ፈንታ የላችሁም ብለው ልጆቻችሁ ልጆቻችንን ባዕድ
አድርገው እግዚአብሔርን ከማምለክ እንዳያወጡዋቸው
ብለን ይህን አደረግን ።

ስለዚህም መሠውያን እንሠራ ዘንድ እንሥራ አልን
እንጂ ለሚቃጠል መሥዋዕት ወይም ለሌላ መሥዋዕት
አይደለም ። ኢያ፣ ፳፪ ፳፰፣ ፳፬ ፳፯ ።

ነገር ግን በኛና በናንተ መካከል ድኅነት በሚገኝበት
መሥዋዕትና በቍርባናችሁ በፊቱ እግዚአብሔርን ያመል
ኩት ዘንድ ነገ ልጆቻችሁ ልጆቻችንን ከእግዚአብሔር
ጋር ዕድል ፈንታ የላችሁም እንዳይሉዋቸው ከኛም በኋላ
በልጆቻችንና በልጆቻችሁ መካከል ይህ ምስክር ይሆን
ዘንድ ነው እንጂ ስለ መሥዋዕትና ስለ ቍርባን አይደለም ።

ኋላ ይህ በተደረገ ጊዜ ነገ ይህ ምንድር ነው፤ ባሉን
ጊዜ ወይም ልጆቻችንን እንዲህ ባሏቸው ጊዜ እነሆ አባ
ቶቻችን የሠሩት የእግዚአብሔርን መሥዋዕት መሠውያ
አምሳል እዩ ይሉዋቸው ዘንድ ብለን በናንተና በኛ መካ
ከል ምስክር ይሆን ዘንድ ነው እንጂ፣ ስለ መሥዋዕትና
ስለ ቍርባን አይደለም ። ዘዳ፣ ፬ ፲፯ ።

በደብተራ ኦሪት አንጻር ባለ በፈጣሪያችን በእግዚአ
ብሔር መሠውያ እንሠዋለን እንጂ እግዚአብሔርን እንክ
ደው ዘንድ የፍቅር መሥዋዕትንና ቍርባንን ድኅነት የሚ
ገኝበት መሥዋዕትንም ልንሠዋ እኛ መሠውያን እንሠራ
ዘንድ እግዚአብሔርን ማምለክ እስክንተው ድረስ ደርሰን
ለኛ አገባባችን አይደለም አሏቸው ። ኢያ፣ ፳፬ ፲፯ ።

የሠራዊቱ አለቆች ሁሉና አገልጋይ የሚሆን ፊንሐስ
ከሱም ጋር ያሉ የእስራኤል ሹማምንት የጋድ ልጆችና

ዎሙ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ እርመሙ ወተፈሥሑ ።

የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም እኩሌቶች የነገሩዋቸውን ቃል በሰሙ ጊዜ ደስ ብሏቸው ዝም አሉ ።

፴፪ ወይቤሎሙ ፊንሐስ ወልደ አልአዛር ካህን ለደቂቀ ሮቤል ወለደቂቀ ጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ዮም አእመርነ ከመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌነ እስመ ኢአበስክሙ ቅድመ እግዚአብሔር ዘንተ ኀጢአተ ወእስመ አድኀንክምዎሙ ለእስራኤል እምእዴሁ ለእግዚአብሔር ።

አገልጋይ የሚሆን የአልአዛር ልጅ ፊንሐስም የጋድ ልጆችንና የሮቤልን ልጆች የነገደ ምናሴንም እኩሌቶች በእግዚአብሔር ፊት ይህን ኃጢአት አልሠራችሁምና ሽኤልንም ከእግዚአብሔር እጅ አድናችኋቸዋልና እግዚአብሔር በረድኤት ከኛ ጋራ እንዳለ አሁን አወቅን አላቸው።

፴፫ ወገብአ ፊንሐስ ወልደ አልአዛር ካህን ወመላእክተ ትዓይንኒ ምስሌሁ ኀበ ደቂቀ እስራኤል ወሐሩ ምስሌሆሙ መላእክት እምደቂቀ ሮቤል ወእምደቂቀ ጋድ ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ እምገለአድ ውስተ ምድረ ከነአን ኀበ ደቂቀ እስራኤል ።

የአገልጋዩ አልአዛር ልጅ ፊንሐስም ከሱ ጋራ ከሉ ከሠራዊቱ አለቆችም ጋራ ወደ እስራኤል ልጆች ተመለሱ ከጋድ ልጆችና ከሮቤል ልጆች ከነገደ ምናሴም እኩሌታ የተቈጠሩት አለቆችም ከእስራኤል ልጆች ዘንድ ከገለዓድ ወደ ከነዓን ከነሳቸው ጋራ ሄዱ ። ኢያ፣ ፳፪ ፲፣ ፲፩ ፲፫ ።

፴፬ ወነገርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ወአደሞሙ ዝንቱ ነገር ወሰበ ነገርዎሙ ለደቂቀ እስራኤል ባረክዎ ለአምላከ ደቂቀ እስራኤል ወይቤሉ ኢነዓርግ እንከ ኀቤሆሙ ከመ ንትቃተሎሙ ወከመ ናጥፍኢ ለምድረ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ዘነበሩ ላዕሌሃ ።

ለእስራኤል ልጆች ነገሩዋቸው ይህም ነገር እስራኤልን ደስ አሰኛቸው፤ ለእስራኤልም ልጆች በነገሩዋቸው ጊዜ የእስራኤል ልጆችን ፈጣሪ አመሰገኑት፤ የጋድ ልጆችና የሮቤል ልጆች የነገደ ምናሴም ልጆች እኩሌቶች የሚኖሩበት አገራቸውን እናጠፋት ዘንድ እንግዲህ ወደ ነሳቸው አንወጣም አሉ ። ፩ ዜና መዋ፣ ፳፱ ፳፩ ።

፴፭ ወሰመዮ ኢያሱ ለውእቱ ምሥዋዕ ስምዐ ዘሮቤል ወዘጋድ ወዘመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወይቤሉ እስመ ስምዕ ውእቱ ማእከሎሙ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ አምላኮሙ ።

ኢያሱም ያነን ግምብ የጋድና የሮቤል የነገደ ምናሴም እኩሌታ ምስክር አለው፤ (እስራኤልም) ፈጣሪያቸው እሱ እግዚአብሔር እንደሆነ በመከከላቸውም እሱ ምስክር ነውና ምስክር አሉት ። ዘፀ፣ ፲፰ ፬ ።

## ምዕራፍ ፳፫ ።

፩ ወእምዝ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል እምድኅረ አዕረፎሙ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል እምኵሉ ፀሮሙ ዘዓውዶሙ ወልህቀ ኢያሱ ወኀለፈ መዋሊሁ ።

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር በዙርያቸው ካሉ ከጠላቶቻቸው ሁሉ ካሳረፋቸው ከብዙ ዘመን በኋላ ኢያሱም የሕፃንነቱ ወራት አልፎ ካረጀ በኋላ ።

፪ ጸውዐ ኵሎ ደቂቀ እስራኤል ወሊቃናቲሆሙ ወመላእክቲሆሙ ወጸሐፍቶሙ ወመኳንንቲሆሙ ወይቤሎሙ ናሁ ረሣዕኩ አንሰ ወኀለፈ መዋዕልየ ።

ሽማግሎቻቸውንና የእስራኤልን ልጆች ሁሉ ጸሐፊዎቻቸውን አለቆቻቸውና መኳንንቶቻቸውንም ጠርቶ እነሆ እኔ አረጀሁ የሕፃንነቴም ወራት አለፈ ። ዘዳ፣ ፴፩ ፳፰ ።

፫ ወለሊክሙ ርኢክሙ ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር አምላክነ ላዕለ አሕዛብ እለ ቅድመ ገጽክሙ ከመ እግዚአብሔር አምላክነ ፀብአሙ ለነ ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንዳጠፋልን በፊታችሁ ባሉ አሕዛብ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ እናንተ አይታችኋል ። ዘፀ፣ ፲፱ ፲፬ ።

፬ ወናሁ ርእዩ ኀደጉ ለክሙ አሕዛበ እለ ተርፉ ውስተ እድዋሊክሙ ዘዘሕዘቢክሙ ወዘእምዮርዳኖስ ኵሎ አሕዛበ ዘሠረውክምዎሙ ወባሕር ዐቢይ ምዕራበ ፀሐይ ወሰንክሙ ።

እነሆ በየወገኖቻችሁ በአውራጃችሁ የቀሩ አሕዛብን ከዮርዳኖስ ጀምሮ ያጠፋኋቸው አሕዛብን ሁሉ ለናንተ እንደተውኩላችሁ እዩ ወሰናችሁም በፀሐይ መግቢያ ያለ ሰፊ ባሕር ነው ፡ ኢያ፣ ፲፫ ፯፣ ፲፭ ፲፪ ።

፭ ወእግዚአብሔር አምላክክሙ ውእቱ ያጠፍኦሙ ለክሙ እምቅድመ ገጽክሙ ወትወርሱ ምድሮሙ በከመ ይቤለነ እግዚአብሔር አምላክነ ።

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እሱ ከፊታችሁ ያጠፉላችኋል፤ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንደ ነገረን አገራቸውንም ትወርሳላችሁ ። ዘፀ፣ ፳፫ ፴ ። ኢያ፣ ፲፫ ፯ ።

፮ ወአጽንዑ ጥቀ ከመ ትዕቀቡ ወከመ ትግበሩ ኵሎ ዘጽሑፍ ውስተ መጽሐፈ ሕጉ ለሙሴ ከመ ኢትትገኃሡ እምኔሁ እምዘአዘዘክሙ ሙሴ ኢ ለየማን ወኢ ለፀጋም ከመ ኢትኣብሱ ።

ሕጉን ትጠብቁ ዘንድ የሙሴ ሥርዓቱ በተጻፈበት መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ ታደርጉ ዘንድ እንዳትበድሉ፤ ሙሴ ካዘዛችሁ ከሱ ወደ ቀኝም ወደ ግራም እንዳትሉ ፈጽማችሁ ልቡናችሁን አጽኑ ። ዘዳ፣ ፭ ፴፬ ።

፯ ወኢትባኡ ውስተ እሉ አሕዛብ እለ ተርፉ እምኔክሙ ወአስማተ አማልክቲሆሙ ኢይሰመይ በውስቴትክሙ ወኢትምሐሉ በሙ ወኢትስግዱ ሎሙ ወኢታምልክዎሙ ።

ከናንተም ወደ ቀሩ ወደ አሕዛብ አትግቡ፤ የጣኦቶቻቸውም ስም በናንተ ዘንድ አይጠራ፤ አትማሉባቸው አትስገዱላቸውም አታምልኩዋቸውም ። ዘፀ፣ ፳፫ ፴፫ ።

፰ አላ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ ትልውዎ በከመ ገብረ ለክሙ እስከ ዛቲ ዕለት ።

እስከዚች ቀን ድረስ እንዳደረገላችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን አምልኩት እንጂ እነሳቸውን አታምልኳቸው።

፱ ወውእቱ እግዚአብሔር ያጠፍኦሙ እምቅድመ ገጽ
ክሙ ለአሕዛብ ዐበይት ወጽኑዓን ወለክሙሰ አልቦ ዘተቃ
ወመክሙ ቅድሜክሙ እስከ ዛቲ ዕለት ።

፲ አሐዱ ብእሲ እምኔክሙ ይሰድድ ዐሥርተ ምእተ እስ
መ እግዚአብሔር አምላክነ ይፀብእ ለክሙ በከመ ይቤለነ።

፲፩ ወተዓቀቡ ጥቀ ነፍሰክሙ ከመ ታፍቅርዎ ለእግዚአ
ብሔር አምላክነ ።

፲፪ ወእመሰ ተመየጥክሙ ወኀደግምዎ ትገብኡ ውስተ
እሉ አሕዛብ እለ ተርፉ ምስሌክሙ ወኢትትዋሰቡ ምስሌ
ሆሙ ወኢትደመሩ ውስቴቶሙ ።

፲፫ ወለሊክሙ አእምሩ ከመ ኢያጠፍኦሙ እንከ እግዚ
አብሔር አምላክነ ለእሉ አሕዛብ እምቅድሜክሙ ወይ
ከውኑክሙ እንከ መሥገርተ ወዕቅፍተ ወቀኖታተ ውስተ
ሰኳንዊክሙ ወይደጕጹክሙ ውስተ አዕይንቲክሙ እስከ
ትጠፍኡ እምድር ቡርክት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር
አምላክክሙ ።

፲፬ ወአንሰ አሐውር ውስተ ፍኖት ከመ ኵሉ እለ ውስተ
ምድር፣ ወአእምሩ በኵሉ ልብክሙ ወበኵሉ ነፍስክሙ
ከመ ኢተኀድገት ወኢ አሐቲ ቃል እምኵሉ ሠናይት
ዘይቤለክሙ እግዚአብሔር አምላክነ ።

፲፭ ወኵሉ በጽሐነ ወአልቦ ዘኢረከብነ እምኔሁ፣ ወበ
ከመ በጽሐክሙ ኵሉ ቃል ሠናይ ዘይቤለክሙ እግዚአ
ብሔር አምላክክሙ ከማሁ ያመጽእ ላዕሌክሙ እግዚአብ
ሔር አምላክክሙ ኵሎ ቃለ እኩየ እስከ ያጠፍአክሙ
እምዛቲ ምድር ቡርክት ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር ።

፲፮ እምከመ ኀደግሙ ኪዳኖ ለአምላክክሙ ዘወሀበክሙ
ወዘአዘዘክሙ ወለመ ሖርክሙ ወአምለክሙ አማልክተ ባ
ዕድ ወሰገድክሙ ሎሙ ይትመዓዕ በመዐት እግዚአብሔር
ላዕሌክሙ ወፍጡነ ያጠፍአክሙ እምድር ዘወሀበክሙ ።

## ምዕራፍ ፳፬ ።

፩ ወአስተጋብኦሙ ኢያሱ ለኵሉ ሕዝበ እስራኤል ው
ስተ ሴሎም ወጸውዖሙ ለሊቃናተ እስራኤል ወለመላእክቲ
ሆሙ ወለጸሐፍቶሙ ወአቀሞሙ ቅድመ እግዚአብሔር ።

፪ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለኵሉ ሕዝብ ከመዝ ይቤ እግ
ዚአብሔር አምላክ እስራኤል፣ በማዕዶተ ፈለግ ነበሩ አበ
ዊክሙ ቀደምት ታራ አቡሁ ለአብርሃም ወአቡሁ ለናኮር
ወአምለኩ ባዕዳነ አማልክተ ።

፫ ወነሣእክዎ ለአብርሃም አቡክሙ እማዕዶተ ፈለግ ወወሰ
ድክዎ ውስተ ኵሉ ምድረ ከነአን ወአስተብዛኁኩ ዘርአ ።

፬ ወወሀብክዎ ይስሐቅሃ፣ ወለይስሐቅኒ ያዕቆብሃ ወኤሳ
ውሃ፣ ወወሃብክዎ ለኤሳው ደብረ ሴይር ወአውረስክዎ፣
ወያዕቆብሰ ወደቂቁ ወረዱ ውስተ ግብጽ ወኮኑ በህየ ሕዝ
በ ዐቢየ ወበዝኁ ወጸንዑ ወሣቀይዎሙ ግብጽ ።

፭ ወፈነውኩ ሙሴሃ ወአሮንሃ በከመ ገበርኩ በማእከ
ሎሙ ወቀተልክዎሙ ለግብጽ በበይነ ዘገብሩ ላዕሌሆሙ ።

፮ ወእምድኅረ ዝንቱ አውፃእክዎሙ ለአበዊክሙ ወበእ
ክሙ ውስተ ባሕር ወዴገኑክሙ ግብጽ ወተለዉክሙ ወተ

እሱ እግዚአብሔር ብዙ ጽኑ የሚሆኑ አሕዛብን ከፊ
ታችሁ ያጠፋቸዋል፣ እናንተን ግን እስከዚች ቀን ድረስ
ማንም በፊታችሁ የተቋቋማችሁ የለም ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እንደነገረን ይዋጋላችኋልና
ከናንተ አንድ ሰው ሺሑን ሰው ድል ያደርጋቸዋል ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ትወዱት ዘንድ ሰውነታ
ችሁን አጥብቃችሁ ጠብቁ ። ዘዳ፣ ፴ ፲፰ ። ኢያ፣ ፳፪ ፭ ።

(እግዚአብሔርን) ትታችሁ ወደ አሕዛብ ብትመለሱ
ግን ከናንተ ጋራ በቀሩ በነዚያ አሕዛብ እጅ ትጠፋላችሁ
ከነሳቸውም ጋር አትጋቡ፣ በግብርም አንድ አትሁኑ ።

(ይህን ካደረጋችሁ) ፈጣሪያችን እግዚአብሔር እነዚ
ህን አሕዛብን እንግዲህ ከፊታችሁ እንደማያጠፋቸው እና
ንተ ዕወቁ፣ እንግዲህ ዕንቅፋትና ወጥመድ በእግራችሁም
ችንካር ይሆኑባችኋል ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከሰጣ
ችሁ ከተባረከች አገር እስክትጠፉ ድረስ ዓይኖቻችሁን
ይጠነቁሏችኋል ።

እኔም በዚህ ዓለም እንዳሉ ሰዎች ሁሉ ወደ ሞት ጐ
ዳና እሄዳለሁ፣ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ከነገራችሁ በጎ
ነገር ሁሉ አንዲት ቃል ስንኳን እንዳልቀረች በፍጹም
ሰውነታችሁና በፍጹም ልቡናችሁ ዕወቁ ።

ሁሉ ደረሰን ከሱ ያላገኘነው የለም፣ ፈጣሪያችሁ እግ
ዚአብሔር የነገራችሁ በጎ ነገር ሁሉ እንደደረሳችሁ እግ
ዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚች ከተመረቀች አገር እስኪያ
ጠፋችሁ ድረስ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር እንዲሁ በና
ንተ ክፉ ነገር ሁሉ ያመጣባችኋል ።

ያዘዛችሁንና የሰጣችሁን የፈጣሪያችሁ የእግዚአብሔ
ርን መሐላ ካፈረሳችሁ ሄዳችሁ ልዩ በሆኑ ጣኦታትን ብታ
መልኩና ብትሰግዱላቸው እግዚአብሔር በናንተ ላይ ተቈ
ጥቶ ከሰጣችሁ አገር ላይ ፈጥኖ ያጠፋችኋል ።

## ምዕራፍ ፳፬ ።

ኢያሱ የእስራኤልን ወገኖች ሁሉ በሴሎም ሰበሰበ
ቸው፣ አለቆቻቸውንና የእስራኤልን ሽማግሎች ጸሐፎቶ
ቻቸውንም ጠርቶ በእግዚአብሔር ፊት አቆማቸው ።

ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ የሺል ፈጣሪ እግዚአብሔር እን
ዲህ አለ ፤ የቀደሙ አባቶቻችሁ የናኮር አባትና የአብርሃም
አባት ታራ በወንዝ ማዶ ነበሩ፣ ልዩ ጣኦታትን አመለኩ ።

አባታችሁ አብርሃምን ከወንዝ ማዶ አምጥቼ ወደ ከነ
ዓን ወሰድሁት፣ ዘሩንም አበዛሁለት ።

ለአብርሃም ይስሐቅን ሰጠሁት፣ ለይስሐቅም ዔሳው
ንና ያዕቆብን ሰጠሁት፣ ለዔሳው የሴይርን ተራራ ሰጥቼ
አወረስኩት፣ ያዕቆብና ልጆቹ ግን ወደ ግብጽ ወረዱ፣
በዚያም ብዙ ወገን ሆኑ በዙ ጸኑም የግብጽም ሰዎች መ
ከራ አጸኑባቸው ።

ሙሴንና አሮንን ላክሁ በመካከላቸው እንዳደረግሁትም
በነሱ ላይ ክፉ ስላደረጉ የግብጽን ሰዎች አጠፋኋቸው ።

ከዚህ በኋላ አባቶቻችሁን አወጣኋቸው ወደ ባሕረ
ኤርትራም ገባችሁ፣ የግብጽም ሰዎች ፈጽመው ተከተሏ

ለዉ ድኅሬሆሙ ለአበዊክሙ በአፍራስ ወበሠረገላት ው
ስተ ባሕረ ኤርትራ ።
፯ ወጸራሕክሙ ኀበ እግዚአብሔር ወፈነውኩ ደመና
ወቆባረ ማእከሌክሙ ወማእከለ ግብጽ ወአስተጋባእኩ ላዕ
ሌሆሙ ባሕረ ወደፈኖሙ ፣ ወርእያ አዕይንቲክሙ ኵሎ
ዘገበርኩ በምድረ ግብጽ ወነበርክሙ ብዙኀ መዋዕለ ው
ስተ ገዳም ።
፰ ወወሰድኩክሙ ውስተ ምድረ አሞሬዎን እለ ይነብሩ
በማዕዶተ ዮርዳኖስ ወተቃተሉሙ ሙሴ ወአግባእክዎሙ
ውስተ እዴክሙ ወተዋረስክሙ ምድሮሙ ወአጥፋእክ
ዎሙ እምቅድሜክሙ ።
፱ ወተንሥአ ባላቅ ወልደ ሰፎር ንጉሠ ሞአብ ወተቃተ
ሎሙ ለእስራኤል ወለአከ ወጸውዖ ለበለዓም ወልደ ቤዖር
ከመ ይርግምክሙ ።
፲ ወኢፈቀድኩ አጥፍእክሙ ወበረከተ ባረኩክሙ ወአ
ድኅንኩክሙ እምእዴሁ ።
፲፩ ወዐደውክሙ ዮርዳኖስ ወበጻሕክሙ ውስተ ኢያሪኮ
ወተቃተሉክሙ እለ ይነብሩ ውስተ ኢያሪኮ ወአሞሬዎን
ወከናኔዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወኢያቡሴዎን ወኬጤ
ዎን ወጌርጌሴዎን ወአግባእክዎሙ ውስተ እዴክሙ ።
፲፪ ወፈነውኩ ላዕሌሆሙ እምቅድሜክሙ ዐከተ ወሰደድ
ክዎሙ እምቅድሜክሙ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ ነገሥት ዘአ
ሞሬዎን አኮ በሰይፍከ ወአኮ በቀስትከ ።

፲፫ ወወሀብኩክሙ ምድረ ዘኢጻመውክሙ ባቲ ወአህጉረ
እለ ኢነደቅክሙ ነበርክሙ ውስቴቶን ወአዕፀደ ወይን
ወዘይት ዘኢተከልክሙ ትበልዑ አንትሙ ።
፲፬ ወይእዜኒ ፍርህዎ ለእግዚአብሔር ወአምልክዎ በጽ
ድቅ ወበርትዕ ወአሰስሉ እምኔክሙ አማልክተ ነኪር ዘአ
ምለኩ አበዊክሙ በማዕዶተ ፈለግ ወበግብጽ ወአምልክ
እምልክዎ ለእግዚአብሔር ።
፲፭ ወእመሰ ኢፈቀድክሙ ታምልክዎ ለእግዚአብሔር ኅ
ረዩ ለክሙ ዮም መነ ታመልኩ እመ አኮ አማልክተ አበ
ዊክሙ እለ ማዕዶተ ፈለግ ወእመ አኮ አማልክተ አሞሬ
ዎን እለ ውስተ ምድሮሙ ሀሎክሙ ዮም ወአንሰ ወቤትየ
እግዚአብሔርሃ ናመልክ እስመ ቅዱስ ውእቱ ።

፲፮ ወአውሥኡ ኵሉ ሕዝብ ወይቤሉ ሐሰ ለነ እስከ ነኀ
ድጎ ለእግዚአብሔር ወናመልክ ባዕዳነ አማልክተ ።
፲፯ ወለነሰ እግዚአብሔር አምላክነ እስመ ውእቱ አምላክ
ወውእቱ አውፅአነ ለነ ወለአበዊነ እምግብጽ ወእምቤተ
ቅኔት ወኵሎ ዘገብረ ለነ ተአምረ ዐበይተ ወዐቀበነ በኵሉ
ፍኖት እንተ ባቲ ሖርነ በውስተ ኵሉ አሕዛብ እለ ኀለፍነ
ላዕሌሆሙ ።
፲፰ ወአውፅአሙ እግዚአብሔር ለአሞሬዎን ወለኵሉ አሕ
ዛብ እለ ይነብሩ ውስተ ምድር እምቅድሜነ ወከማሁ ንሕ
ነሂ ናመልክ ለእግዚአብሔር እስመ ውእቱ አምላክነ ።

፲፱ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለሕዝብ ኢትክሉ አምልኮቶ ለእግ

ችሁ በፈረስና በሠረገላ ሁነው አባቶቻችሁን እስከ ኤርትራ
ባሕር ድረስ አባረሩዋቸው ። ዘፀ፡ ፲፬ ፴፯ - ፶፩ ።
እናንተ ወደ እግዚአብሔር ጮኻችሁ እኔም በግብጽ
ሰዎችና በናንተ መካከል ጽጋግንና ደመናን አመጣሁ፣ የኤ
ርትራንም ባሕር በነሳቸው ላይ ሰበሰብኩ ውኃም አሰጠ
ማቸው በግብጽ ያደረግሁትን ሁሉ ዓይኖቻችሁ አዩ፣ ከናን
ተም ጋራ በምድረ በዳ ብዙ ዘመን ኖርሁ ። ዘፀ፡ ፲፬ ፲ ።
በዮርዳኖስ ማዶ ወደሚኖሩ ወደአሞሬዎንም አገር
ወሰድኳችሁ ሙሴም ተዋጋቸው በእጃችሁም ጣልኳቸው
አገራቸውንም ወረሳችሁ በፊታችሁም አጠፋኋቸው ።
ዘኍ፡ ፳፩ ፳፩ - ፴፩ ።
የሞዓብ ንጉሥ የሰፎር ልጅ ባላቅም ተነሥቶ እስራኤ
ልን ተዋጋቸው፣ ይረግማችሁም ዘንድ የቢዖርን ልጅ በለ
ዓምን ልኮ አስጠራው ። ዘኍ፡ ፳፪ ፭ ። ዘዳ፡ ፳፫ ፬ ።
አጠፋችሁም ዘንድ አልወደድሁም ምርቃንን መረቅ
ኋችሁ፣ ከመርገሙ አዳንኳችሁ ። ዘዳ፡ ፳፫ ፳፰ ።
ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ወደ ኢያሪኮም ደረሳችሁ፣
በኢያሪኮ የሚኖሩ ከናኔዎንና አሞሬዎን፣ ኤዌዎንና ፌር
ዜዎን፣ ኬጤዎንና ኢያቡሴዎን፣ ጌርጌሴዎንም ተዋጓችሁ
እነዚህንም በእጃችሁ ጣልኳቸው ። ኢያ፡ ፫ ፲፬ ።
ከናንተ በፊት ተቈናጣጭ ዝንብ አመጣሁባቸው ዓሥ
ራ ሁለቱንም የአሞሬዎን ነገሥታት ከፊታችሁ አስወጥቼ
ሰደድኋቸው ፣ ነገር ግን ያጠፋኻቸው በጦርህና በሰይፍህ
አይደለም ። ዘፀ፡ ፳፫ ፳፰ ። ዘዳ፡ ፯ ፳ ።
ያልደከማችሁበትን አገር ሰጠኋችሁ ፣ ባልሠራችኋ
ቸውም መንደሮች ኖራችሁ፣ እናንተ ያልተከላችሁትን
የዘይቱንና የወይኑን ፍሬ ትበላላችሁ ።
አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩት፣ በሚገባና በእውነ
ትም አምልኩት አባቶቻችሁ በግብጽና በወንዝ ማዶ በሰ
ርያ አባቶቻችሁ ያመለኳቸው የአሕዛብ ጣኦታትንም ከና
ንተ አስወግዱ፣ እግዚአብሔርንም ፈጽማችሁ አምልኩት።
እግዚአብሔርን ታመልኩት ዘንድ በትወዱ ግን አሁን
ምረጡ፣ ማንንን ታመልኩ፤ ወይስ በወንዝ ማዶ አባቶቻ
ችሁ ያመልኳቸው የነበሩ ጣኦታትን ታመልኩን፤ ወይስ
አሁን በአገራቸው ያላችሁባቸው የአሞሬዎንን ጣኦታት
ታመልኩን፤ ወገኖቼና እኔ ግን እሱ ልዩ ነውና እግዚአብ
ሔርን እናመልከለን አላቸው ። ኢያ፡ ፳፬ ፲፬ ። ሩት ፩ ፷ ።
ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን ትተን ልዩ የሆኑ ጣኦ
ታትን እናመልክ ዘንድ አገባባችን አይደለም ።
ፈጣሪ እሱ ነውና፣ ከአገዛዝ ቤት ከግብጽ አባቶቻች
ንንና እኛን አውጥቶናልና ታላላቅ ተአምራትን ሁሉ ያደ
ረገልን እሱ ነውና፣ በነሳቸው ላይ አልፈን በሄድንባቸው
አሕዛብ ሁሉ በሄድንበት ጐዳና ሁሉ ጠብቆናልና ።
ዘዳ፡ ፮ ፲፪ ።
እግዚአብሔር በምድሪቱ (በከነዓን) የሚኖሩ አሕዛብን
ሁሉና አሞሬዎንን ከፊታችን አጥፍቶልናልና ለኛስ ፈጣ
ሪያችን እሱ ነውና፣ እኛም እንደዚሁ እግዚአብሔርን እና
መልከዋለን ብለው መለሱለት ።
ኢያሱም ሕዝቡን እሱ ልዩ ነውና፣ እሱ ለአምላክነቱ

ዚአብሔር እስመ ቅዱስ ውእቱ ወእምላክ ቀናኢ ውእቱ
ወኢምክመ አቅናእክምዎ ኢየኀድግ ለክሙ ኃጢአቲክሙ
ወአበሳክሙ ።
፳ ወእምከመ ኀደግምዎ ለእግዚአብሔር ወአምለክሙ
በዕድ አማልክተ የሐውር ወየሣቅየክሙ ወያጠፍአክሙ
ህየንተ ዘአሠነየ ላዕሌክሙ ።
፳፩ ወይቤልዎ ሕዝብ ለኢያሱ ዳዕሙ ለእግዚአብሔር
ናመልክ ።
፳፪ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለሕዝብ ለሊክሙ ስምዕ ላዕለ
ርእስክሙ ከመ ለሊክሙ ኀረይክምዎ ለእግዚአብሔር
ታምልክዎ ወይቤሉ ስምዕ ንሕነ ።
፳፫ ወይቤሎሙ ይእዜኒ አሰስሉ አማልክተ ነኪር ዘኀቤ
ክሙ ወአርትዑ ልበክሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላከ እስ
ራኤል ።
፳፬ ወይቤልዎ ሕዝብ ለኢያሱ ለእግዚአብሔር አምላክነ
ናመልክ ወቃለ ዚአሁ ንሰምዕ ።
፳፭ ወተካየዶሙ ኢያሱ ለሕዝብ በይእቲ ዕለት ወወሀቦሙ
ሕገ ወፍትሐ በሴሎም በቅድመ ደብተራሁ ለአምላከ እስ
ራኤል ።
፳፮ ወጸሐፈ ኢያሱ ለዝንቱ ነገር ውስተ መጽሐፈ ሕጉ
ለእግዚአብሔር ወነሥአ ኢያሱ እብነ ዐቢየ ወአቀማ መት
ሕተ ዕፀ ጠርቤንቶስ ቅድመ እግዚአብሔር ።
፳፯ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለኵሎሙ ሕዝብ ናሁ ዛቲ እብን
ስምዕ ላዕሌክሙ እስመ ይእቲ ሰምዓት ኵሎ ዘተብህለ በ
ኀበ እግዚአብሔር ዘከመ ተናገርክሙ ዮም ፣ ወትኩንክሙ
ይእቲ ስምዐ ላዕሌክሙ በደኀሪ መዋዕል ለእመ ሐሰውክ
ምዎ ለእግዚአብሔር አምላኪየ ።
፳፰ ወፈነዎሙ ኢያሱ ለሕዝብ ወአተዉ ኵሎሙ ውስተ
በሐውርቲሆሙ ወአምለክዎ እስራኤል ለእግዚአብሔር
በኵሉ መዋዕሊሁ ለኢያሱ ወበኵሉ መዋዕሊሆሙ ለሊቃ
ናት እለ እኁኑ መዋዕሊሆሙ እምድኅረ ኢያሱ ወኵሎሙ
እለ ርእዩ ግብሮ ለእግዚአብሔር ኵሎ ዘገብረ ለእስራኤል ።
፳፱ ወከነ እምድኅረ ዝንቱ ሞተ ኢያሱ ወልደ ነዌ ገብረ
እግዚአብሔር ወምእት ወዐሠርቱ ዓመታቲሁ ።
፴ ወቀበርዎ ውስተ ደወለ ርስቱ ተምናሥራኅ ውስተ ደ
ብረ ኤፍሬም እመንገለ መስዕ ለደብረ ገዓስ ህየ ።
፴፩ ወወደዩ ምስሌሁ ውስተ መቃብሩ ኀበ ቀበርዎ መጣ
ብሐ ዘእብን እለ ቦቱ ገዘርሙ ለደቂቀ እስራኤል በገልገላ
እመ ወፅኡ እምግብጽ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር ፣ ወህየ
ሀለዋ እስከ ዮም ።
፴፪ ወአዕፅምቲሁ ለዮሴፍ ዘአውፅኡ እምግብጽ ወከረዩ
ውስተ ሰቂማ ውስተ አሐዱ ገብር ዘገራህት ዘተሣየጣ ያዕ
ቆብ እምአሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ሰቂማ በምእት አበ
ግዕ ወወሀበ ለዮሴፍ ክፍሎ ።
፴፫ ወከነ እምድኅረ ዝንቱ አልአዛር ወልደ አሮን ሊቀ
ክህናት ሰበ ሞተ ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ብእር ዘውህበ
ለፊንሐስ ወልዱ በደብረ ኤፍሬም ።
፴፬ ወይእተ አሚረ ነሥኡ ደቂቀ እስራኤል ታቦቶ ለእግ
ዚአብሔር ወወሰድዋ ምስሌሆሙ ወፊንሐስ ክነ ሊቀ ክህ

የሚቀና ፈጣሪ ነውና፣ አምልኩትቱን ከለቀቃችሁት በደላ
ችሁንና ኃጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም ። ዘሌ፣ ፲፱ ፪።

እግዚአብሔርንም ትታችሁ ሌሎ ጣኦታትን ከመለክ
ችሁ ከናንተ ተለይቶ ሂዶ መከራ ያጸናብችኋል በጎ ነገር
በአደረገላችሁ ፈንታ ያጠፉችኋል አላቸው ።
ሕዝቡም ኢያሱን እግዚአብሔርን ብቻ እናመልከዋ
ለን አሉት ። ኢሱ፣ ፩ ፳፰ ። ኤር፣ ፲፯ ፲፫ ።
ኢያሱም ሕዝቡን ታመልኩት ዘንድ እናንተ እግዚ
አብሔርን እንደመረጣችሁት እናንተ ለራሳችሁ ምስክር
ናችሁ አላቸው፣ እነሱም አዎን ምስክር ነን አሉት ።
አሁንም በናንተ ዘንድ ያሉ የአሕዛብ ጣኦታትን አስወ
ግዳችሁ ልቡናችሁን ወደ እስራኤል ፈጣሪ አቅኑ አላቸው ።
ዘፍ፣ ፴፭ ፪ ። ኢያ፣ ፲ ፲፯ ።
ሕዝቡም ኢያሱን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እናመ
ልከዋለን የሱንም ቃል እንሰማለን አሉት ።
ኢያሱም በዚያች ቀን ሕዝቡን ተማማላቸው በእስራ
ኤል ፈጣሪ ድንኳንም ፊት በሴሎም ፍርድንና ሥርዓትን
አስተማራቸው ። ዘፀ፣ ፲፩ ፳፭ ። ፪ ነገ፣ ፲፩ ፲፯ ።
ኢያሱ ይህንን ነገር የእግዚአብሔር ሕግ በተጻፈበት
በኦሪት ጻፈው፣ ታላቅ ደንጊያም አምጥቶ በእግዚአብሔር
ፊት በጉዋም ሥር አቆማት ። ዘዳ፣ ፴፩ ፳፬ ።
ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ አሁን እንደ ተናገራችሁ በእግ
ዚአብሔር ዘንድ የተነገረውን ሰምታለችና እነሆ ይህች
ደንጊያ በናንተ ምስክር ናትና ኋላ በፍጻሜ ዘመን ፈጣሪ
እግዚአብሔርን ብትክዱት ይህች (ደንጊያ) በናንተ ምስክር
ትሁንባችሁ አላቸው ። ዘፍ፣ ፴፩ ፭ ። ዘሌ፣ ፲፱ ፲፩ ።
ኢያሱም ሕዝቡን አሰናበታቸው ሁሉም ወዳገራቸው
ገቡ፣ እስራኤልም በኢያሱ ዘመን ሁሉ ከኢያሱም ዘመን
በኋላ ዘመናቸው በበዛ በሽማግሎችም ዘመን ሁሉ ለእስ
ራኤል ያደረገውን የእግዚአብሔር ተአምራቱን ሁሉ ባዩ
ሰዎች ሁሉ ዘመን እግዚአብሔርን አመለኩት ።
ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ
የነዌ ልጅ ኢያሱ ሞተ ዘመኑም መቶ ዓሥር ነበረ ።
ከገዓስ ተራራ በስተቀኝ የኤፍሬም ዕፃ በምትሆን በር
ስቱ ተምናሥራሕ አውራጃ ቀበሩት ።
ከግብጽ በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር እንዳዘዘው የእስ
ራኤልን ልጆች በገልገላ የገረዘባቸው የቡልጭት ምላጮ
ችን እሱን በቀበሩበት መቃብር ከሱ ጋራ አብረው ቀበሩ
እስከሁን ድረስም በዚያ አሉ ። ዘዳ፣ ፴፩ ፪ ።
ከግብጽም ያወጡት የዮሴፍን አጥንት ያዕቆብ በሰቂማ
ከሚኖሩ ከአሞሬዎን በመቶ በጎች በገዛት ለዮሴፍ ፈንታ
አድርጎ በሰጣት እርሻ በአንድ ወገኑ በሰቂማ ቈፍረው
ቀበሩት ። ዘፍ፣ ፶፩ ፳፭፣ ፴፫ ፲፱ ።
ከዚህ በኋላ እንዲህ ሆነ፣ የአሮን ልጅ የካህናት አለቃ
አልአዛር በሞተ ጊዜ ለልጁ ለፊንሐስ በሰጠው በእር በም
ትባል አገር በኤፍሬም ዕጣ ቀበሩት ።
የዚያን ጊዜ የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔር ማደሪያ
ታቦትን ከነሱቸው ጋራ ይዘዋት ሄዱ፣ ፊንሐስም በሳባቱ

ናት ሀገሮት አልአዛር አቡሁ እስከ አመ ሞተ ወቀበርዎ ሎቱ
ውስተ ገበአን ውስተ ምድሮሙ፡ ወአተዉ ኵሎሙ ደቂቀ
እስራኤል ውስተ አብያቲሆሙ ወውስተ አህጉሪሆሙ።
፴፫ ወእምዝ አምለኩ ደቂቀ እስራኤል አስጠራጢን ወአ
ስጣሮት ወአማልክተ አሕዛብ እለ ዐውዶሙ ወአግብኦሙ
እግዚአብሔር ውስተ እደ ኤግሎም ንጉሠ ሞአብ፡ ወቀነ
ዮሙ ዐሠርተ ወሰመንተ ዓመተ።

ስለ አልአዛር ፈንታ እስኪሞት ድረስ ሊቀ ክህናት ሆነ፡
በገበዖን ባለች በአገራቸው መቃብር ቈፈሩለት፡ የእስራኤ
ልም ልጆች ሁሉ ወደ አገሮቻቸውና ወደ ቤቶቻቸው ገቡ።

ከዚህ በኋላ የእስራኤል ልጆች አስጣሮትንና አስጠራ
ጢንን በዙርያቸው ያሉ የአሕዛብን ጣኦታት አመለኩ፡
እግዚአብሔርም በሞዓብ ንጉሥ በኤግሎም እጅ ጣላቸው
ዓሥራ ስምንት ዓመት ገዛቸው።

ተፈጸመ ኦሪት ዘኢያሱ፡
ወስብሐት ለእግዚአብሔር ዘኢይቀብል ብሕረ ተውዳሱ፡
አሜን።

ለእግዚአብሔር ለዘለዓለሙ ክብር ምስጋና ይግባውና
ሆሴዕ (ኢያሱ) የተናገረው መጽሐፍ መላ
ተፈጸመ፡ አሜን በእውነት።